# የተዘመሩና ያልተዘመሩ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች፤ ዐውዳዊ ትንተና

መስፍን መሰለ

## አኅጽሮተ ጥናት

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጠዋት ሰንደቁ ላይ ሲወጣ፣ ማታ ደግሞ ከሰንደቁ ሲወርድ የሚዘመሩ መዝሙሮች በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ተደርሰው እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. መጨረሻ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደረገ፡፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በኢትዮጵያ የሥርዓት ለውጥ በመደረጉ መዝሙሮቹ ከአገልግሎት ታገዱ፡፡ አገልግሎት በሰጡትም ኾነ አገልግሎት ላይ ባልዋሉት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ላይ ምንም ዓይነት ጥናት አልተደረገም፡፡ በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የተንጸባረቁትን ሀገራዊ ይዘቶች መመርመር ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ለመረዳት ይጠቅማል፡፡ የዚኽ ጥናት ዋና መነሻ ምክንያትም እስከ ዛሬ በመዝሙሮቹ ላይ ጥናት አለመካኼዱ ነው፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ አገልግሎት ላይ የዋሉትንና ያልዋሉትን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ይዘት መመርመርና መተርጎም ነው፡፡ ከዚኽ ዐቢይ ዓላማ የሚመነጩ ዝርዝር ዓላማዎችም፡- ሀ) የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹን ለማዘጋጀት ያነሣሡ ታሪካዊ ምክንያቶችን መግለጽ፣ ለ) በመዝሙሮቹ የተንጸባረቁትን ታሪካዊ ክንዋኔዎች መግለጽ፣ ሐ) በመዝሙሮቹ የተነጸባረቁትን የፖለቲካ ሥልጣን ማራመጃ ሐሳቦች መረዳትና መተርጎም፤ እንዲሁም መ) የሀገር ፍቅር ስሜትን ለማዳበር የመዝሙሮቹ ፋይዳ ምን ያኽል ጠቃሚ እንደ ነበር ማሳየት ናቸው፡፡ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የተንፀባረቁትን ይዘቶች በታሪካዊ፣ በፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዐውዶች ውስጥ አስፈላጊ መረጃዎችን ከጽሑፍ ከሰፈሩ መዛግብት በማሰባሰብ በመዝሙሮቹ የተንፀባረቁትን ይዘቶች ለመተርጎም ተችሏል፡፡ ማስረጃዎቹም የተለያዩ መሠረታዊ መዛግብትን ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥቶችን፣ ዐዋጆችን፣ መጻሕፍትን፣ መጽሔቶችን፣ ጋዜጦችን፣ የምርምር ውጤቶችን፣ ቃለ ጉባዔዎችንና ደብዳቤዎችን መመርመር ናቸው፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ ሲኾን መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ የመረጃ ትንተናው የተካሄደው ዐውድን መሠረት በማድረግ የገላጭና የትረካ ስልቶችን በመጠቀም ነው፡፡ ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው የመጀመሪያዎቹ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች የተደረሱት፡- አንደኛ፣ ለዐምስት ዓመታት በጠላት ክብሯን አጥታ የነበረችውን ሰንደቅ ዓለማ ክብር ለማስመለስ የተከፈለውን መሥዋዕትነት ለመዘከር፤ ኹለተኛ፡- ዐርበኞች መሥዋዕትነት ከፍለው የሰንደቅ ዓላማዋን ክብር እንዳስመለሱት ኹሉ ወደፊትም ክብሯን ለማዋረድ ከሚያስቡና ከሚሞክሩ ጠላቶች ልጆቿ እንዲጠብቋት ለማትጋት ነበር፡፡ ዐርበኞች መሥዋዕትነት እንደከፈሉ ኹሉ ትውልዱም ንጉሠ ነገሥቱን፣ ሀገሩንና ክብሩን ለመጠበቅ እንዲተጋ፣ ብሔራዊ ፍቅሩ እንዲጎለብት መዝሙሮቹ ይቀሰቅሳሉ፡፡ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀል በሚዘመረው መዝሙር ንጉሠ ነገሥቱን ስለመውደድ የተገለጸው ሥልጣን ላይ የነበረው መንግሥት የፖለቲካ ማራመጃ ሐሳብ እንደነበርም ይጠቁማሉ፡፡ ከ፲፱፻፴፫ እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ያገለገሉት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ዐርበኛ፣ ንጉሥ፣ አገር፣ ነጻነትና ክብር የሚሉት ፖለቲካ ማራመጃ ሐሳቦች የተመረጡት ግጥሞች አገልግሎት ላይ ሳይውሉ በ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. የሥልጣን ለውጥ ተካኼደ፡፡ የተመረጡት የሰንደቅ ዓለማ መዝሙሮችም እንደ መጀመሪያዎቹ መዝሙሮች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ማስከበር የትውልዱ ኃላፊነት መኾኑን ይሰብካሉ፡፡ ሥልጣን ላይ የነበረውን መንግሥት የፖለቲካ ዓላማ ማራመጃ ሐሳቦችም

ተካተውበታል፡፡ ይኸን እንጂ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ በሥርዓት ለውጥ ምክንያት አገልግሎት ሳይሰጡ ቀሩ፡፡ በምትካቸውም የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች አልተዘጋጁም፡፡ ስለኾነም፣ የትውልድን ብሔራዊ ስሜት ሊያጎለብት የሚችል/ሉ መዝሙር/ሮች በማዘጋጀት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡-** [መዝሙር፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ዐውድ፣ ነጻነት፣ ዐርበኛ፣ ጀግና፣ ክብር፣ ንጉሥ፣ ጠላት፣ ኅብረተሰባዊነት]

## 1) መግቢያ

የኢጣልያ ጦር በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. የኢትዮጵያን ጦር ድል አድርጎ ንጉሡ ነገሥቱን ለስደት ዳረጋቸው፡፡ ለዐምስት ዓመታት ኢትዮጵያን ወርሮ የሀገሪቱን ሰንደቅ ዓላማ አውርዶ የራሱን ሰንደቅ ዓላማ ከመስቀሉም በላይ ብዙ የግፍ ተግባሮችን ፈጽሟል፡፡ ድርጊቱም ዐርበኞች ነጻነታቸውን ለማስከበር እንዲነሣሡ አድርጓቸዋል፡፡ የነጻነታቸውና የሀገራቸው ሉዓላዊነት ምልክት የኾነችውን ሰንደቅ ዓላማቸውን እንዲናፍቁና እንዲያስከብሩ ገፋፍቷቸዋል፡፡ መሥዋዕትነት ለመክፈል እንዲቆርጡ፣ እንዲተጉ፣ እንዲበረቱ፣ እንዲጸኑና ቆርጠው እንዲነሡ አድርጓቸዋል፡፡ መሥዋዕትነት ከፍለው ለነጻነት እንዲበቁ አስችሏቸዋል፡፡[1] ንጉሡ ነገሥቱም ለሀገራቸውና ለሥልጣናቸው በቅተዋል፡፡ ዐርበኞቹ በከፈሉት ከፍተኛ መሥዋዕትነት ኢትዮጵያውያን ነጻነታቸውን ካስመለሱ በኋላ ለሰንደቅ ዓላማቸው ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ገልጸዋል፣ በጋዜጣም ጽፈዋል፡፡ የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር በብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ልቦና ውስጥ ነበር፡፡ ከነጻነት በኋላ ሰንደቅ ዓላማውን ከአንቆለጳጰሱት ጸሐፍት መካከል ከበደ (፲፱፻፵፫) አንደኛው ናቸው፡፡

ሕዝቡ ለሰንደቅ ዓላማው የነበረውን ከፍተኛ ፍቅር ለመግለጽ፣ ይበልጥ ለማጎልበትና በወጣቱ ትውልድ ለማስረጽ ኹለት "የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የክብር ሰላምታ" መዝሙሮች በ፲፱፻፵፫ ዓ. ም. ተደረሱ፡፡ አንደኛው ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ሌላኛው ደግሞ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ በማጀቢያነት በትምህርት ቤት የሚዘመሩ ነበሩ፡፡ መዝሙሮቹም እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. መጨረሻ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በኢትዮጵያ የሥርዓት ለውጥ በመደረጉ ከአገልግሎት ታገዱ፡፡ በምትካቸው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮችን ለማዘጋጀት የሥነጽሑፍ ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ተጋበዙ፡፡ ተወዳዳሪዎች ካቀረቧቸው ግጥሞች መካከል ኹለቱ (አንዱ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ሌላኛው ደግሞ፣ ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ እንዲዘመሩ) ተመረጡ፡፡ የተመረጡት ግጥሞች አገልግሎት ላይ ሳይውሉ በ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. የሥርዓት ለውጥ ተካኼደ፡፡ ሥልጣን የያዘው ኢሕአዴግም የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር የማዘጋጀቱ ሥራ እንዲቀጥል አላደረገም፡፡

---

[1] ኢትዮጵያውያን ዐርበኞች (ኤርትራውያንም ነበሩበት) የኢጣሊያንን ወራሪ ጦር ለዐምስት ዓመታት በዘለቀ የሽምቅ ውጊያ ተፋልመዋል፡፡ በመጨረሻም ኢትዮጵያን ለቆ እንዲወጣ የተደረገው በእግሊዝ ጦር ድጋፍ ነው (ከበደ፣ ፲፱፻፷፱፤ ባሕሩ፣ ፪ሺህ)፡፡

በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ላይ ጥናት ማካኼድ ያስፈለገበት ምክንያት፣ አንደኛ ጥናት መደረጉን የሚገልጽ መረጃ ማግኘት አለመቻሉ ነው፡፡ ኹለተኛ፣ በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የተንጸባረቁትን ሀገራዊ ጉዳዮች መመርመር አስፈላጊ በመኾኑ ነው፡፡

የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ አገልግሎት ላይ የዋሉትንና ያልዋሉትን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች የሚያንጸባርቁትን ታሪካዊ[2]፣ ፖለቲካዊ[3]ና ማኅበራዊ[4] ጉዳዮች መመርመር ነው፡፡ ከዚኽ ዐቢይ ዓላማ የሚመነጩ ዝርዝር ዓላማዎችም ሀ) የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹን ለማዘጋጀት ያነሣሡ ታሪካዊ ምክንያቶችን መፈተሽ፣ ለ) ስለመጀመሪያዎቹ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች በተለያዩ ጸሐፍት የተነገረውን መቃኘት፣ ሐ) በመዝሙሮቹ የተንጸባረቁትን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ክንዋኔዎች መመርመር፣ መ) በመዝሙሮቹ የተነጸባረቁትን የፖለቲካ ሥልጣን ማራመጃ ሐሳቦች መረዳትና መተንተን፤ እንዲሁም ሠ) የሀገር ፍቅርን ለማዳበር የመዝሙሮቹ ፋይዳ ምን ያኽል እንደ ነበር መመርመር ናቸው፡፡

የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹን ለመድረስ ያነሣሡ ታሪካዊ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? ስለመጀመሪያዎቹ የሰንደንቅ ዓላማ መዝሙሮች ጸሐፍት ምን አሉ? መዝሙሮቹ የተደረሱባቸውን ታሪካዊ ዐውዶች ምን ያኽል ያንጸባርቃሉ? በሥልጣን ላይ የነበሩትን መንግሥታት የፖለቲካ ማራመጃ ሐሳቦች ምን ያኽል ይገልጻሉ? ብሔራዊ ማንነት ለማዳበር የመዝሙሮቹ ፋይዳ ምን ያኽል እንደ ነበር? የሚሉትን ጥያቄዎች በጥናቱ ለመመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት አገልግሎት ይሰጡ የነበሩትንና የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት አገልግሎት እንዲሰጡ የተመረጡትን የሰንደቅ ዓላማ

---

[2]ታሪካዊ የሚለው ቅጽል የሚገልጸው የዘመርናቸውና ያልዘመርናቸው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ከመደራሳቸው በፊትና በተደረሱበት ወቅት የተካኼዱና የተመዘገቡ ክዋኔዎችን በጊዜ ቅደም ተከተል መመርመርን ነው፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት፣ ዐርበኞች፣ የኢጣሊያ፣ የእንግሊዝና የሱዳን መንግሥታት ድርጊቶች፣ በጊዜው የነበሩትን ሁኔታዎች፣ በኢትዮጵያ የተካኼደውን የመንግሥት ለውጥ፣ ርዕዮተ ዓለም፣ ወዘተርፈ መመርመራቸው ታሪካዊ የሚለው ቃል ይገልጻል፡፡

[3]ስለፖለቲካ ምንነት የተሰጠው ትርጉም ፖለቲካዊ የሚለውን ቅጽል ይገልጻል፡፡ ቃሉም "የኅብረተሰብ አደረጃጀትን፣ የመንግሥት ይዘትን፣ ቅርፅንና ተግባርን፣ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች መሠረታዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የሚያደርጉትን ትግል፣ በመንግሥታት መካከል የሚፈጠሩትን ግንኙነቶች ማለትም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲንም በሚመለከት የተወሰነ መደብ የሚኖረውን ንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤና ከዚኹ የሚመነጨውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያጠቃልላል፡፡" (ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1978፤ 508) ይኽ ሰፊ ትርጉም ቃሉ በዚኽ ጥናት ያለውን አገልግሎት ይገልጻል፡፡ ከዚኽም በላይ፣ ኢትዮጵያውያን ነጻነታቸውን ለማስመለስ፣ ሉዓላዊነታቸውንና ሰንደቅ ዓላማቸውን ለማስከበር ያደረጉት ትግል የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ የተደረገው እንቅስቃሴ ፖለቲካዊ ነው ሊባል ይችላል፡፡

[4]ማኅበራዊ የሚለው ቅጽል የሰዎችን ማኅበራዊ ግንኙነት፣ ማኅበራዊ አኗኗር/ሕይወት፣ እርስበርሳቸውና ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርጉትን መስተጋብር ወዘተ. ይገልጻል፡፡ "ሰዎች በኅሊናዊ ሕይወታቸው ውስጥ የሚቀርጿቸው ሐሳቦች፣ ዝንባሌዎች፣ ግምቶች፣ ማኅበራዊ ሥነልቡናዎች (ፍልስፍና፣ ኪነታዊ አስተሳሰቦች፣ ሃይማት፣ ሥነምግባራዊ አመለካከቶች ወዘተ.) የሚመነጩትና የሚያንጸባርቁት አኗኗራቸውን ማኅበራዊ ሕይወታቸውን፣ እርስ በእርሳቸውና ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ነው፡፡" (ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1978፤ 77) በመኾኑም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በእርሱ ያደርገው የነበረው ግንኙነት፣ ዐርበኞች የዐርበኝነት ተግባራቸውን ለመፈጸም ያነሣሣ ጉዳይ፣ ሐዝብ ስለንጉሡ የነበረው አመለካከት፣ ስለነጻነቱና ስለሰንደቅ ዓላማው የነበረው ግንዛቤ፣ መንግሥት ይከተለው የነበረው ርዕዮተ ዓለም ወዘተርፈ በማኅበራዊ ጉዳይነት የሚፈረጁ ናቸው፡፡

መዝሙሮች ማጥናት የተለያዩ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ መዝሙሮቹን መመርመር ለታሪካችን ሊኖረን የሚገባውን ዕውቀት ያሰፋል፡፡ አባቶች ለነጻነት የከፈሉትን መሥዋዕትነት ተተኪው ትውልድ እንዲረዳና ኃላፊነቱን ለመወጣት እንዲተጋ ለማድረግ የተደረገውን ጥረት ለመገንዘብ ይረዳል፡፡ በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች የፖለቲካ ማራመጃ ሐሳቦች እንዴት እንደተንጸባረቁና ብሔራዊ ስሜትን ለማዳበር፣ ሰንደቅ ዓላማ የነጻነትና የሉዓላዊነት ትእምርት መኾኑን በትውልዱ ለማስረጽ የተደረገውን ጥረት ለመረዳት ያስችላል፡፡

ጥናቱ በተዘመሩና ባልተዘመሩ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ግጥሞች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመዝሙሮቹ የተንፀባረቁትን ታሪካዊ ድርጊቶች፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ለመረዳት ተገቢ ናቸው የተባሉ ምንጮች በማገናዘቢያነት ተመርምረዋል፡፡ የመረጃ ምንጮቹም የኢትዮጵያ ሕግጋተ መንግሥታት፣ ዐዋጆች፣ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎች፣ ቃለ ጉባዔዎችና ደብዳቤዎች ናቸው፡፡ መዝሙሮቹ የተተነተኑት የመረጃ ምንጮቹን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዐውዶች መሠረት በማድረግና ገላጭ የትንተና ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡

የተዘመሩት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ተደርሠው አገልግሎት ይሰጡ የነበረው "ኢትዮጵያ ሆይ" በሚል የሚታወቀው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር አገልግሎት ይሰጥ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ ያልተዘመሩት የኢትዮጵያ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ደግሞ ለአገልግሎት የተዘጋጁት የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ማዝሙር የተካውና "ኢትዮጵያ ቅደሚ" በሚል የሚታወቀው መዝሙር አገልግሎት ይሰጥ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡

የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ ታሪክን፣ ነጻነትን፣ ክብርን፣ ዐርበኝነትን፣ ጀግንነትንና ርዕዮተ ዓለምን ማንጸባረቃቸው ከሕዝብ መዝሙር ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ አገልግሎታቸውም በትምህርት ቤት ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀል፣ ማታ ደግሞ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ በመኾኑ የሕዝብ መዝሙር ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ጋር በዚኽ ይመሳሰላሉ፡፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የሀገር ትእምርት ናቸው፡፡ በኢትዮጵያውያን መካከል አንድነትንና ብሔራዊ ስሜትን የሚያጎለብቱ በመኾናቸው ከሕዝብ መዝሙር ጋር ተመሳሳይ ተግባር አላቸው፡፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ እንደ ሕዝብ መዝሙር በብሔራዊ በዓላት፣ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ስርጭት መዝጊያ፣ በስፖርታዊ ክንዋኔዎች፣ የውጭ እንግዳ በመቀበል፣ በውጭ ሀገር ኢምባሲዎችና ቆንስላዎች ወዘተርፈ አይዘመሩም፡፡ በሌሎች አገሮች የሕዝብ መዝሙርን የተመለከተ እንጂ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ላይ የተጻፈ መረጃ ማግኘት ባለመቻሉ ከለሳ ድርሳን ማካኼድ አልተቻለም፡፡

ቀጥለን በቅድሚያ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን በመዝሙር መግለጽ መቼ እንደተጀመረ እንመለከታለን፡፡ ይኽም የሰንደቅ ዓላማንና የመዝሙርን ጥምረት ታሪክና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ አገልግሎት እንዴት እንደነበርና ለምንስ እነደታሰበ ለመረዳት ያስችላል፡፡

## 2) የሰንደቅ ዓላማ ክብር ታሪክ በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ክብርና የሰንደቅ ዓላማውን ቀለማትና ትርጉም በመዝሙሮች መግለጽ የሰንደቅ ዓለማ መዝሙሮች ከመደራሳቸው በፊት የተለመደ ነበር፡፡ በ፲፱፻፲፯ ዓ. ም. ለመጀመሪያ

ጊዜ በቀረበው የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት መዝሙር[5]፣ "የኢትዮጵያን ብርሃን" በሚል ርእስ "ለሦስት ቀለሞች ጽናት" በሚል አዝማች አረንጓዴው፣ ብጫውና ቀዩ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቀለማት ተደጋግመው ተጠርተዋል፡፡ በመዝሙሩ መሥዋዕትነት በመክፈል ሰንደቅ ዓላማውን ለማስከበር የውዴታ ግዴታ ቃል ኪዳን መግባታቸው፣ ተስፋ መስጠታቸው ተገልጿል፡፡ ከዚኽ ከየተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት መዝሙር በኋላም በተለያዩ ጊዜያት በተደረሱት መዝሙሮች[6] የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ምንነትና የነጻነት ትእምርትነት በልዩ ልዩ መንገድ የሚገልጹ መዝሙሮች ተዘምረዋል፡፡ መዝሙሮቹም በትምህርት ቤቶች፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኰንን (የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከተባሉ በኋላም) የልደት በዓል፣ የውጭ ሀገር እንግዶች ትምህርት ቤቶችን በተለይም የተፈሪ መኰንንን እና የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክን ትምህርት ቤቶች ሲጎበኙ ይዘመሩ ነበር፡፡[7] በዓመቱ መጨረሻ በክረምቱ ምክንያት ትምህርት ቤቶች ለዕረፍት ሲዘጉ በሚኖረው ሥነሥርዓት ላይ መዘመራቸው ይታወቃል፡፡[8]

የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያ ለመውረር እንቅስቃሴ ማድረጉ እንደታወቀ ዐርበኞች ሀገራቸውን ከጥቃቱ እንዲከላከሉ በተቀሰቀሱባቸው ግጥሞች ሰንደቅ ዓላማውን የማስከበር ተግባር እንዳለባቸው ተመክረዋል፡፡ ለዚኽ ማስረጃ በወልደ ጊዮርጊስ ወልድ ዮሐንስ (ሺ፱፻፳፯፤፱ኛ ክፍል)፡-

> ሰንደቅ ዓላማችን ክርስቲያናዊቱ፡፡
> ለጠላት (ለጣኦት) እንዳትሰግድ አርበኞች መክቱ፡፡
> አርበኛው ዘመማቹ ባለሃይማኖቱ፡፡

በማለት የተገጠመው ማስረጃ ነው፡፡

---

[5]መዝሙሩ ብርሃንና ሰላም፣ (መጀመሪ[ሪያ] ዓመት፣ ቁጥር ፴፩፣ ሐሙስ መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፲፯፤ ፻፳፩)፣ የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት አጭር ታሪክ (፲፱፻፵፪፤ ፱)፣ በመርስዔ ኀዘን (፲፱፻፺፱) እና በዮሐንስ (፪ሺህ፩) ተመዝግቧል፡፡

[6]ለምሳሌ፣ በብርሃንና ሰላም፣ መጀመሪ [ሪያ] ዓመት፣ ቁጥር ፴፰፣ ሐሙስ መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፲፰፤ በብርሃንና ሰላም፣ ሦስተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፳፩፣ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፲፱፤ በብርሃንና ሰላም፣ ሰባተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፣ ሐሙስ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፫፤ በብርሃንና ሰላም፣ ሰባተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፣ ሐሙስ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፫፤ በብርሃንና ሰላም ስምንተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፩፣ ሐሙስ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፬፤ በብርሃንና ሰላም፣ ዐሥረኛ ዓመት፣ ቁጥር ፵፣ ሐሙስ መስከረም ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፮፣ ጋዜጣ ላይ በታተሙት መዝሙሮች የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ልዩ ልዩ ገጽታና የነጻነት ትእምርትነት ተገልጿል፡፡

[7]በክረምቱ ምክንያት ትምህርት ቤቶች ለዕረፍት ሲዘጉም፣ እንግዶችም ትምህርት ቤቶችን ሲጎበኙ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የሚያንቆለጳጵሱ መዝሙሮችም፣ ሌሎች መዝሙሮችም ይዘመሩ ነበር፡፡ በትምህርት ቤቶችና በሌላም አጋጣሚዎች ይዘመሩ ከነበሩ መዝሙሮች መካከል በ፲፱፻፲፯ ዓ. ም. መዘመር የተጀመረው ማርሽ ተፈሪ እና በ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. መዘመር የተጀመረው የኢትዮጵያ ማርሽ (የኢትዮጵያ የሕዝብ መዝሙር) ይጠቀሳሉ፡፡ መዝሙሮቹ የሚዘመሩት ሕግና ሥርዓት ተበጅቶላቸው አልነበረም፡፡ ዘማሪዎቹ፣ ወይም የዝግጅት አስተባባሪዎች ተገቢ ነው ያሉትን መዝሙር በማስቀደም ሌላኛውን በማስከተል ወይም አንዱን ብቻ በመምረጥ እንዲዘመሩ/ር ያደርጉ ነበር፡፡

[8]መዝሙሮቹ ሰንደቅ ዓላማውን የሚገልጹ ይኹን እንጂ ሰንደቅ ዓላማው ሲሰቀልም፣ ሲወርድም መዘመራቸውን የሚገልጽ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ እንዲሁም የኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን ከመውረሩ ከ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በፊት ጠዋት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ምሽት ደግሞ ሰንቅ ዓላማው ሲወርድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ስለመዘመሩ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ከበደ ሚካኤልም (፲፱፻፴፫፤ ፴፬) ሰንደቅ ዓላማን ካንቆለጳጰሱባቸውና ከፍ አድርገው ከገለጹባቸው *ሥንኞች* መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

> *ሹመት ነጻነት ነው ሽልማት ባንዲራ*
> *ስምን የሚያስከብር ልብን የሚያኮራ፡፡*
>
> *ነጻነት ከሌለ ባንዲራ ካልቆመ*
> *ርስትና ገንዘብ ምንም አልጠቀመ፡፡*
>
> *ባንዲራ ከሌለ ሕዝብ ይሆናል ደሀ*
> *ወንድምም ባዕድ ነው አገሩም በረሀ፡፡*
>
> *ነጻነት ሲጠፋ ባንዲራ ሲታጠፍ*
> *ባላንጣ ሲገፋ ዐርበኛ ሲሸነፍ፡፡*
> *ሀብታሙ ድሀ ነው ጌታው ስደተኛ*
> *ብልሁ ደንቆሮ ነው ቁጡው ትግሥተኛ፡፡*
> *ጎበዝ ደካማ ነው አፈኛውም ዲዳ*
> *ወዳጅህ ጠላት ነው ዘመድህም ባዳ፡፡*
> *ባንዲራ ካልቆመ ነጻነት ካልጠና*
> *ኑሮና ደስታ አልተገኘም ጤና፡፡*

በተጠቀሱት *ሥንኞች* እንደተገለጸው ነጻነት እና "ባንዲራ" አይነጣጠሉም፡፡ ነጻነት ካለ ሰንደቅ ዓላማው ይከበራል፤ ነጻነት የእያንዳንዱን ዜጋ ስም ያስከብራል፤ ልብንም ያኮራል፡፡ ነጻነት ከሌለ፣ ሕዝቡ በሀብቱ፣ ንብረቱ ሊያዝበት፣ ሊጠቀምበት አይችልም፡፡ ሰንደቅ ዓላማ በክብር መውለበለቡ ቀርቶ ይታጠፋል፤ ዜጎችም ማኅበራዊ ክብር አይኖራቸውም፡፡ ሀብታም፣ ጌታ፣ ብልህ፣ ጎበዝ፣ አንደበተ ርቱእ የሚባል አይኖርም፡፡ ኹሉም አፈ ድዳ፣ ቀንደ ጎዳ ይኾናል፡፡

እንደዚሁም፣ "የነጻነት ክብር፣ የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር እየታደሰ ስለመሔዱ" በሚል ርእስ ገዛኸኝ ውቤ በ<u>*አዲስ ዘመን*</u> (፲፱፻፴፬፤ ፪) ጋዜጣ ላይ ባሳተሙት ጽሑፍ የኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን በመውረሩና ነጻነት በመጥፋቱ ሕዝቡ ስለ ሰንደቅ ዓላማው የነበረውን ስሜት እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> *በአዲሱ ዘመን አሁን ባለንበት ጊዜ የነጻነት ክብር ታወቀ፤ የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር እየጸና ሔደ፡፡ ዱሮ ነጻነት ምን እንደሆነ፣ ሰንደቅ ዓላማ የነጻነት መሪ እንደሆነች የሚያውቁት እንዳሉም ጥቂቶች ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ሁላችንም ታሪኳንና ክብሯን ፈጽመን አናውቅም ነበር፡፡ እኛስ እንደሚመስለን እንደ ቀስተ-ደመና ፫ ቀለማት መሆኑን ብቻ እንመለከት ነበረ፡፡ ሥራዋም ደግሞ የነጋሪት መቾ ምልክትና የሰልፍ ማድመቂያ ትመስለን ነበረ፡፡ አሁን ግን ሙሶሎኒ በጭከና ከቀጣነ በኋላ በድል አድራጊው በግርማዊ ንጉሣችን*

> በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ብርታትና ብልሃት በልዑል እግዚአብሔር ቸርነትና መሐሪነት፣ የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር በየአንዳንዳችን በሁላችን ልብ ስለ ተሳለችብን እያሰብን ምንም የብሉይ ትርጓሜዋን ሊቃውንት ቢያውቁላት እኛም አሁን የኢትዮጵያ ልጆች ሴት ወንድ ሳንለይ የፍቅሯ ናፍቆት በሰውነታችን እየጸናና እየታደሰ ስለ ሔደ ሁሉም በየራሱ ሊሸከማት ፈለገ፤ ወደደ፤ ተሸከማትም፡፡
>
> ...አንዱ በራሱ ላይ፣ በባርኔጣው ላይ አድርጎ በማክበር የተሸከማት አለ፡፡ አንዱ በአንገቱ ላይ፣ አንዱ በጫንቃው ላይ፣ አንዱ በወገቡ ላይ ጠምጥሞና ሰፍቶ ተሸክሞአታል፡፡ አንዱም ከልብሱ ከኩታው ላይ ጥለት ጌጥ አድርጎ በፍቅር ተጎናጥፎ ለብሿት ይታያል፡፡ አንዱም ከቤቱ ደጃፍ፤ አንዱም ከቤቱ ጉልላት ላይ ሰቅሎ ይታያል፡፡ ፩ዱ በክንዱ ሰቅሎ ይታያል፡፡

ጸሐፊው እንደገለጹት ሙሶሎኒ ኢትዮጵያን ወርሮ የኢትዮጵያውያን የነጻነት ምልክት የሆነውን ሰንደቅ ዓላማ አውርዶ በራሱ መተካቱ፣ ሕዝቡን በጭካኔ መቅጣቱ፣ አካል ማጉደሉና ንብረት ማውደሙ በሕዝቡ ላይ የኀዘንና የመከፋት ስሜት ፈጠረ፡፡ የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን ከመውረሩ በፊት ክብር ያልሰጠውን ሰንደቅ ዓላማውን እንዲናፍቅ፣ እንዲያፈቅር አደረገው፡፡ ነጻነቱን ከሰንደቅ ዓላማው በሰላም መውለብለብ ጋር በማገናኘት የልብሱ፣ የቤቱና የባርኔጣው ማስጌጫ አደረጋት፡፡ እያንዳንዱ ሰው በእጁ፣ በዐንገቱ፣ በወገቡ አስሮ ፍቅሩን ገለጸ፡፡ የነጻነቱ ዋስትናም አድርጎ አሰባት፡፡ ገዛኸኝ ውቤ ይኽን ይበሉ እንጂ ከ፲፱፻፲፰ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በትምህርት ቤት መዝሙሮችና በተለያዩ አጋጣሚዎች በቀረቡ ግጥሞች ይገለጽ ነበር፡፡ ይኽንንም በጊዜው ይታተም ከመነበረው <u>ብርሃንና ሰላም</u> ጋዜጣ ማንበብ ይቻላል፡፡ ስለኾንም ሰንደቅ ዓላማን በመዝሙር ማንቆለጳጰስ ከኢጣሊያ ወረራ በፊት የነበረ ባህል ቀጣይ ተግባር ነው፡፡

ከታሪካዊ እውነታው በመነሣት በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. "የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የክብር ሰላምታ" መዝሙሮች የተደረሱበትን በትምህርት ቤቶች እንዲዘመሩ የተደረገበትን ምክንያት መናገር ይቻላል፡፡ ይኸውም፣ አንደኛ፣ የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን ከመውረሩ በፊት በትምህርት ቤት መዝሙሮች ለወጣቱ ትውልድ ሰንደቅ ዓላማው የነጻነት ተምሳሌት መኾኑን በመግለጽ ለሰንደቅ ዓላማው ተገቢውን ፍቅርና አክብሮት እንዲሰጥ ይደረግ የነበረውን የተለመደ ተግባር ለማስቀጠል ነው፡፡ ኹለተኛ፣ ዐርበኞች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ክብር ለማስመለስ ለዐምስት ዓመታት ከወራሪው የኢጣሊያ ጦር ጋር መዋጋታቸውንና የከፈሉትን መስዋዕትነት ለማክበርና ለመዘከር በተተኪው ትውልድም ሲታወስ እንዲኖር ለማድግ ነው፡፡ ሦስተኛ፣ በኢጣልያ ጦር የተሸነፉት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አገር ጥለው ወደ አውሮፓ በመሰደድ ያሳለፉትን የከፋ ሕይወትና የሀገራቸውን ነጻነት የመንግሥታቱ ማኅበር እንዲያስመልስላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ፣ እንዲኹም በሀገር ውስጥ የሚታገሉትን ዐርበኞች ማበረታታቸውን ለመዘከር ነው፡፡ አራተኛ፣ የኢትዮጵያን ነጻነት ለማስመለስ አባቶና እናቶች የከፈሉትን መስዋዕትነት ወጣቱ እንዲያውቅና የሀገሩን ሉዓላዊነት ከወራሪ የመጠበቅ ኃፊነት እንዳለበት እንዲገነዘብ ለማድረግ ነው፡፡

ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀል፣ ምሽት ደግሞ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመሩትን መዝሙሮች የደረሱት ዮፍታሔ ንጉሤ ናቸው (ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፬)፤ ሙሉጌታ (1964)፤ ሰይፉ (1987)፤ አስፋው (1991) እና ዮሐንስ (፪ሺህ፬))፡፡ እሸቴ ደግሞ የመዝሙሮቹን ዜማ ደርሰዋል (ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፬)፤ አስፋው፣ (1991))፡፡ ይኹን እንጂ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ መቼ አገልግሎት መስጠት እንደ ጀመሩ፣ ስለሚዘመሩበት ሥርዓት የተደነገገ ሕግ ማግኘት አልተቻለም፡፡

በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር ስለ ሰንደቅ ዓላማ ክብር በየዕለቱ ጠዋት ተማሪዎች ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት፣ ከሰዓት በኋላ ደግሞ የዕለቱ ትምህርት እንዳበቃ በሰንደቅ ዓላማው አካባቢ ተሰባስበው ተማሪዎች የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮችን ይዘምሩ ነበር፡፡ አስፋው ተፈራ አክለውም የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ ሲዘመሩ የነበረውን ሥርዓት (1991፤ 27) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> ዓላማውን ለመስቀል ከሚያድርበት ስፍራ ወደ ሰንደቁ ይዘው የሚመጡት በጠባያቸው ምስጉን፣ በትምህርታቸው መልካም የሆኑ ሦስት ተማሪዎች ይሆናሉ፡፡ ከሦስቱ አንዱ በደንብ የታጠፈውን ዓላማ ግራ ክንዱን አጠፍ አድርጎ በሥነ ሥርዓት ይዞ፣ ሁለቱ ጓደኞቹ ግራና ቀኝ አጅበውት በንቃት ወደ ሰንደቁ ሲሄድ የፊሽካ ድምጽ ይሰማል፡፡ ለመዝሙሩም ዝግጅት የፊሽካ ድምጽ ሲሰማ በአካባቢው የሚገኘው ሰው ሁሉ በተጠንቀቅ ይቆማል፡፡ እንደኢጋጥሚ ባርኔጣ ወይም ቆብ የደፉም ካሉ በራሳቸው ላይ ያለውን ያወርዳሉ፡፡ መዝሙሩ ሲዘመር የዘገዩ ተማሪዎችና ከሰልፉ ውጭ ያሉ ሰዎች በያሉበት ቀጥ ብለው እስከ መዝሙሩ ፍጻሜ ይቆማሉ፡፡ በተመሳሳይ ሥርዓት ከትምህርት በኋላም የሰንደቅ ዓላማው መዝሙር ከተዘመረ በኋላ ሦስቱ ምርጥ ተማሪዎች ሰንደቅ ዓላማውን ወደ ማደሪያ ስፍራው ወስደው በክብር ያስቀምጣሉ፡፡
>
> ቅዳሜና እሁድ፤ እንዲሁም ትምህርት በሌለበት ጊዜ የየዕለቱ ተረኞች (ዘበኞች) ጠዋት በ12 ሰዓት ሰንደቅ ዓላማውን ያወጣሉ፣ ማታም በ12 ሰዓት ሰንደቅ ዓላማውን አውርደው በክብር ስፍራው ማስቀመጥ ኃላፊነታቸው ይሆናል፡፡ በፖሊስና በጦር ክፍሎች የተለየ የክብር ሥነ ሥርዓት አለ፡፡ በተለይም በጥሩንባ መታጀቡና ሌላም፡፡
>
> የሰንደቅ ዓላማው ግጥምና ዜማው ባልታወቀበት ስፍራ ዓላማው (ምልክቱ) ሲወጣና ሲወርድ ከላይ በተገለጸው ስነሥርዓት መሠረት የሰንደቅ ዓላማው ክብር "በኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር" ይከናወናል፡፡

ከዚኽ በላይ እንደተገለጸው ጠዋት የኢትዮጵያን የሰንደቅ ዓላማለ መስቀል፣ ማታ ደግሞ ለማውረድ ዝግጅት መደረጉን የሚገልጸው የፊሽካ ድምጽ ሲሰማ ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ ሰዎችም ባሉበት ይቆማሉ፡፡ ለሰንደቅ ዓላማው ያላቸውን አክብሮት ለመግለጽም ባርኔጣቸውን፣ ወይም ቆባቸውን ከራሳቸው ያወርዳሉ፡፡ ተማሪዎችና በቅርብ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ለሰንደቅ

ዓላማው ተገቢውን ክብር እንዲሰጥ መደረጉ[9] ብሔራዊ ስሜትን ለማጎልበት ይረዳል፡፡ ሰንደቅ ዓላማውን ለመስቀልም፣ ለማውረድም በሚዘመሩት መዝሙሮች አማካይነት ወጣቱ ትውልድ ንጉሡን፣ ዐርበኞችንና ሰንደቅ ዓላማውን እንዲያከብር ለማድረግ ጥረት መደረጉን እንገነዘባለን፡፡

የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የማይታወቁባቸው ቦታዎች እንደ ነበሩ በአስፋው (1991) ከተገለጸው አገልግሎታቸው ሀገር አቀፍ እንዳልነበር እንገነዘባለን፡፡ ይኹን እንጂ፣ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮችም ብሔራዊ መዝሙሩም በኹሉም ቦታ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እንዲዘመሩ ትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፬) ባሳተመው መጽሐፍ ግጥሞቹንና የሙዚቃ ምልክቶቹን አሳትሟል፡፡

በፖሊስና በጦር ክፍሎች የተለየ የክብር ሥነ ሥርዓት የሚደረገው ዘወትር ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀልና ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ ስለመፈጸሙ ማስረጃ የለም፡፡ እንደዚሁም በሌሎች የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በየቀኑ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማው ሲሰቀል፣ ምሽት ደግሞ ሲወርድ በምን ዓይነት ሥነ ሥርዓት እንደ ነበር አይታወቅም፡፡

ሙሉጌታ (1964)፣ ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፬) እና ሠይፉ (1987) የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ ኹለት መኾናቸውንና ሰንደቅ ዓላማው ሲወጣ የሚዘመረው፣ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ ከሚዘመረው የተለየ መኾኑን ገልጸዋል፡፡ ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፬)፣ ሙሉጌታ (1964) እና አስፋው (1991) ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የሚዘመረው መዝሙር "ደሙን ያፈሰሰ"፣ ምሽት በ፲፪ ሰዓት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመረው መዝሙር ደግሞ "ተጣማጅ አርበኛ" የሚሉ ርእሶች እንዳሏቸውም ገልጸዋል፡፡ "ደሙን ያፈሰሰ" የሚለው ርእስ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የሚዘመረው መዝሙር የመጀመሪያው ሥንኝ የመጀመሪያ ሐረግ ነው፡፡ በተመሳሳይ "ተጣማጅ አርበኛ" የሚለው ርእስም ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመረው መዝሙር የመጀመሪያ ሥንኝ የመጀመሪያ ሐረግ ነው፡፡

ሰይፉ (1987፤ 243) በበኩላቸው "ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ" ለሚዘመረው "ተጣማጅ ዐርበኛ"፣ "ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ" ለሚዘመረው ደግሞ "ደሙን ያፈሰሰ" የሚሉ መኾናቸውን ገልጸዋል፡፡ በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ በርእስነት ከተመለከቱት ሥር የተመዘገቡት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች በርእሶቹ ከተገለጸው ጊዜ በተቃራኒ የሚዘመሩ ናቸው፡፡ ሰይፉ የገለጹት በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፬)፣ በሙሉጌታ (1964) እና በአስፋው (1991) ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣና ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ እንደሚዘመሩ ከየግጥሞቹ በላይ በቅንፍ ከተገለጸው ርዕስ ተቃራኒ ነው፡፡ ቀድሞ "ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ"፣ ቀጥሎ ደግሞ "ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ" የሚለውን መጥራት የመዝሙሮቹን አገልግሎት አሰጣጥ ቅደም ተከተል የጠበቀ አይደለም፡፡ ቀድሞ መጠራት የነበረበት "ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ" የሚለው ነበር፡፡ ሰይፉ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹን ከመዘገቡ ወይም ስለሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ ከተናገሩ የተለያዩ ጸሐፊዎች በተለየ

---

[9]ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀል፣ ወይም ሲወርድ "በአካባቢው የሚገኙ ትንንሽ ልጆች ኳስ ቢጫወቱም እንኳ ሽማግሌዎች "እናንተ፣ ወድቃ የተነሣች ባንዲራ ናት'ኮ፤ ትጫወታላችሁ?" እያሉ ሲገስጹ በተደጋጋሚ ሰምቻለኹ፡፡" (ሺፈራው በቀለ፣ ይኽንን ጽሑፍ አንብበው ያከሉት መረጃ ነው)፡፡

ለውጥ አለመደረጉን የመዘገቡበትን ምክንያት ለመረዳት አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም፣ "ገናናው ክብራችን፣ ሰንደቅ ዓላማችን" የሚለውን ሥንኝ ኹለት ሐረጎች እያንዳንዳቸውን እንደ ሥንኝ ቆጥረው እንደሚከተለው መዝግበዋል፡፡

ገናናው ክብራችን፣
ሰንደቅ ዓላማችን፣
ያኰራሻል አርበኝነታችን፡፡

ይኽ ዓይነቱ አከፋፈልና አመዘጋገብ የተስተዋለው በእሳቸው ብቻ ነው፡፡

ጠዋትና ማታ የሚዘመሩትን መዝሙሮች ሳይነጣጠሉ አንድ ላይ አከታትለው "የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር" በሚል ርዕስ የመዘገቡም አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ዮሐንስ (፪፻ህ፬፤ ፪፻፴፫) ከትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር ያገኟቸውን የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች አከታትለው መዝግበዋል፡፡ በመጀመሪያ የጻፉት "ደሙን ያፈሰሰ" በሚል ሐረግ የሚጀምረውን ሲኾን "ተጠማጅ አርበኛ" በሚል የሚጀምረውን ደግሞ ቀጥለው ጽፈዋል፡፡

በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር በ፲፱፻፰፬ ዓ. ም. ባሳተመው መጽሐፍ የተመዘገቡት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች በዚኽ ጽሑፍ በተጠቀሱት ሌሎች ጸሐፍት ከተመዘገቡት መጠነኛ ልዩነት ይስተዋልባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ሙሉጌታ (1964፤ 70) የመዘገቧቸው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች የመጨረሻዎቹ ተመሳሳይ ሥንኞች[10] ፡-

[10]ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመሩትን መዝሙሮች የመጨረሻ ሥንኞች፣ ሙሉጌታ (1964) "ዐርኬ" ሲሏቸው፣ ዮሐንስ አድማሱ ደግሞ "አዝማች" ብለዋቸዋል፡፡ ዐርኬ ለሚለው ቃል በዮሐንስ (፪፻ህ፬፤ ፫፻፲፫) "በግጥም በቅኔ ሥልት፣ ግጥሞች፣ በተለይ ረዘም ሲሉና የያዙትን ጭብጥ እየዘረዘሩ "እየተረጎሙ" ሲሆኑ፤ እያንዳንዱን ሐሳብ በተለያዩ አንጓዎች ያዋቅሩታል፡፡..." በማለት ቃሉ ለሚገልጸው እሳቤ የተሰጠውን "መፍትሔ" ከተቀበልን የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ ረጅም አይደሉም፤ የሚገልጹትም የሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ ብቻ ነው፤ የሚዘረዘር ወይም የሚተረጎም የተለያየ ሐሳብ አልቀረበባቸውም፡፡ ስለኾነም ጸሐፊው የመጨረሻዎቹ ሥንኞች "ዐርኬ ናቸው" በማለት የሰጡት ስም ከተግባሩ አንጻር ሲመረመር ትክክል ነው ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

ዮሐንስ አድማሱ (፪፻ህ፬) በበኩላቸው የኹለቱን የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ተመሳሳይ የመጨረሻ ኹለት ስንኞች አዝማች ብለዋቸዋል፡፡ "አዝማች (refrain) በተወሰነና በሚገመት መዋቅራዊ ስፍራ ተመላልሶ እየመጣ ራሱን የሚደግም ስንኝ ወይም መንቶ" ነው የሚለውን የብርሃኑ ገበየሁ (1999፤ 411) ብያኔ ከተቀበልን ዮሐንስ አድማሱ (፪፻ህ፬) በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ ያሉትን ማለት እንዳልኾነ እንረዳለን፡፡ እሳቸው "አዝማች" ያሉበት ምክንያት ከትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር ያገኟቸውን (ምን ሥራ ውስጥ እንደኾነ አልገለጹም) የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ሲመዘግቡ "የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር" በሚል ርእስ አንድ መዝሙር አድርገው መመዝገባቸዋል፡፡ "የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር" የሚለው ርእስ አንድ እንጂ ኹለት መዝሙሮች መኾናቸውን አለመግለጹ የመጀመሪያው ስህተት ነው፡፡ ጠዋት የሚዘመረውንና ምሽት ከሚዘመረው ሳይለዩ አንድ ላይ አከታትለው መመዝገባቸው ሰንደቅ ዓለማ ሲወጣ የሚዘመረው መዝሙር የመጨረሻ ሥንኞች ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ በሚዘመረው መዝሙር መጨረሻ ላይ መደገማቸው እንደ አዝማች ለመቁጠር ምክንያት ኾነ፡፡ ይኽም ኹለተኛው አሳሳች ምክንያት ነው፡፡ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፰፬፤ ፲፩) በተዘጋጀው መጽሐፍ (እሳቸው ያልተመለከቱት አይመስልም) ጠዋት የሚዘመረውን "ሲወጣ የሚዘመር"፣ ምሽት የሚዘመረውን ደግሞ "ሲወርድ የሚዘመር" በማለት ለያይቶ መዝግቧቸዋል፡፡ ይኽም መዝሙሮቹ የሚዘመሩበት ጊዜ የተለያየ መኾኑን፣ አንድ ላይ የማይቀርቡና የተለያዩ መኾናቸውን ያስረዳል፡፡ እንደ አዝማች የተቆጠሩት ኹለት ሥንኞች የተለያዩ መዝሙሮች የመጨረሻ ሥንኞች እንጂ

ገናናው ክብራችን ሰንደቅ ዓላማችን፣
ያኰራሻል አርበኝነታችን፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡ ይኹን እንጂ፣ ሙሉጌታ (1964፤ 70) በግርጌ ማሳታዎሻ ቁጥር 40 እንደገለጹት ከላይ የተጠቀሱት ሥንኞች ከ፲፱፻፴፮ ዓ. ም. ጀምሮ ከዚኽ በታች በተጠቀሱት ሥንኞች ተተኩ፡፡

ሰንደቅ ዓላማችን ክብራችን ውዲቱ፣
ያኰራሻል ንጉሠ ነገሥቱ፡፡

ዮሐንስም (፪ሺህ፬) የመጨረሻዎቹ ሥንኞች በተጠቀሱት ሥንኞች መተካታቸውን፣ መቼ እንደ ተለወጡ፣ "ለጊዜው ማን እንደለወጣቸው" አለመታወቁንና ዮፍታሔ ግን፣ አለመኾናቸውን በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 503 ገልጸዋል፡፡ ሙሉጌታም፣ ዮሐንስም ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመሩት መዝሙሮች የመጨረሻዎቹ ኹለት ሥንኞች ከጊዜ በኋላ በጠቀሷቸው ሥንኞች መተካታቸውን ገልጸዋል፡፡ ሥንኞቹ የኢትዮጵያውያንን ክብርና ነጻነት የሚገለጽበትን ሰንደቅ ዓላማ የሚያስከብሩ፣ የሚያኰሩ ንጉሠ ነገሥቱ መኾናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ኹለቱም ተመራማሪዎች መዝሙሮቹ ሳይለወጡ ተመዝግበው ያገኙበትን/ባቸውን ምንጭ/ጮች አልጠቀሱም ወይም አልገለጹም፡፡ ይኹን እንጂ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፹፬) ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመረው መዝሙር የመጨረሻ ሥንኞች በሌላ አለመተካታቸውን፣ ወይም አለመለወጣቸውን ያስነብባል፡፡ በአስፋው (1991) የተመዘገበው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ስንኞችም በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ከተመዘገበው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር የተመዘገበውና ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመረው መዝሙር የመጨረሻ ሥንኞች ሙሉጌታም፣ ዮሐንስም እንደሚሉት የንጉሠ ነገሥቱን ሚና በሚገልጹ ስንኞች አልተተኩም፡፡ ከዚኽም የተለወጡት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የሚዘመረው መዝሙር የመጨረሻዎቹ ሥንኞች እንጂ፣ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመረው መዝሙር የመጨረሻ ሥንኞች አልተለወጡም ሰይፉ (1987) በበኩላቸው ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ምሽት ደግሞ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመሩት መዝሙሮች ርእሶች ቢለዋወጡም የመጨረሻዎች ሥንኞች ተመሳሳይ መኾናቸውን መዝግበዋል፡፡

ከዚኽ ላይ በአጭሩ ለመመልከት የተሞከረው የሰንደቅ ዓላማና የመዝሙርን ጥምረት፣ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮችን አገልግሎትና መዝሙሮቹን በመዘገቡ ወይም የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹን በሥራቸው ውስጥ በጠቀሱ፣ ወይም ስለሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ሐተታ ባቀረቡ ሰዎች መካከል ልዩነት ተስተውሏል፡፡ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ማስከበር የዐርበኞች ሚና እንደኾነ ይገልጹ የነበሩት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የመጨረሻ ኹለት ሥንኞች የንጉሠ ነገሥቱ እንደኾነ በሚገልጹ ሥንኞች መተካታቸውን የገለጹ እንዳሉት ኹሉ እንዳልተለወጡ የሚገልጹም አሉ፡፡ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፹፬) የታተመው የትምህርት ቤት መዝሙር ጠዋት ሰንደቅ ዓለማ ሲወጣ የሚዘመረው መዝሙር የመጨረሻዎቹ ኹለት ሥንኞች ሰንደቅ ዓላማውን

---

በአንድ መዝሙር ተደጋግመው የሚመጡ ስንኞች አይደሉም፡፡ ስለኾነም ሥንኞቹ "አዝማች" ተብለው መጠራታቸው ትክክል አይደለም፡፡

የማስከበርና የማኩራት ሚና የንጉሡ ነገሥቱ መኾኑን ይገልጻሉ፡፡ ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ ይዘመር የነበረው መዝሙር የመጨረሻዎቹ ኹለት ስንኞች ደግሞ ሰንደቅ ዓላማ የማስከበርና የማኩራት ሚና የዐርበኞች መኾኑን ይገልጻሉ፡፡

በንዑስ ርእሱ ከዚኽ በላይ ከተነሣው ሐሳብ ጋር ግንኙነት ያለውን ጉዳይ በማንሣት እናጠቃልላለን፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር በ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. ተደርሶ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት መዘመር ጀመረ (መርስዔ ኀዘን፣ ፲፱፻፺፱)፡፡ ከ፲፱፻፳ ዓ. ም. ጀምሮም የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ኾኖ እንደአገለገለ በየቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት (፲፱፻፳፰) ተገልጿል፡፡ ይኹን እንጂ ብሔራዊ መዝሙሩ የሚዘመርበት ጊዜና ቦታ በሕግ ያልተወሰነ በመኾኑ ትምህርት ቤቶች ለክረምቱ እረፍት ሲዘጉ፣ ወይም በውጭ እንግዳ ሲጎበኙ፣ ወይም የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ ሀገር ሰው ጋር የሥራ ግንኙነት ሲያደርግ ወዘተርፈ ይዘመራል፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ማርሽ ተፈሪ የብሔራዊ መዝሙሩን ሚና ተክቶ ይዘመራል፡፡ በየትምህርት ቤቶቹ በሚከበር በዓልና በንጉሡ የልደት በዓል ላይ ሌሎች መዝሙሮችም ይዘመሩ ነበር፡፡ ኾኖም፣ የብሔራዊ መዝሙሩ አገልግሎት በሕግ ሳይመራ ኢትዮጵያ በኢጣልያ ተወረረች፡፡ ከዐምስት ዓመታት በኋላ ኢትዮጵያ ከጠላት ነጻ ስትወጣ ንጉሠ ነገሥቱ በቤተ መንግሥታቸው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቅሉ ብሔራዊ መዝሙሩ አለመዘመሩን ከከበደ ተሰማ (፲፱፻፳፪) መጽሐፍ እንረዳለን፡፡ በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. "የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የክብር ሰላምታ መዝሙር" ሲደረስ አገልግሎቱ በሕግ የተደነገገና በሕዝብ ዘንድ የተለመደ ብሔራዊ መዝሙር አልነበረም፡፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሩ ከተደረሰ በኋላም ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ምሽት ደግሞ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ መዘመሩ ብሔራዊ መዝሙሩ ከሚሰጠው አገልግሎት ያመሳስለዋል፡፡ ይኹን እንጂ የሰንደቅ ዓላማው መዝሙር በተጠቀሰው ተግባር ብቻ የተገደበ ሲኾን፣ ብሔራዊ መዝሙሩ ግን በተለያዩ ብሔራዊ ጉዳዮችም ላይ ይዘመር ነበር፡፡ ቀጥለን የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የሚያንጸባርቋቸውን ታሪካዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እንመረምራለን ፡፡

### 3) በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የተዘመሩ ሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ትንተና

በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች የተንጸባረቁትን ጉዳዮች ለመመርመር፣ ለመተንተንና ለመተርጎም ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ በሚዘመረው መዝሙር እንጀምራለን፡፡ በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፬፤ ፲፭) በተዘጋጀው መጽሐፍ እንደሚከተሉ ተመዝግቦ እናገኘዋለን፡፡

ደሙን ያፈሰሰ፣ ልቡ የነደደ፣
በአርበኝነት ታጥቆ፣ ጠላት ያስወገደ፣
ንጉሡን[11]፣ አገሩን፣ ክብሩን የወደደ፣

[11]በአስፋው (1991፤ 26) በተመዘገው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር "ንጉሥ" የሚለው ቃል "መሪ" በሚል ቃል ተተክቶ ሥንኙ "መሪውን፣ አገሩን፣ ክብሩን የወደደ" በሚል ይነበባል፡፡ ይኽ ለውጥ በእሳቸው በተመዘገበው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ላይ ብቻ የተስተዋለ ነው፡፡ ቃሉ መቼና ለምን እንደተለወጠ ማወቅ ግን አልተቻለም፡፡ ለውጡ ንጉሥ የሚለውን መጠሪያ በሚጠሉ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ተፅዕኖ የመጣ ሊኾን ይችላል፡፡ "ንጉሥ" የሚለው ቃል "መሪ" በሚል መተካቱም የመዝሙሩን አገልግሎት ለማስቀጠል ለሚፈልጉ ሰዎች መልካም አማራጭ ሊኾን ይችል ነበር፡፡

ነጻነቱን ይዞ መልካም ተራመደ፡፡
ሰንደቅ ዓላማችን፣ ክብራችን ውዲቱ፣
ያኰራሻል፣ ንጉሠ ነገሥቱ፡፡

የዚኽ ሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ዋና ትኩረት ዐርበኞች የኢትዮጵያን ነጻነትና ሉዓላዊነት ለማስከር ባደረጉት ተጋድሎ፣ በከፈሉት መሥዋዕትነትና ባገኙት ድል ላይ ነው፡፡ ከ፲፱፻፳፰ እስከ ፲፱፻፴፫/፬[12] ዓ. ም. ዐርበኞች ኢትዮጵያን ወርሮ ከነበረው የኢጣልያ ጦር ጋር ከፍተኛ ተጋድሎ አካኺደዋል፡፡ ተጋድሏቸውም፣ በመዝሙሩ ዐርበኛ፣ ንጉሥ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ነጻነት፣ ጠላት፣ ሀገርና ክብር በሚሉት ቃላት ተገልጿል፡፡ ቃላቱ በጊዜው የተከናወኑ ድርጊቶችን እንደሚገልጹ ታሪካዊ ዐውዱን መሠረት በማድረግ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን ወርሮ፣ በኢትዮጵያውያን ላይ የጭካኔ ድርጊትና የሰብአዊ መብት ጥሰት መፈጸሙ ያበሳጫቸውና የግፍ ሥራው ያስቆጣቸው ኢትዮጵያውያን ደማቸውን ለማፍሰስ፣ አጥንታቸውን ለመከስከስ፣ ሕይወታቸውን ለመስጠት ጠላታቸውን ወግተውና ድል አድርገው ለማስወጣት ለዐርበኝነት ተነሣሡ፡፡ የነጻነት ምልክት የኾነውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አውርዶ የራሱን መስቀሉ፣ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በማዋረዱና ማንሳቆሉ ተቆጨ፤ ተናደዱ፤ መሥዋዕትነት ለመክፈል ተዘጋጁ፡፡ ለሀገራቸው፣ ለወገናቸው ክብርና ነጻነት ሲሉ በሀገር ወዳድነት ወራሪ ከኾነው የኢጣልያ ጦር ጋር ባላቸው የጦር መሣሪያና አቅም ትግል ጀመሩ፡፡ የትጥቅ፣ የስንቅና የሰለጠነ ሰራዊት ብልጫ የነበረው የኢጣልያ ቅኝ ገዢ ጦር የሚያደርስባቸውን ጥቃት ተጋፈጡ፡፡ የሀገራቸውን ነጻነት ለማስመለስ፣ ሰንደቅ ዓላማቸውን ለማስከበር በአጠቃላይ ዓላማቸውን ለማሳካት መሥዋዕትነት ከፈሉ፤ ከፍተኛ ተጋድሎም አደረጉ፡፡ ዐርበኞች የኢጣልያንን ጦር ከኢትዮጵያ ለማስወጣት ለዐምስት ዓመታትና ከዚያም በላይ ባደረጉት ትንቅንቅና ከእንግሊዝ ጦር ባገኙት ድጋፍ ድል አደረጉ፡፡ ነጻነትን አስመለሱ፣ አስከበሩ፡፡ ሰንደቅ ዓላማው በክብር ክፍ ብሎ እንዲውለበለብ ለማድረግ ቻሉ፡፡ የመዝሙሩ የመጀመሪያዎቹ ሥንኞች የሚገልጹትም ይኸንኑ ነጻነትን የተጋፋ፣ ሉዓላዊነትን ያሳጣ፣ ክብርን ያዋረደ፣ ንጉሥን ያሰደደ ወራሪ ኀይልን፣ ወይም ጠላትን ዐርበኞች ደማቸውን አፍስሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው ማባረራቸውን ነው፡፡

ይኸንን የዐርበኞች ተጋድሎ ንጉሠ ነገሥቱ ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ መሬት ገብተው ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ኦሜድላ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቅሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባሰሙት ንግግር፡- "...የኢትዮጵያ አርበኞች ሠይፋችሁን ሳትከቱ ሰንደቅ ዓላማችሁን ሳታጥፉ ለባዕድ አንገዛም በማለት በመሣሪያ ብዛት ከሚበልጣችሁ ጨካኝ ጠላት የባኅርይ ጀግንነታችሁን መሣሪያ አድርጋችሁ ቀን ከሌት፤ በዱር በገደል ስትጋደሉ ጠብቃችሁን፤ ይኸው አሁን እንደምታዩት ለ፭ ዓመት ታግላችሁ የድካማችሁንና የመሥዋዕትነታችሁን ፍሬ ለማየት እንድትበቁ አደረጋችሁ፡፡"

---

[12]የኢጣሊያ ጦር ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ ክፍል የወጣበትን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ የገቡበት ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. በመቁጠር የዐርበኞች ተጋድሎ በዐምሥት ዓመታት የገደበ ነው ይላሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ኢጣሊያ ከጎንደር ተሸንፎ የወጣው ፲፱፻፴፬ ዓ. ም. ስለኾነ የጎንደር ዐርበኞች ከጠላት ጋር ተጋድሎ ያደረጉት ለስድስት ዓመታት ነው ብለው ያምናሉ (ጌታቸው ወረደ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 25 ቀን ፳፻፲፩፣ አዲስ አበባ)፡፡

(ከበደ፣ 2007፤ 345) በማለት ገልጸውታል፡፡ ከንግግራቸው መረዳት እንደሚቻለው ዐርበኞች ጠላትን የታገሉትና የወጉት፣ ለድልም የበቁት ዘመናዊ ሥልጠና ሳይኖራቸውና ኋላ ቀር ጦር መሣሪያ በመጠቀም ነው፡፡

ዐርበኞችን ለተጋድሎና ለመሥዋዕትነት ያነሣሣቸውና ነጻነትን ለመጎናጸፍ ያስቻላቸው ንጉሠ ነገሥታቸውን፣ ሀገራቸውንና ክብራቸውን በመውደዳቸው፣ በማፍቀራቸው መኾኑ በሚከተሉት የመዝሙሩ ሥንኞች ተገልጿል፡፡

ንጉሡን አገሩን ክብሩን የወደደ
ነጻነቱን ይዞ መልካም ተራመደ፡፡

በመጀመሪያው ስንኝ እንደተነገረው ዐርበኞችን ለዐርበኝነት ተግባር ያነሣሣቸው ከኹሉም በላይ ንጉሠ ነገሥቱን በመውደዳቸው ነው፡፡ ከነጻነት በኋላ በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሩ በዐርበኝነት ለመትጋት ከሀገር ይልቅ ንጉሡ እንደዋና ቁጭት ፈጣሪ ተደርጎ ለምን እንደ ተገለጸ የሚከተሉትን መላምቶች እንመልከት፡፡ ዐርበኞች ከኹሉም በላይ ለተጋድሎ የተነሣሡት ለንጉሠ ነገሥቱ ሲሉ ነው መባሉ፣ አንድም፣ የጠላት ጦር ንጉሠ ነገሥቱን ከሥልጣን ማስወገዱና ለስደት መዳረጉ ዐርበኞችን አስቆጭቷቸውና አበሳጭቷቸው ነው፡፡ ይኽም ንጉሡን ወደ ሥልጣናቸው መመለስ ከኹሉም ቅድሚያ የሚሰጠው የዐርበኝነት ተግባር ተደርጎ እንዲታመን አድርጓል፡፡ አንድም፣ “በንጉሥ አምላክ”፣ “በኀይለ ሥላሴ አምላክ” እያለ ፍትሕ፣ ርትእ ይጠይቅ የነበረው ሕዝብ በወራሪው የኢጣልያ ጦር በደል ይደርስበት የነበረው መሪ በማጣቱ ተደርጎ በመታኑ፣ “ንጉሡ በሥልጣን ቢኖሩ ኖሮ ሕዝብ ፍትሕ ርትዕ ያገኝ ነበር” ብሎ በማሰቡ ነው፡፡ ጠላት የፈለገውን የሚፈጽምበት ኹኔታ የተፈጠረው ንጉሥ፣ መሪ በማጣት ምክንያት የተፈጠረ በደል ተደርጎ በመቆጠሩ ነው፡፡ አንድም፣ የመዝሙሩ ደራሲ ዮፍታሔ ለንጉሠ ነገሥቱ ቅርበት፣ ፍቅርና አክብሮት ስለነበራቸው[13] ንጉሠ ነገሥቱ ለሀገራቸው ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ በመዝሙሩ መግለጽ በመፈለጋቸው ነው፡፡ አንድም፣ ንጉሠ ነገሥቱን ከኹሉም በላይ አድርጎ በማቅረብ መዝሙሩን በሚዘምሩት ወጣቶች ለንጉሠ ነገሥቱ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ እንዲኾንና እንዲወዷቸው ለመቀስቀስ ነው፡፡ አንድም፣ የጠላት ጦር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን መሪ ስለአሳጣቸው፣ ንጉሡ ሀገራቸውን ጥለው፣ የሚመሩትን ሕዝብ ትተው መሰደዳቸው ለሕዝባቸው ጉዳት ነው ተብሎ በመታመኑ ነው፡፡ ይኽንን እምነት ዘርዘር አድርገን እንመልከት፡፡

በሰንደቅ ዓላማው መዝሙር ንጉሥ ከሀገር ነጻነትና ከዐርበኞች ክብር ቀድሞ መጠራቱ በዘመኑ ስለንጉሥ ይነገር ወይም ይሰበክ ከነበረው እምነትና ለንጉሥ ይሰጥ ከነበረው ክብርና ኀላፊነት የመነጨ ይመስላል፡፡ በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፯፤ የኀይልና የክብር ምንጭ ንጉሥ) እንደተገለጸው "ንጉሥ በመቀባቱ ሕዝቡን ለመጠበቅ፣ ሥርዓትን ለማስፈጸም

[13]በንጉሡና በመዝሙሩ ደራሲ መካከል ቅርርብ እንደ ነበርም በስደት ላይ ኾነው ከንጉሡ ጋር የተለዋወጧቸው ደብዳቤዎች ማስረጃ ናቸው (ዮሐንስ፤ ፪ሺ፱)፡፡

ከእግዚአብሔር አደራ የተቀበለ አባት ነው::"ንጉሥ ከእግዚአብሔር በታች የኀይልና የክብር ምንጭ ነው ተብሎ ይታመንና ይሰበክ ነበር:: የንጉሥ ሥልጣን ከፈጣሪ የተሰጠ ተደርጎ በመታመኑ የሚቀናቀኑትን ኹሉ የእግዚአብሔርን ሥራ ተቃዋሚ አድርጎ ይቆጥራል፤ ጠላትም ይላቸዋል:: በላያቸው ላይም ጥቃትን ይፈጽማል:: ድንበር ተሻግረው ሉዐላዊነቱን የሚቀናቀኑትንም እሳት ኾኖ ይጠብቃቸዋል፤ በስለትም ያጠቃቸዋል:: ንጉሥ ይተክላል፣ ንጉሥ ይነቅላል ተብሎም ይታመናል::ንጉሥ "...ያገር አውራ፣ የሕዝብ እረኛ፣ መሪና አሳዳሪ፣ ለወዳጁ ሹመት፣ ሽልማት፣ ለጠላቱ እሳት፣ ስለት የሚሰጥ..." ተደርጎ ይቆጠራል (ደስታ፣ ፲፱፻፳፪፤ ፯፻፴፱):: በሕዝቡ ዘንድ ንጉሥ ፍትሕንና ርትዕን በሚመራው ሕዝብ ዘንድ ለማስፈን ሥልጣን ያለው ተደርጎ ለመታመኑ፣ ለነጻነት ጠበቃ፣ አለኝታ ተደርጎ ለመቆጠሩ "ንጉሥ ቢሞቱ፣ በማን ይሟገቱ" የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር ተጨማሪ ማስረጃ ነው:: ስለኾነም፣ ዐርበኞች መሥዋዕትነት የከፈሉት፣ ከኹሉም በላይ ንጉሡ በዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው ፍርድ ጎደለ፣ ድኻ ተበደለ ማለት ባለመቻላቸው ነው::

ይኹን እንጂ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. የኢጣልያን ወረራ ለመመከት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በታወጀው የክተት ጥሪም፣ በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንግግርም ዐርበኞች ሀገርን እንዲያስቀድሙ የሚቀሰቅሱ ናቸው:: መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በጸሓፊ ትእዛዝ ኀይሌ ወልደ ሩፌ የክተት ዐዋጁ ቃል በነጋሪት ሲነገር ንጉሡ ነገሥቱ ቀድመው አልተጠሩም:: ይኽን በተመለከተ ማኅተመ ሥላሴ (፲፱፻፳፪፤ ፩፻፸፪ ፩፻፸፫) የመዘገቡትን ቀጥለን እንመለከታለን::

> ...ከ፫ ሺሕ ዘመን ይበልጥ በነጻነት የኖረችውን በጥንታዊነቷ የታወቀችውን ሽማግሌዋን አገራችንን ነጻነቷን አጥፍቼ እወስዳለሁ በማለት ስለ ተመኘ፤ ለመጠቃት በመታሰባችን እጅግ አዝኛለሁና ያገሬ የኢትዮጵያ ሰው ጉልበት ያለህ በጉልበትኽ ጉልበት የሌለኽ በሐዘንኽ ርዳኝ:: በጉልበትም በሐዘንም የምትረዳበት ምክንያቱ ለሃይማኖትኽና ለነጻነትኽ፤ እንደ አባትና እንደ ልጅ እየተሳሰበ ሲረዳዳ ለኖረው ለንጉሠ ነገሥትኽ ኵርቶ ነጻነቱን ለሚያሳየው ባንዲራኽ ስትል ነው::
>
> ነጻነትም የሌለው ሕዝብ በጠላት እጅ እንደ ከብት እየተነዳ ካገሩ የሚሰደድ በገዛ ምድሩ ርስቱን በሌላ የሰው እጅ እያየ ጨሰኛ ሆኖ በውርደትና በመረረ ሐዘን የሚኖር በከብቱና በመቃብሩ መሬት እንኳ የማያዝበት፤ ለዘሩ የሚተላለፍ ባርነት ወርሶ የሚኖር ሕዝብ ማለት ነው:: ስለዚህ ስንኳን ሌላው ሰው ንጉሥም ጳጳስም ቢሞት ሰው ነውና ዘሩ ይተካበታል:: ያገሩ ነጻነት ሲጠፋ ግን ምትክ የሌለው ባርነቱም ከዘር ሲተላለፍ ከማይሞት ስም ጋራ የሚኖር የዘላለም እስር ነውና፣ ኢጣልያ ምንም በመሣሪያው ቢኰራ ሞት የጋራ መሆኑ የታወቀ ነው::

በዐዋጁ እንደተነገረው ነጻነት ለአንድ ሕዝብ ከፍተኛ ዋጋ ያለው መኾኑን ነው:: ነጻነት ከሰው ሕይወት እንደሚበልጥ ለማስረዳትም የንጉሥና የጳጳስ ሞት ሰው ሊተካበት እንደሚችል፣ ነጻነት ማጣት ግን የሚተካው እንደሌለ ተገልጿል:: በዐዋጁ ለሀገር መሞት ከንጉሠ ነገሥቱም ከምንም ነገር በላይ ነው ብሎ ይቀሰቅሳል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥትን በጉልበትም በሐዘንም

እንዲረዳ የተጠየቀው ሃይማኖቱን፣ ነጻነቱን፣ ንጉሠ ነገሥቱንና ባንዲራውን እንዲያስከብር ነው፡፡ እንዲከበሩ ከተባሉት ንጉሠ ነገሥቱ የተጠሩት በሦስተኛ ደረጃ ነው፡፡ በአራተኛ ደረጃ የተጠራው ባንዲራውም የኢትዮጵያ ሕዝብ የነጻነቱ፣ የክብሩ መለያ ትእምርት መኾኑን ልብ ይሏል፡፡

እንደዚሁም ጥቅምት ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. የጦር ሚኒስትሩ ክቡር ራስ ሙሉጌታ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ፊት ቀርበው ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ለመዝመት ሲሰናበቱ ጠላት ከንጉሡ ፊት ከመድረሱ በፊት ቀድመው ለመሞት ቃል ይገባሉ፡፡ የጦር ሚኒስትሩን ቃል መግባት ያዳመጡት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ቁመው በንባብ ባሰሙት ቃል "ላገርህ ነጻነትና ለኛ ለንጉሠ ነገሥትህ ክብር ደምህን ለማፍሰስ ቆርጠህ መነሣትህን ማየታችን ደስ የሚያሰኝ ነው፡፡" (ማኅተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፳፱፤ ፪፻፹፩) በማለት ስሜታቸውን ገልጸዋል፡፡ በዚኽ ንጉሠ ነገሥቱ በንባብ ባሰሙት ቃል የጦር ሚኒስትሩን ሲያመሰግኑ ለሀገር ነጻነት መሥዋዕት መኾንን ቀድመው መጥራታቸው በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሩ ንጉሠ ነገሥቱ ቀድመው በመጠራታቸው ከሚፈጠረው ግንዛቤ ይለያል፡፡

ንጉሠ ነገሥቱ ከስደት ተመልሰው ሚያዝያ ፳፯ የድል ቀን ኾኖ እንዲከበር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባሰሙት ንግግር ጀግኖች ኢትዮጵያውያን መሥዋዕትነት ለምን እንደ ከፈሉ ሲገልጹ የሀገርን ነጻነት አስቀድመዋል፡፡ ይኽን የተመለከተው ንግግራቸው "በዚህም ቀን ለሚወዷት ላገራቸው ነጻነት ለንጉሠ ነገሥታቸው ለሰንደቅ ዓላማቸው ክብር ከአባቶቻቸው የተላለፈውን ጥብቅ አደራ አናስወስድም በማለት መሥዋዕት ሆነው ደማቸውን ያፈሰሱትን አጥንታቸውን የከሰከሱትን ጀግኖቻችንን እናስታውሳለን፤ ለነዚህም ለጀግኖቻችን የኢትዮጵያ ታሪክ ምስክር ይሆናል፡፡" (ከበደ፣ 2007፤ 424) የሚል ነበር፡፡

አንዳንድ ሰዎችም ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ሲጽፉ ከዚኽ በላይ ከተመለከተው የተለየ አጠራር አልነበራቸውም፡፡ ኢትዮጵያውያን የኢጣልያን ጦር ለመመከት እንዲነሣሡ የሚቀሰቅሱ ጽሑፎችን ስለሚያቀርቡ ሰዎች ማኅተመ ሥላሴ (፲፱፻፳፱፤ ፪፻፺፪) ሲገልጹ "ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ በግፍ በተነሣችባት ጊዜ በሀገሩ በንጉሠ ነገሥቱና በነጻነቱ ፍቅር ልቡ የተነደፈ ሁሉ በየጊዜው ጥልቅ የሆነ ሐሳቡን በጋዜጣ ይጽፍ እንደነበረ እናውቃለን፡፡" ነበር ያሉት፡፡

ሰለሀገራቸው የመቆርቆራቸውና የመቆጨታቸው ምክንያቶች ቀደም ሲል የተገለጹት ፍትሕ ርትእ ካለማግኘት፣ ከሰብአዊ መብት ጥሰትና መሪ ከማጣት ከሚሉት የመነጩ ሊኾኑ ይችላሉ፡፡ ከኹሉም በላይ አንድም፣ በሥነ ቃል ለትውልድ የተላለፈን መልእክት ዐርበኞኞች በማወቃቸው ነው፡፡ አንድም፣ መንግሥት ስለሀገር ምንነት የተናገረውን ዐርበኞች በመገንዘባቸው ነው፡፡ በቃላዊ ግጥም ስለሀገር ከሚነገረው እንጀምር፡፡

እናት አባት ቢሞት፣ ባገር ይለቀሳል፣
እኅት ወንድም ቢሞት፣ ባገር ይለቀሳል፣
አክስት አጎት ቢሞት፣ ባገር ይለቀሳል፣

አገር የሞተ[14] እንደሁ፣ ወዴት ይደረሳል፡፡

በግጥሙ የተገለጹት የቤተሰብ አባላት (የእናት፣ የአባት፣ የእኅት፣ የወንድም፣ የአክስትና የአጎት) ሞት ከፍተኛ የኀዘን ስሜት ያስከትላል፡፡ ከተጠቀሱት የቤተሰብ አባላት አንዳቸው በሞት ቢለዩ የሚፈጠረው የኀዘን ስሜት ደረጃ የቤተሰብ አባላቱ በግጥሙ በተጠሩበት ቅድም ተከተል ሊኾን ይችላል፡፡ ይኹን እንጂ፣ በግጥሙ ከተቆጠሩት የቤተሰብ አባላት ሞት የበለጠና የከበደ ኀዘን ያስከትላል ተብሎ የሚታመነው የሀገር ሞት[15] ነው፡፡ በመኾኑም፣ የሉዓላዊነት መደፈር፣ የነጻነት መጥፋት፣ የሀር ውድቀት፣ ከኹሉም ነገር የከፋ ሞት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በሀገር ሰላም ከጠፋ፣ መሪና ተመሪ ከሌለ፣ ሕግና ሥርዓት ከጠፋ፣ ሀገር በሕግ ካልተመራ፣ ሕዝብ በሰላም ወጥቶ በሰላም መግባት ካልተቻለ ሀገር ሞተ ሊባል ይችላል፡፡

የሀገር ሞት ከኹሉም የከፋ ነው የተባለበትን ምክንያት በአንድ ወቅት ከተነገረ ዐዋጅ እንገነዘባለን፡፡ ሕዝቡ ስለሀገሩ ያለውን ጥልቅ ግንዛቤ የተረዱት ዐፄ ዮሐንስ ከደብረ-ታቦር ወደ ሰሐጢ ለመዝመት ሲነሡ ባወጁት ቃለ አዋዲ ሀገር ኹሉንም ማለት መኾኑ ተንጸባርቋል፡፡ "በ1880 ዓ. ም. የኢጣልያ ጦር ከምፅዋ ወደብ 35 ኪሎ ሜትር ርቀት ድረስ ገፍቶ መጥቶ ሰሐጢ ላይ መመሸጉ ሲታወቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመቻ እንዲከት ዐፄ ዮሐንስ የሚከተለውን የቅስቀሳ ዐዋጅ እንዲነገር አደረጉ፡፡

> የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ! ልብ አድርገህ ተመልከት፤ ኢትዮጵያ የተባለች፡-
> አንደኛ እናትህ ናት፣
> ኹለተኛ ዘውድህ ናት፣
> ሦስተኛም ሚስትህ ናት፣
> አራተኛም ልጅህ ናት፣
> ዐምሥተኛም መቃብርህ ናት፣

እንግዲህ የእናት[ን] ፍቅር፣ የዘውድ[ን] ክብር፣ የሚስት[ን] ደግነት፣ የልጅ[ን] ደስታ፣ የመቃብር[ን] ከባቲነት (ታቃፊነት) በመገንዘብ፣ እንደዚህ መሆኑን አውቀህ ተነሣ፡፡"[16] (ዘውዴ፣

[14] በዚኽ ግጥም ሀገር የሚለው እሳቤ በተባታይ ፆታ የተጠራበት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የአብዛኛዎቹ ክፍላተ ሀገር ነዋሪዎች ለአካባቢያቸው የሰጡትን ፆታ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወሎ፣ ሸዋ፣ ወለጋ፣ ባሌ. በተባታይ ፆታ ይጠራሉ፡፡ ትግራይ ግን በተወላጆቹ "አደይ ትግራይ" በማለት በአነስታይ ፆታ ትጠራለች፡፡ ከፍላተ ሀገሮች በተለያየ ፆታ የሚጠሩበትን ምክንያት ለማወቅ ምርምር ማድረግ ይጠይቃል፡፡ ኢትዮጵያ ስትጠቀስ ግን፣ በአንስታይ ፆታ፣ በእናትነት ነው፡፡ ግጥሙ ተባዕታይ ፆታን የተጠቀመው ዜማውን ለመጠበቅ ወይም በተባዕታይ ፆታ የሚጠራን ክፍለ ሀገር በማስብ ሊኾን ይችላል፡፡

[15] በግጥሙ የሀገር ሞት በብዙ መንገድ ሊከሰት ይችላል፡፡ የሀገር ሉዓላዊነት በጠላት ከተደፈረ፣ ነጻነት ከሌለ ሀገር ሞተ ማለት ነው፡፡ ሀገር ለነዋሪዎቹ የሚበላና የሚጠጣ መስጠት ካልቻለ፣ ርኻብ፣ ድርቅ በሀገር ከነገሠ፣ ሀገር ሞተ ይባላል፡፡ የሀገር ነጻነት ማለት ተራራው፣ ሸለቆው፣ ወንዙ፣ ሐይቁ ባጠቃላይ መሬቱ ማለት ብቻ አይደለም፡፡ ከተፈጥሮ የምናገኛቸው፣ ለእኛነታችን ከሚያሰፈልጉ ነገሮች ኹሉ ማለት እንጂ፡፡

[16] ዐዋጁ በዘመቻው ይሳተፋሉ ተብለው ለሚጠበቁ ወንዶች የተነገረ ነው፡፡ መልእክቱም ወንዶች ይወዷቸዋል፤ ያፈቅሯቸዋል የተባሉትን በመዘርዝር ለወንዶች ብቻ ጥሪ ያደርጋል፡፡ በዘመቻ ይሳተፉ የነበሩትን ሴቶችን ግምት ውስጥ አላስገባም፡፡ ምናልባትም በዘመቻ ወቅት የሴቶቹ ቁጥር ከወንዶች እኩል አለመመጣጠኑ ለወንዶች ብቻ ጥሪ እንዲደረግ ገፋፍቶ ይኾናል፡፡ ዘመቻውን የሚመሩትን የንጉሠ ንጉሥቱን፣ የመሳፍንቱን፣ የመኳንንቱንና የጦር አበጋዞቹን ምግብና መጠጥ የሚያዘጋጁትና የሚያቀርቡት ሴቶች ነበሩ፡፡ በተጨማሪም የጌቶቻቸውን ሰውነት

2007፤ 99) ዐዋጁ የተነገረው በዐዋጁ በተጠሩት የቤተሰብ አባላት ቅደም ተከተልና ልክ ኢትዮጵያን እንድንወድና እንድናፈቅር ለመቀስቀስ ነው።

በዐዋጁ ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ሊኖራቸው የሚገባውን ፍቅር ለማስረዳት ለዋጭ ዘይቤን ተጠቅመዋል። ኢትዮጵያን በለዋጭ ዘይቤ ከወከሉት ዐምስት ነገሮች ቀድሞ የተነገረው እናትነቷ ነው። ይኸም እናት ለአብራኳ ክፋይ ያላትን የስሜት ቅርበት በመግለጽ ከሀገር ጋር በማመሳሰል ብቻ አይደለም። እናት ከአጥንቷ አጥንት፣ ከደሟ ደም ሰጥታ ጽንሱን እንደምታፋፋው፣ ከጡቷ ወተት እንደምትመግበው፣ ከሰውነቷ ሙቀት እንደምትለግሰው ኹሉ፣ ሀገርም የሚበላውን አብቅላ ታበላለች፣ ታለብሳለች፤ ከሚፈሰው ወይም ከሚመነጨው ውሃ ታጠጣለች።

እናት ለአብራኳ ክፋይ ያላትን የስሜት ቅርበት በመግለጽ ከሀገር ጋር ማመሳሰል ብቻ አይደለም። እናት ለወለደችው ያላትን ደግነት፣ ሩኅሩኅነትና ሊጋስነት ሀገር ከምትሰጠው መልካም ነገር ጋር በማመሳሰል ለማስረዳት ነው። በዐዋጁ ቀድሞ ኢትዮጵያን “እናት ሀገር” ብሎ የመጥራት ምክንያት ከእናት ማኅጸን መወለድንና ለኢትዮጵያውያን መገኛ መኾኗን በመግለጽ በዐዋጁ ከተጠሩት በላይ ነች ብሎ ማመንን ማስረዳት ነው። ይኸንም ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፷፯፤ አገር) “እግዚአብሔር ከምድሯ ፍሬ ሕይወት እንዲገኝባት በማድረጉ አገር እያጠባች የምታሳድግ ፍቅር በአጥንት በሥጋ ገብቶ የማይደመሰስ የሆነች እናት ማለት ናት።” በማለት ያስተምር ከነበረው ጋር ይመሳሰላል። በዐዋጁ ኢትዮጵያ ቀድማ መጠራቷና በእናትነቷ ከንጉሥነትም፣ ከሥልጣንም፣ ከዘውድም በላይ ነች ማለት ነው።

በዐዋጁ እንደተነገረው ኢትዮጵያ ለዜጎቿ የነጋሢነት ማዕረግ ምልክት የኾነውን ዘውድ[17] ማለት ናት። ዐዋጁ በተነገረበት ታሪካዊ ዐውድ፣ በአማራውና በትግራዊው ባሕል ዘውድ ንግሥናን፣ በሥልጣን ቁንጮ ላይ መቀመጥንና ከኹሉ በላይ መኾንን ይገልጻል። ኢትዮጵያውያንን ለማገንዘብ በዐዋጁ የተነገረው ኢትዮጵያ በከበረ ማዕድን አጊጦ ከኹሉም በሚበልጠው የሥልጣን እርከን ላይ መቀመጥን ያኽል ናት የሚል ነው። ኢትዮጵያ ለዜጎቿ በሥልጣን እርከን ከኹሉም ከሚልጠው ንግሥና ጋር ተመስላ በዐዋጁ የቀረበችው በኹለተኛ ተራ ቁጥር ነው።

በዐዋጁ በሦስተኛ ተራ ቁጥር የተጠራችው ሚስት ናት። እሷም ከወንድ ጋር በሕጋዊ ጋብቻ ተጣምራ በትዳር ጓደኝነት በምትዘልቀው፣ በደግነቷ፣ በመልካም ምግባሯ፣ በቸርነቷ፣ በይሁን፣

---

የሚያሻሹትና አብረው በመተኛት ሙቀት የሚሰጡት ሴቶች ናቸው። ወታደሩን የሚቀሰቅሱትና የሚያጀግኑት ሴት አዝማሪዎች የዘመቻው ተሳታፊዎች ነበሩ። ለምሳሌ፣ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በተደረገው የክተት የዘመቻ ጥሪ “እንደ ጥንት ጊዜ ልማድ ሴቶችም ወታደሩን በማደፋፈር ቁስለኛ በማስታመም ላገራቸው ይከላከሉ።” (ማኅተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፷፪፤ ፪፻፷፮)

ከዚኽም በላይ መዋቅራዊ በኾነ ምክንያት ሴቶች ይዘምታሉ፤ ማለትም የዘመቻ መሬት (በበጌምድር በጎጃም)፣ የኦሮሞ መሬት (በወሎ)፣ የግንደበል መሬት (በሸዋ) የወረሰች ሴት ወይ እራሷ መዝመት አለባት፤ ወይ ወንድ (ባል፣ አሽከር፣ ወዘተ.) መተካት አለባት። “በእኔ አመለካከት፣ ዐዋጁ ለወንዶች ብቻ ጥሪ የሚያደርገው የኅበረተሰቡ አመለካከት “የወንድ ትምክህተኝነት” የሰፈነበት ስለነበረ ነው።” (ሺፈራው በቀለ በ2011 ዓ. ም. ይሕን ጽሑፍ አንብበው ያከሉትሐሳብ ነው።)

[17] ዘውድ እንደ አክሊል፣ እንደ ቆብ በራስ ላይ የሚደፋ፣ የሚጫን ጌጠኛ ዕቃ ነው። የሚሠራውም ለማጌጫነት ከሚፈለጉትና ከሚወደዱት የተለያዩ ማዕድናት በተለይም ከወርቅና ከአልማዝ ነው።

እሺ ባይነቷ በኢትዮጵያ ተመስላለች፡፡ ሚስት በባል አጣማጅነቷ ምኞትን፣ ድሎትን፣ አርካታን እንደምታስገኘው ኹሉ፣ ሀገርም በጠላት ካልተጠቃች ሚስት የምትሰጣቸውን መልካም ነገሮች ትሰጣለች ተብሎ መታመኑን ከአዋጁ መረዳት ይቻላል፡፡ መልካም ሚስት ለበሏ ከምትሰጠው ፍቅር፣ እንክብካቤና ኩራት ጋር ሀገር ተነጻጽራለች፡፡ "መልካም ሚስት ለባሏ ዘውድ ናት" የሚባለውም ለዚኽ ነው፡፡

ሀገር የምታስገኘው ደስታ ሴት ልጅ ለወላጅ ከምትሰጠው ደስታ እኩል መኾኑ በዐዋጁ ተገልጿል፡፡ በጋብቻ የተሳሰሩ ባልና ሚስት የትዳር ሕይወታቸው እንዲጸና፣ ቤታቸው በፍስሐና በደስታ እንዲደምቅ ልጅ ሊኖራቸው ይገባል ተብሎ ይታመናል፡፡[18] በዐዋጁ ሴት ልጅ ለአባቷ የምታስገኘው ደስታ ነጻ ሀገር ከምትሰጠው ደስታ ጋር መነጻጸሩ የተወሰነው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ክፍል ለሴት ልጅ የሚሰጠውን ከፍተኛ ቦታ ይገልጻል፡፡

ለነጻትና ለሉዓላዊነት መትጋት የሚያስፈልገው ሀገር ኖረው የሚደሰቱባት ብቻ ሳትኾን ሞተው የሚቀበሩባትም በመኾኗ ነው፡፡ "ዞሮ ዞሮ ከቤት፣ ኖሮ ኖሮ ከሞት" እንደሚባለው ሰው በሥጋ ሕይወት መኖሩ ሲያበቃ የሬሳው መኖሪያ ጉድጓድ፣ የአጽሙ ማረፊያ ቦታ እንዲኖረው ይሻል፡፡ ሰው ሥጋ ሞቱን ሲያስብ አፈር ተምሶ፣ ድንጋይ ተንተርሶ የሚቀበርበት የሚያሸልብበት ቦታ እንዳለው ሲረዳ በሕይወተ ሥጋ እያለ መልካም ስሜት ይሰማዋል፡፡ በባህላችን ሬሳ የሚቀብሩት እንጂ የትም የሚጥሉት አይደለም፡፡ ቀብሩ የሚፈጸመው ባገር መኾኑን ዐዋጁ ይገልጻል፡፡ በዐዋጁ የተገለጸው ሐሳብ በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፯፤ አገር) "አገር ማለት አያት ቅድም አያት የተወለዱበት አድገውም በጀግንነት ከውጪ ጠላት እየተከላከሉ ለሕዝብና ለመንግሥት የሚጠቅም ሥራ ሠርተው ዕድሜአቸው ሲደርስም ልጆቻቸውን ተክተው የተቀበሩበት ጉድጓድ ነው፡፡" በማለት ተገልጿል፡፡ ይኸም፣ ሀገር ማለት ኑረው የሚደሰቱበት፣ ሞተው የሚቀበሩበት ነው የሚለው ግንዛቤ ለትውልዱ የሚተላለፍ የሀገር ፍቅር መቀስቀሻ ሐሳብ ስለነበር በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሩም ተመሳሳይ ቁም ነገር ተነግሮበታል፡፡

ጠዋት በሚዘመረው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ዐርበኞች መሥዋዕትነት የከፈሉት፣ አጥንታቸውን የከሰከሱት፣ ደማቸውን ያፈሰሱት፣ የተራቡት፣ የተጠሙትና የታረዙት በተዋረድ ለንጉሠ ነገሥታቸው፣ ለሀገራቸውና ለራሳቸው ክብር ብለው ነው ማለትን ይገልጻል፡፡ በመዝሙሩ የዐርበኞች ክብር ከንጉሡ ሥልጣን ማጣትና ከሀገር ጥቃት የሚመጣ ተደርጎም ቀርቧል፡፡

ወራሪው የኢጣልያ ጦር በኢትዮጵያውያን ላይ ያደረሰውን የሰብአዊ መብት ጥሰት ለመከላከልና ለመመከት የዐርበኝነት ተግባር ለመፈጸም ዐርበኞችን ካነሣሧቸው ምክንያቶች አንዱና በሦስተኛ ደረጃ የተጠራው የራሳቸውን ክብር የማስጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡ በጊዜው በኢትዮጵያውያን ላይ

[18] ተዋደው ተዋደው ካልወለዱ ልጅ፣
 እንደመንገደኛ/እንደገበያተኛ ደህና ዋል ነው እንጅ፡፡
የሚለው ቃል ግጥም በጋብቻ ወይም በፍቅር የሚኖሩ ሰዎች ልጅ ወልደው ፍቅራቸውን ማጎልበት፣ ትዳራቸውን ማሞቅ፣ ዝምድናቸውን ማስፋት እንደሚፈልጉ ያስረዳል፤ይኽ ካልኾነ ደግሞ የሚወዱትን የሞቀ ትዳራቸውን መፍታት አለባቸው ማለት ነው፡፡

ይደርስ በነበረው የሰብአዊ መብት ጥሰት የሰብአዊ ክብር መደፈር ከፍተኛ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ለሰው ክብር ከማይሰጥና በትንንሽ ምክንያት ጥቃት ለማድረስ ከሚፈልግ ጠላት ራስን ለመከላከልና ለመጠበቅ፣ ነጻነታቸውን ለማስመለስ፣ የነጻነት ምልክት የኾነውን ሰንደቅ ዓላማ ለማስከበር ዐርበኞች የኢጣልያንን ጦር በደፈጣ ውጊያ በማጥቃት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፤ መሥዋዕትነትም ከፍለዋል፡፡ የዐርበኝነት ተግባር ለመፈጸም ዐርበኞችን ለውጊያ ያነሣሣው የራስ ክብር ነው፡፡የራስ ክብር የሚለው በስንኙ በመጨረሻ መጠራቱ ለራስ ክብር የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ነው ማለትን ይገልጻል፡፡

ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ በሚዘመረው መዝሙር "ያኰራሻል ንጉሥ ነገሥቱ" የሚለው ሥንኝ ኢትዮጵያን የማኩራትና ነጻነቷን የማስጠብቅ የሀገር ሉዓላዊነት መገለጫ የኾነችውን ትእምርት ወይም ሰንደቅ ዓላማ የማስከበር ኀላፊነት የንጉሠ ነገሥቱ መኾኑ መገለጹ ሰንደቅ ዓላማን በማክበር፣ ሉዓላዊነት በመጠበቅ የተሰጣቸውን ቦታ ያስረዳል፡፡ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበርና በማደራጀት ከውጭ የመጣን ጠላት የመከላከል፣ የሀገርን ነጻነት የመጠበቅና የማስጠበቅ ኀላፊነት ከማንም በላይ የንጉሠ ነገሥቱ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ይኸንን የሰንደቅ ዓላማው መዝሙር ከተጻፈበት የታሪክ ዐውድ አንጻር በመቃኘት በሥንኙ የተገለጸውን የታሪክ እውነታ መረዳት ይቻላል፡፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በትግራይ በኩል የኢጣልያ ጦር የከፈተውን ጥቃት የኢትዮጵያ ጦር ለመመከት በንጉሠ ነገሥቱ የበላይነት ተዘመተ፡፡[19] በጦርነቱ የኢጣልያ ጦር በማሸነፉ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡ ቤተሰቦቻቸውንና የሚቀርቧቸውን መሳፍንትና መኳንንት ይዘው ወደ ውጭ ሀገር ተሰደዱ፡፡ ሀገሪቱን ወርሮ የያዘውንና የግፍ ተግባር የሚፈጽመውን የኢጣልያን ወራሪ ጦር ድርጊት በስደት የነበሩት ንጉሠ ነገሥት መቃወማቸውን ቀጠሉ፡፡ የኢጣልያንን መንግሥት የወራሪነት ድርጊት እንዲያወግዝ ለመንግሥታቱ ማኅበር (ሊግ ኦቭ ኔሽንስ) ይከሱና አቤቱታ ያቀርቡ ነበር (ዘውዴ፣ 2005)፡፡ በሀገር ውስጥ ከነበሩት ዐርበኞች ጋር በደብዳቤና በሰው መልእክት እየተገናኙ ይመክሯቸውና ያበረታቷቸው ነበር (ዮሐንስ፣ ፪ሺ፱)፡፡

"ያኰራሻል ዐርበኝነታችን" የሚለውንና የኢትዮጵያውያንን ኀናነትና ክብር፤ የኢትዮጵያውያን ነጻነት የሚገለጽበትን ትእምርት፣ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ያኰሩትና የሚያኰሩት፣ ያስከበሩትና የሚያስከብሩት ዐርበኞች መኾናቸውን የሚገልጸውን በማሻሻል "ያኰራሻል፣ ንጉሠ ነገሥቱ" በሚል ሥንኝ መተካት በተራው ሕዝብ የተገነባው የዐርበኞች ኀይል የፈጸመውን የዐርበኝነት ተግባር ያሳንሳል፣ ያደበዝዛል፡፡ የዐርበኞች ተጋድሎ ከሕዝቡ አእምሮ ሳይደበዝዝ፣ ዐርበኞችም በሕይወተ ሥጋ እያሉ የኢትዮጵያን ነጻነት የማስከበር፣ ሰንደቅ ዓላማውን የማኩራት ተግባር የንጉሠ ነገሥቱ እንደኾነ መዝሙሩን ማሻሻል የንጉሠ ነገሥቱን የኹሉም ነገር ወሳኝነት የበላይነት ማጠናከሪያ ተደርጎ መታሰቡን ያስረዳል፡፡

ለማጠቃለል ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የሚዘመረው መዝሙር በኢትዮጵያ መወረር የተበሳጩ፣ የበገኑ፣ የበሸቁ፣ ዐርበኞች የወገናቸውን ክብርና ነጻነት ለማስከበር፣ በሀገር ወዳድነት ከኢጣልያ ወራሪ ጦር ጋር መዋጋታቸውን፣ ደማቸውን አፍስሰው ጠላታቸውን ማስወገዳቸውን፤

[19]ሌሎቹ ኹለት ጥቃቶች የመጡት በኦጋዴንና በሲዳሞ በኩል ነበር፡፡

ነጻነታቸውን ማስከበራቸውን፣ ክብራቸውን ማስመለሳቸውን ይገልጻል፡፡ በመዝሙሩ በተገለጸው ቅደም ተከተል መሠረት፣ ዐርበኞች የዐርበኝነት የውዴታ ግዴታቸውን የፈጸሙት ንጉሡን ወደ ሥልጣናቸው ለመመለስ፣ የመሪያቸውን የንጉሡን ሥልጣን ለማስከበር፣ የሀገራቸውን ሉዓላዊነትና ነጻነት እንዲሁም የራሳቸውንና የወገናቸውን ክብር ለማስመለስ በመሻት ነው፡፡ በዐርበኞቹ ተጋድሎ የተገኘውን ድል የመጠበቅና የማስቀጠል፣ የነጻነት ትእምረት የኾነውን ሰንደቅ ዓላማ የማስከበር ኀላፊነት የንጉሡ ነገሥቱ መኾኑን የመዝሙሩ የመጨረሻዎቹ ኹለት ሥንኞች ይገልጻሉ፡፡

ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ ይዘመር የነበረው መዝሙር የሚያንጸባርቀው ጉዳይ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ ከሚዘመረው ጋር መመሳሰል አለመመሳሰሉን እንመረምራለን፡፡ ምርምራችንም ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመረውንና በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፷፬፤ 11) የተመዘገበውን መዝሙር በመጥቀስ እንጀምራለን፡፡

ተጠማጅ[20] ዐርበኛ፣ ባገር መውደድ ቀንበር[21]፣

---

[20]ተጠማጅ የሚለው ቃል በሌሎች ሰዎች (ሙሉጌታ (1964)፣ ሰይፉ (1987)፣ አሰፋው (1991) እና ዮሐንስ (፪ሺ.ህ፬)) በተመዘገበው መዝሙር "ተጣማጅ" በሚል ቃል ተተክቷል፡፡ ተጣምጅ የሚለውም ጠመደ ከሚለው ግስ የወጣ ነው፡፡ ቃሉ በግብርና ሙያ ባለው አገልግሎቱ ኹለት ፍቺ አለው፡፡ አንደኛው የእርሻ ሥራ ለመሥራት ቀንበር የተጫነበት በሬ ማለት ነው፡፡ ተጣማጅ ያስባለውም ከሌላ በሬ ጋር በመቆራኘት ትከሻው ላይ የተጫነውን ቀንበር በመሸከም አብሮት ከተጠመደው በሬ ጋር በእኩል እርምጃ በመጎተት የእርሻ ሥራ የሚያከናውን መኾኑ ነው፡፡ ኹለት በሬዎች የሚሸከሙትን ከባድ ቀንበር በጋራ መሳባቸው የእርሻ ሥራን ለማከናወን ያስችላል፡፡ የተጣማጆቹን በሬዎች ኅብረት መልካም ውጤት እንደሚያስገኘው ኹሉም የዐርበኝነት ተግባር ለመፈጸም ሸፍተው በዱር በገደሉ ራሳቸውን ያስጠለሉ፣ በጠላት ሥር የነበሩትም ልቦናቸውን አሸፍተው የዐርበኞች አጋር የነበሩ ኢትዮጵያውያን ሀገርን የሚያኮራ በታሪክ የሚወሳ ተግባር የፈጸሙት ተባብረውና ተረዳድተው ነው፡፡

"ተጠማጅ" የሚው ቃል ግብሩን ፈጻሚው ከሌላ ጋር አለመቆራኘቱን፣ ራሱ የሚፈጽመውን ተግባር ይገልጻል፡፡ ይኸው የሆሄ አጠቃቀም ለውጥ የተስተዋለበት ቃል ዐርበኛ ከሚለው ቃል ጋር ተጣምሮ አንድ ሐረግ ኾኗል፡፡ "ተጠማጅ ዐርበኛ" የሚለው ሐረግ ዐርበኛው በራሱ ተነሳሽነትና ውሳኔ የዐርበኛነት ተግባር የፈጸመውን የታሪክ እውነታ ይገልጻል፡፡ የሆሄ አጠቃቀም ለውጡም የጎላ የፍቺ ልዩነት አላመጣም፡፡ እንደዚሁም፣ በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር በመዘገበው ግጥም ሦስተኛ ሥንኝ "ሲፈክር" የሚለው ቃል በተጠቀሱት ጸሐፍት "ሲፎክር" ተብሎ ይነበባል፡፡ ለውጡ ግእዙ "ፈ" በሳብእ "ፎ" ሆሄ መተካቱ ነው፡፡ ልዩነቱ ከቀበልኛ የመነጨም ሊኾን ይችላል፡፡ ቃሉ በአካባቢ ልዩነት ምክንያት "ፈከረ"ም "ፎከረ"ም ሊባል ይችላል፡፡ በተጨማሪም፣ ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ባሳተመው መጽሐፍ በተመዘገበው የሰንደቅ ዓላማ ማውረጃ መዝሙር ዐምሥተኛ ሥንኝ "ገናና" በሚል የተመዘገበው ቃል ላይ "ው" የሚል ምዕላድ ታክሎበት "ገናናው" ተብሎ በሌሎቹ በጠቀስናቸው ሰዎች ሥራዎች ተመዝግቧል፡፡ ቃሉ በመዝሙሩ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም "ገናና ክብራችን" እና "ገናናው ክብራችን" በሚለው የፍች ልዩነት አላስከተለም፡፡ቃሉ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም የሆሄ ለውጡ የፍቺ ልዩነት አላመጣም፡፡ ይኸም በመዝሙሩ ላይ የተስተዋለው የሆሄ አጠቃቀም ልዩነት ታስቦበት የተደረገ፣ ወይም ሲገለብጡ የተደረገ ስሕተት ስለመኾኑ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

[21]ቀንበር፡- አንደኛ፣ "በእርሻ ጊዜ በሁለት በሬዎች ትከሻ ላይ የሚያርፍና ከሞፈር ጋር በምራን የሚያያዝ የግብርና እቃ" ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፫፤ ፻፹)፡፡ ኹለተኛ፣ መከራ፣ ዕዳ፣ ስቃይ፣ ከባድ ኃላፊነት መቀበል፣ መውሰድ፣ መጋለጥ ማለት ነው፡፡ ቀንበር የተሸከሙት በሬዎች ኃላፊነታቸውን እኩል እንዲወጡ በቀንበሩ አማካይ ቦታ ላይ በምራን ይታሰራል፡፡ ቀንበሩ ከበሬው ትከሻ እንዳይወጣ በማነቂያ እንጨትና ጠፍር ይታሰራል፡፡ እርፉን፣ ማረሻ ብረቱን፣ ድግሩን፣ ቅትርቱን፣ በምራኑ አስተካክሎ ያስራል፡፡ የበሬው እርምጃ ሸሩን ጠብቆ እንዲሆን አብሮት ከተጠመደው በሬ እኩል እንዲራመድ ወይም የተጠመዱት ኹለቱም በሬዎች ፍጥነት እንዲጨምር ጠምዶ የሚያርሰው ገበሬ በጅራፍ እያስፈራራም እየገረፈም ይነዳቸዋል፡፡ በሬዎቹን ጠዋትም ማታም ሣር/ገለባ ማብላት፣ ቀን ፈትቶ ውሃ ማጠጣት የአራሹ ገበሬ ኃላፊነት ነው፡፡

ገዳይ ድል አድራጊ፣ ደም አፍሳሽ ወታደር፣
አንቺን እያሰበ፣ ይጓዛል ሲፎክር፣
ሰንደቅ ዓላማችን፣ የነጻነት አገር፡፡
ገናናው ክብራችን፣ ሰንደቅ ዓላማችን፣
ያኰራሻል ዐርበኝነታችን፡፡

መዝሙሩ ሙሉ በሙሉ ዐርበኞች የሀገራቸውን ነጻነት ማስከበራቸውን፣ ጠላታቸውን ድል ማድረጋቸውን፣ ሰንደቅ ዓላማቸውን የማስከበር ኀላፊነታቸውን ይገልጻል፡፡ ትናንት የተፈጸመን የጀግንነት ተግባር ስንቅ አድርገው ነገ የሚመጣን ጥቃት ለመመከት ዝግጁ መኾናቸውን "አንቺን እያሰበ፣ ይጓዛል ሲፎክር" በሚለው ሥንኝ ያሻግራል፡፡ የሀገራቸውን ሰንደቅ ዓላማ ክብር የማስጠበቅ ኀላፊነት የዐርበኞች መኾኑን ይገልጻል፡፡

"ተጣማጅ" የሚለው ቃል ከሌላ ጋር መቆራኘትን፣ በዓላማ፣ በተግባር መተሳሰርን ይገልጻል፡፡ ቃሉ "ተጣማጅ ዐርበኛ" በሚለው ሐረግ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም ዐርበኞች ታሪካዊ ተግባራቸውን የፈጸሙት በራሳቸው ተነሣሽነት፤ እርስ በእርሳቸው በመተባበር፣ በመተጋገዝ፣ በመረዳዳት እንደነበር ያስረዳል፡፡

በተጠቀሰው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ውስጥ ተጣማጅና ቀንበር የሚሉት ቃላት የዐርበኝነት ተግባርን ይገልጻሉ፡፡ ተጣማጅ የሚለው ቃል በሰንደቅ ዓላማው መዝሙር የገባው፣ ዐርበኛ የሚለውን ቃል ገላጭ ኾኖ ነው፡፡ ቃሉ በዚኽ አገባቡ የዐርበኝነትን ተግባር ለመፈጸም መዘጋጀትን፣ በውጊያ መሳተፍን፣ ኀላፊነት መቀበልን ይገልጻል፡፡ ዐርበኛ የሚለውም በወል መጠሪያነቱ የዐርበኛነት ተግባር የፈጸሙትን ኹሉንም ኢትዮጵያውያን ይጠራል፡፡

የዐርበኞች ኀላፊነት የተገለጸው ቀንበር የተጫነበት በሬ የሚፈጽመውን የሥራ ተግባር እና ጠምዶ የሚያርሰውን ገበሬ ተግባር በማሰብ ነው፡፡ ቀንበር የሚለው ቃል ተሸከመ ከሚለው ጋር ተጣምሮ ሲቀርብ "መከራ፣ ስቃይ ወዘተርፈ ተቀበለ" ማለት ነው፡፡ ሀገርን መውደድ ወይም ማፍቀር ከፍተኛ ኀላፊነት በመኾኑ ቀንበር ከመሸከም ጋር ይነጻጸራል፡፡ ሀገርን የመውደድ ቀንበር የተሸከመ ሰው ራሱን አሳልፎ ለመስጠት መዘጋጀትን፣ የውጭ ወራሪን ለመውጋት በሚደረግ የዐርበኝነት ትግል መሥዋዕትነት ለመክፈል መወሰንን ይገልጻል፡፡ የሀገር መውደድ ቀንበር ኀላፊነት መሸከሙ በውዴታ ግዴታ መቀበልን ሲገልጽ፣ መጠመዱም የዐርበኝነት ተግባርን ለመፈጸም ከሌላ ዐርበኛ ጋር መተጋገዝን፣ መተባበርን ያስረዳል፡፡ ቃሉ "ባገር መውደድ" ከሚለው ሐረግ ጋር በመጣመሩ ሀገር ማፍቀርን፣ ከባድ ኀላፊነት መሸከምንና የጠላትን ጫና ለመቋቋም መዘጋጀትን የዐርበኝነት ተግባር ለመፈጸም መቁረጥን ረኻብን፣ ጥምን፣ መታረዝን በጨልማ መደነቃቀፍን፣ በሾኽ፣ በጋሬጣ መወጋትን ለመቀበል መዘጋጀትን ይገልጻል፡፡

---

በተመሳሳይ ዐርበኞች ተግባራቸውን እንዲወጡ የሚመራቸው፣ ጥይት የሚያቀርብላቸው፣ የውጊያ ቦታ የሚመርጥላቸው፣ የውጊያ መሣሪያ የሚያሟላላቸው የጦር መሪው ወይም አስተባባሪው ነው፡፡ ከጠላት የሚማርኩት ጠብ መንጃና ጥይት የሚያከፋፍለው እሱ ነው፡፡ የጦርነት እንቅስቃሴው በሽምቅ ውጊያ ሥርዓት እንዲመራ ከሌሎች ዐርበኞች ጋር የሚኖረው ግንኙነት በጥንቃቄ በመተባበር እንዲሆን ማድረግ የጦር መሪው ተግባር ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን ዐርበኞች ለዐምስት ዓመታት ከኢጣልያ ወታደሮችና ደጋፊዎቻቸው (ባንዳዎች) ጋር ባደረጉት ጦርነት ደም አፍስሰዋል፤ ገድለዋል፤ ድልም አድርገዋል፡፡ ይኸም "ገዳይ ድል አድራጊ፣ ደም አፍሳሽ ወታደር" በሚለው ሥንኝ ተገልጿል፡፡ ወታደር የሚለው በዐርበኝነት ተሠማርተው የነበሩትን ኢትዮጵያውያን እንጂ በፖሊስ ወይም በጦር ሰራዊት ውስጥ ተቀጥረው የሚያገለግሉትን መለዮ ለባሾች ማለት አይደለም፡፡[22]

የውዴታ ግዴታቸውን፤ ከባድ ኀላፊነታቸውን የሀገራቸውን ጠላት በመውጋትና ድል በማድረግ የተወጡት ዐርበኞች የነጻነታቸው ምልክት የኾነችውን ሰንደቅ ዓላማቸውን ለማስከበር ቃል ይገባሉ፡፡ ቃል መግባቱ የተገለጸው ፉከራ[23] የሚለው ቃል የሚጠራውን ባህላዊ ክንዋኔ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በሰንደቅ ዓላማው መዝሙር ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም ግን ዐርበኞች ጠላታቸውን ድል ለማድረግ ማቀዳቸውን፣ መወሰናቸውን፣ መቁረጣቸውን፣ በራሳቸው ተነሳሽነት ኀላፊነት መውሰዳቸውን ያስረዳል፡፡ ቀጥሎ ከሚመጣው ሥንኝ ከተገለጸው ሐሳብ ጋር ሲሰናሰል የሀገራቸውን የነጻነት ምልክት የኾነችውን ሰንደቅ ዓላማ ክብር ለመጠበቅና ነጻነታቸውን ለማስከበር የጀግንነት ተግባር ለመፈጸም ቃል መግባታቸውን ያስረዳል፡፡ ዐርበኞች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለማስከበር፣ ነጻነቷን ለመጠበቅ "አንቺን እያሰበ፣ ይጓዛል ሲፎክር" በሚለው ሥንኝ የተገባውን ቃል በሚከተሉት ሥንኞች በድጋሚ ተስፋ መስጠቱን፣ ውል መግባቱን ያረጋግጣል፡፡

ገናናው ክብራችን፣ ሰንደቅ ዓላማችን፣
ያኰራሻል ዐርበኝነታችን፡፡

---

[22]ከ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ከኢጣልያ ጦር ጋር በተደረገው ጦርነት ኢትዮጵያ የተጠናከረ መደበኛ ጦር አልነበራትም፡፡ የኢትዮጵያ የፖሊስ ሠራዊት፣ የምድር ጦር፣ የአየር ኀይል፣ የባሕር ኀይል እንዲሁም ዘመናዊ ወታደራዊ ተቋማት ተደራጅተው ሀገርን ከጠላት መከላከል የጀመሩት የኢጣልያ ጦር በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ድል ከተደረገ በኋላ ዘግይቶ ነው (ባሕሩ፣1999 )፡፡

[23]ፉከራ ባህላዊ የጀግንነት ተግባርን ለመግለጽ በተለያዩ ዐውዶች ይቀርባል፡፡ (ግዳይ መጣል የሚለው ሐረግ የሚገልጸው፣ በጦርነት የተሳተፈ ሰው ስለፈጸመው ጀብድ ምስክር በመጥቀስ በሽለላና በፉከራ መናገሩን ወይም ምርኮውን ማቅረቡን ወይም ያደነውን አቅርቦ ማሳየቱን ነው፡፡ አንድም፣ ወደ ጦርነት ሲዘምት፣ ውጊያ ለመግጠም ሲዘጋጅ፣ ጠላቱን ወግቶ ድል ለማድረግ፣ ጠላቱን ከቅርብ ርቀት የተመለከተ ሰው በጠላቱ ላይ የጀግንነት ተግባር ለመፈጸም ጥቃት ለማድረስ፣ ማርኮ ለማቅረብ ቃል መግባቱን ለመግለጽ፣ የድፍረት ስሜቱን ለማነሣሣት የሚያሰማው ዛቻ ነው፡፡ አንድም፣ በጦርነት የተሳተፈ ወታደር፣ ጠላቱን ለመግደሉና የጀግንነት ተግባር ለመፈጸሙ ከአለቃው ፊት ቀርቦ የፉከራ ግጥም በመደርደር ግዳዩን ያቀርባል፡፡ ግዳይ መጣልም በጦርነት የተሳተፈው ዐርበኛ ጠላቱን ለመግደሉና የጀግንነት ተግባር ለመፈጸሙ ማስረጃ ነው፡፡ ማስረጃ ግዳይ በመጣል ወይም የማረከውን በማቅረብበድንፋታ ማሳወቂያ ነው፡፡ ጠላቱን በመግደል ድል ያገኘ ጀግና ለአለቃው ግዳይ በመጣል መፎከር ነገሥታቱ፣ መሳፍንቱና መኳንንቱ ይመሩት በነበረው የኢትዮጵያ ዐርበኛዘንድ የተለመደ ነበር፡፡ አንድም፣ አዳኝ ያደነውን አቅርቦ በማሳየት፣ በሽለላና በፉከራ የፈጸመውን ተግባር መንገሪያ ነው፡፡ በዐውዳዊ አጠቃቀሙ ፉከራ ለመፈጸም የታሰበን የጀግንነት ተግባር ማሳወቂያ፣ መንገሪያ ድንፋታ ነው፡፡

ለተጨማሪ ግንዛቤ በማኅተመ ሥላሴ (፲፱፻፷፪፤ ፪፻፵፰ የግርጌ ማስታወሻ) ስለ ፉከራ የሚከተለውን ብለዋል፡፡ "ዠግና የሆነ ሰው ሲፎክር ዠግንነቱን የሚያውቁለት ነወር ብለው ይነሡለታል፤ እሱም በእግዚአብሔር ተቀመጡ ይልና ፉከራውን ይቀጥላል፤ በመኻከሉም ሞያውን የሚያውቁለትን እህ እገሌ እህ እገሌ ብሎ ሲጠይቃቸው ለካ ለካ አይተናል ሠርቷል እያሉ ያረጋግጡለታል፡፡ እሱም ደስ ብሎት ካይናችሁ ያውጣኝ ጌቶቼ ወንድሞቼ ተቀመጡ ብሎ ያልፋል፡፡ ሽለላው ይቀጥላል፤ ደግሞ ሌላው ዠግና ይተካል፡፡ አንዱ ሲፎክር አንዱ ተደርቦ የፎከረ እንደ ሆነ ምነው በላዬ በምን በልጠኸኝ ነው ተባብለው ሞያቸውን ይቋጠራሉ፡፡ ለበለጠው ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ ስለዚህም በሞያ ለመብለጥ ባደባባይ ለመከበር ሹመት ሽልማት ለመቀበል ሀገርን መንግሥትን ለማስከበር ሲሉ ወታደሮች በጦር ሜዳ ላይ ያለፍርሃትና ያለሥጋት ጠመንዣቸውን ትተው ቀርበው በጎራዴ ጠላታቸውን ሲቀጡ ይታያሉ፡፡"

“ገናናው ክብራችን” የሚለው ሐረግ ጎልቶ የታወቀውን፣ የተሰማውን፣ የናኘውን የኢትዮጵያውያን የነጻነትና የሉዓላዊነት ክብር ታሪክ ይዘክራል፡፡ ታሪኩም የኢትዮጵያውያን ነጻነት ትእምርት የኾነችውን ሰንደቅ ዓላማ ለማስከበር ዐርበኞች መሥዋዕትነት ከፍለው፤ የኢጣልያንን ጦር ድል በማድረጋቸው የተገኘ ነው፡፡ የኢጣልያ ጦር ድል የተደረገው በዐምሥቱ የዐርበኝነት ትግል ዓመታት ብቻ አይደለም፡፡ ዶጋሊ ላይ በራስ አሉላ፣ ዐምባ አላጌ ላይ በፊታውራሪ ገበየሁ መሪነት፣ እንዳ ኢየሱስ ላይ በእቴጌ ጣይቱ የጦር ሥልትና መመሪያ አድዋ ላይ በዐፄ ምኒልክ መሪነት የኢጣልያ ጦር በኢትዮጵያውን የተሸነፈበት ታሪክ የኢትዮጵያ ስምና የአሸናፊነት ታሪክ በዓለም ላይ እንዲነግሥ አስችሏል፡፡ ዐርበኞች በመሥዋዕትነት ያስከበሩዋትን ሰንደቅ ዓላማቸውን ለማዋረድ የሚያስብና የሚሞክር የውጭ ጠላት በመከላከል አለኝታዋ፣ መኩሪያዋ፣ መመኪያዋ ዐርበኞች ልጆቿ ናቸው፡፡ በሰንደቅ ዓላማ ማውረጃ መዝሙሩ የመጨረሻ ሥንኝ ዐርበኞች የኢትዮጵያን ነጻነት ለመጠበቅ ያላቸው ሚና ጎልቶ ተነግሯል፡፡

የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የተጻፉት የዐርበኞች ተጋድሎ ትዝታ ሳይደበዝዝ አለባበሳቸውና ጎፈሬ አበጣጠራቸው ሳይለወጥ፣ ወኔያቸው ሳይላላና ቁርጠኛ አቋማቸው ሳይለወጥ፣ በሕይወት ሥጋ እያሉ ነው፡፡ የድል ቀን ሲከበር ዐርበኞች ፀጉራቸውን አጎፍረው ትጥቃቸውን አሳምረው እየሸለሉና እየፎከሩ ይታያሉ፡፡ ይኽም፣ ወጣቶቹ አርአያነታቸውን እንዲከተሉ፣ በአንደበታቸው በሚዘምሩት፣ በጆሮአቸው በሚያዳምጡት መዝሙር የሚገለጸውን የዐርበኝነት ወኔያቸውን፣ ስሜታቸውንና አለባበሳቸውን ወጣቶቹ በዐይናቸው ማየታቸው የዐርበኞችን ማንነት ይበልጥ እንዲገነዘቡ ለነጻነት የተከፈለውን መሥዋዕትነት ይበልጥ እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ዐርበኞቹን ለመምሰልና ከእነርሱ የሚጠበቀውን ግዴታ እንዲያጤኑ አርአያነታቸውን ለመከተል እንዲነሣሡ ያበረታታቸዋል፡፡ ሀገራቸውን ከጠላት ለመከላከል ቁርጠኛ አቋም እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

ለማጠቃለል የኢጣልያቅኝ ገዢ ጦር በዐርበኞች ከፍተኛ ትግል በእንግሊዝ ጦር ትብብር ሀገራችንን ለቅቆ ከወጣ በኋላ የተደረሱት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች የጠላትን ጦር በማጥቃት የሀገርን ነጻነት በማስከበር የዐርበኞች ሚና ከፍተኛ እንደ ነበር ይነግራሉ፡፡ ዐርበኞች ለንጉሠ ነገሥቱ፣ ለሀገራቸው ነጻነትና ለክብራቸው የከፈሉትን መሥዋዕትነት ይዘክራሉ፡፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የነጻነት ምልክት ለኾነችው ለኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ክብር ይሰጣሉ፡፡ የኢትዮጵያ ነጻነት የደምና የሕይወት መሥዋዕትነት ከፍለው ያስጠበቁት ዐርበኞች መኾናቸውን በሕዝቡ በጠቅላላ በተለይ ደግሞ በወጣቱ አእምሮ ያሰርጻሉ፡፡ ዐርበኛዎቹ በከፈሉት መሥዋዕትነት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ መደረጉን ያስታውሳሉ፡፡ በየትምህርት ቤቱ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ማታ ደግሞ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ መዝሙሮቹን በመዘመር ወጣቱ ትውልድ የንጉሠ ነገሥቱንና የዐርበኞችን ተጋድሎ እንዲያውቅ፣ አርአያነታቸውን እንዲከተል፣ ለሰንደቅ ዓላማው ክብር እንዲሰጥና ለነጻነቱ እንዲተጋ ይቀሰቅሳል፡፡

በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. የተደረሱት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. በተደረገው የመንግሥት ለውጥ አገልግሎት እንዳይሰጡ ተደረገ፡፡ እላይ እንደተገለጸው በምትካቸው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮችን ለማዘጋጀት የሥነ ጽሑፍና የሙዚቃ ባለሙያዎች በማስታወቂያ ተጋበዙ፡፡ ለሰንደቅ ዓላማ መዝሙር የሚኾኑ ግጥሞችንና ዜማዎችን በማቅረብ ተወዳደሩ፡፡ ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣

እንዲሁም ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ ሊዘመሩ የሚችሉ ግጥሞችና ተስማሚ ዜማዎች በ፲፱፻፹፪ ዓ.ም ተመረጡ፡፡ ግጥሞቹ በዜማ ሳይቀነባበሩና አገልግሎት ሳይሰጡ የ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. የመንግሥት ለውጥ ተካኼደ፡፡

በ፲፱፻፹፪ ዓ.ም. ለሰንደቅ ዓላማ መዝሙር እንዲያገለግሉ ተመርጠው የነበሩት ግጥሞች እንዴት እንደተመረጡ፣ ይዘታቸው ምን እንደነበርና የተመረጡበትን ዐውድ ምን ያኽል እንደሚያንጸባርቁ በሚከተለው ንዑስ ርእስ እንመለከታለን፡፡

## 4) በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ (ኢሕዲሪ) መንግሥት የታጩ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች[24]

> የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ የሕዝብና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሀገር ፍቅር፣ ለሰንደቅ ዓላማው፤ ለአንድነቱና ለነጻነቱ መጋደሉን የሚያበስር ሰፊው ሕዝብ ለሰብአዊ ክብሩ ያደረገውን ተጋድሎና መሥዋዕትነት የሚያስታውስ፤ ያሁኑና ተተኪው ትውልድ ያለፈውን በማስታወስ በጥሩ ታሪኩ እንዲመካ በተራማጅ መንፈስ ኩሩና ቆራጥ ኢትዮጵያዊ መሆኑ እንዲሰማው የሚያደርግ መሆኑን ...አሰፋ ገብረ ማርያም ለአዲስ ዘመን ገልጠዋል፡፡ (አዲስ ዘመን፣ ረቡዕ መስከረም ፲፫ ቀን ፲፱፻፷፰፣ ፴፮ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፷፻፲፮፣ ፩)

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተደደር ደርግ በወርኀ መስከረም ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ሥልጣን ከያዘ በኋላ በኀይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ያገለግሉ የነበሩት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች አገልግሎት እንዳይሰጡ አገደ፡፡ በታገዱት ምትክ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ለማዘጋጀትም መጀመሪያ በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የሥነጽሑፍ ባለሙያዎች ግጥሞችንና ዜማዎችን በማቅረብ እንዲወዳደሩ በቴሌቪዥን ማስታወቂያ በማስነገር፣ በአዲስ ዘመን ጋዜጣም በማውጣት ጋበዘ፡፡[25]የሰንደቅ ዓላማ

---

[24]በዚኽ ሥር ለቀረበው ሐተታ መረጃዎች በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር በሥነ ጥበባትና ቲያትር መምሪያ ሥር ተቋቁሞ ከነበረው አወዳዳሪ ኮሚቴ ቃለ ጉባዔ ፋይል ቁጥር ተመዝግበው የተገኙ ናቸው፡፡

[25]አዲስ ዘመን ጋዜጣ ኀሙስ ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ፫፻፴፩ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፩፻፵፩ "ሊቃውንት አዲስ የሕዝብ መዝሙር እንዲያዘጋጁ ተጠየቀ" በሚል ርእስ ባወጣው ዘገባ ስለሰንደቅ ዓላማ መዝሙር አላወሳም፡፡
ይኹን እንጂ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትን ዋቢ አድርጎ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዐርብ ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ፴፭ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፯፻፷ እትሙ ስለኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር በድጋሚ ባወጣው ማሳሰቢያ ስለ ሰንደቅ ዓላማ መዝሙርም አንስቷል፡፡ ጋዜጣው አንድ የመንግሥት ቃል አቀባይን መግለጫ በመጥቀስ ዘግቧል፡፡ ይኸውም "የሕዝብና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ለማዘጋጀት ተወዳዳሪዎች መዝሙራቸውን አሟልተው እንዲያቀርቡ ከዚህ በፊት ተገልጾ እንደ ነበር ይታወሳል፡፡ ሆኖም ብዙዎች የሕዝብ መዝሙሮች ሕግ ሳይከተሉ ስለቀረቡ ጥሩ ጥሩ ግጥሞችና ዜማዎች ወድቀዋል፡፡" በማለት የተናገረውን አቅርቧል፡፡ ቀጥሎም የሕዝብ መዝመር ሊያሟላው የሚገባውን መመዘኛ ዘርዝሯል፡፡ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተዘገበው የመንግሥት ቃል አቀባዩ መግለጫ መዝሙሩ ሊያሟላው የሚገባውን መመዘኛ ሲገልጽ ሙሉ በሙሉ ትኩረት ያደረገው በሕዝብ መዝሙር ላይ ነው፡፡
አሰፋ ገብረማርያም ረቡዕ መስከረም ፲፫ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ፫፻፷፫ኛ ዓመት ቁጥር ፷፻፲ ስለብሔራዊ መዝሙር በሰጡት ቃለመጠይቅ የብሔራዊ መዝሙርንና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮችን ለመድረስ እንዴት እንደተነሣሡ ገልጸዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ውድድር በመንግሥት ጋባዥነት ሲካኼድ መሰንበቱን ቢያውቁም አልተወዳደሩም ነበር፡፡ የእሳቸው የመወዳደር ፍላጎት የተነሣሣው ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. "ማታ [በቴሌቪዥን ወይም በሬዲዮ] ለውድድር የቀረቡት ግጥሞችና ሙዚቃዎች አጥጋቢ አለመኾናቸውን መንግሥት ገልጦ ከነባሮቹ ሌላ አዳዲስ ተወዳዳሪዎች እንዲገቡ"

መዝሙር አሸናፊዎችም በጋዜጣ ተገለጹ፡፡ ጋዜጣውም “አቶ አሰፋ ገብረ ማርያም የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙርና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች በአብዮታዊ መንፈስ መላውን የኢትዮጵያ ኅብረተሰብና መልክዓ-ምድር በሚያጠቃልል ሁኔታ በማቅረባቸው ከብዙ ተወዳዳሪዎች መካከል አሸናፊ መሆናቸው”ን ገለጸ (አዲስ ዘመን ጋዜጣ ፴፰ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፫፻፰፣ መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፷፰፤ ፲፩)፡፡ በዚኹ ጋዜጣ ገጽ ፪ ላይ አሰፋ ገብረ ማርያም አሸናፊ የኾኑባቸው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ተገለጹ፤ ዜማቸውንም ዳንኤል ዮሐንስ መድረሳቸው ተዘገበ፡፡ ዳንኤል ዮሐንስም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ በሰጡት ቃለ መጠይቅ በአሰፋ ገብረ ማርያም የተደረሱትን የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች በዜማ ማቀነባበራቸውን ገለጹ (አዲስ ዘመን፣ ፴፰ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፫፻፲ መስከረም ፮ ቀን ፲፱፻፷፰፤ ፫)፡፡ መዝሙሮቹ ግን አገልግሎት እንዲሰጡ አልተደረገም፡፡

አሰፋ ገብረ ማርያም (1971) ባሳተሙት የግጥም ስብስብ መጽሐፍ በ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. የደረሷቸውንና በውድድር አሸናፊ የኾኑባቸውን ሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች በገጽ 56- 57 ላይ አሳትመዋል፡፡ መዝሙሮቹን የደረሱበትን ምክንያትና ለምን እንደማይዘመሩ ሲገልጹ፡-

> …በሶሻሊስት አገሮች ለሰንደቅ ዓላማ የተለየ መዝሙር ባይኖርም፤ ሶሺያሊዝም በይዘቱ ዓለም አቀፋዊ፣ በቅርጹ ደግሞ ብሔራዊ ነውና ለታሪካዊቷ ሰንደቅ ዓላማችን ክብር ራሱን የቻለ ዜማ ማውጣቱና በየጦር ክፍሉና በየት/ቤቱ እንዲዘመር ማድረጉ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የታሪክ ቅርስ ባለቤት መሆኑን ያስመሰክራል፡፡ በብሔራዊ ደረጃ በተደረገው ውድድር ግጥሞቹ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በአሸናፊነት ተመርጠው በጊዜው ተስማሚ ሙዚቃ ባለመገኘቱ ዜማው አልወጣም፡፡ ኾኖም ከመስከረም 1 ቀን 1968 ዓመተ ምሕረት ወዲህ ካንዴም ኹለቴ ብዙ የታወቁ የዜማ ደራሲያች ተወዳድረዋል፡፡ ስለኾነም፣ ጉዳዩ በቅርቡ አንድ ውሳኔ እንደሚያገኝ ተስፋ ተደርጓል (አሰፋ፣ 1971፤ 58)፡፡

ብለዋል፡፡

አሰፋ ተወዳድረው አሸናፊ የኾኑባቸው የሰንደቅ ዓላማ ማውጫና ማውረጃ መዝሙሮች ያልተዘመሩበት ምክንያት ተስማሚ ዜማ ባለመገኘቱ መኾኑንም ገለጹ (አዲስ ዘመን፣ ፴፰ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፫፻፲፣ መስከረም ፮ ቀን፣ ፲፱፻፷፰፤ ፫)፡፡[26] ከመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም.

---

ማሳሳቡ ነው፡፡ በማሳሰቢያው መሠረትም የሕዝብ መዝሙሩንና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮችን መድረሳቸውን ገልጸዋል፡፡

[26]ዳንኤል ዮሐንስ በአሰፋ ገብረ ማርያም ለተደረሱት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርንና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮችን በዜማ ማቀነባበራቸውን በተጠቀሰው ጋዜጣ ላይ ገልጸዋል፡፡ አሰፋ ገብረ ማርያምም በ1971 ዓ. ም ባሳተሙት መጽሐፍ በእሳቸው ለተደረሱት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች የሚስማማ ሙዚቃ ባለመገኘቱ ዜማው አለመውጣቱን አስረድተዋል፡፡ ቅዳሜ መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ፴፰ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፫፻፰ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ግጥሞች ተጽፈው ከስራቸው የግጥሙ ደራሲ አሰፋ ገብረማርያም ተሰማ፣ የሙዚቃው ደራሲ ደግሞ ዳንኤል ዮሐንስ መኾናቸው ተገልጿል፡፡ በዚኹ ጋዜጣ “የብሔራዊ ዓርማና መዝሙር አሸናፊዎች ከዋናው ሊቀ መንበር ቀርበው ተመሰገኑ” በሚል ርእስ በቀረበው ዘገባ “አሰፋ ገብረማርያም የኢትዮጵያን የሕዝብ መዝሙርና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ግጥም በአብዮታዊ መንፈስ መላውን የኢትዮጵያ ሕብረተሰብና መልክዐ ምድር በሚያጠቃልል ሁኔታ በማቅረባቸው ከብዙ ተወዳዳሪዎች መካከል አሸናፊ መኾናቸው” ተገልጿል፡፡ በሌላ በኩል፣ ዳንኤል ዮሐንስ ከዋናው ሊቀመንበር ምስጋና ያገኙት “በአቶ አሰፋ ገ/ማርያም

ወዲህ የታወቁ የዜማ ባለሙያዎች በመወዳደራቸው ግጥሞቹ በዜማ ተቀነባብረው እንደሚዘመሩ ተስፋ ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

ሰይፉ (1987፤ 35) በበኩላቸው አሰፋ ገብረ ማርያም የደረሷቸው ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ምሽት ደግሞ ሰንደቅ ዐለማ ሲወርድ የሚዘመሩ መዝሙሮች በመንግሥት ተቀባይነት እንዳገኙና አገልግሎት እንደሰጡ ቆጥረው መዝግበዋቸዋል፡፡ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የሚዘመረውን በገጽ 244፣ ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመር ያሉትን ደግሞ በገጽ 245 መመዝገባቸውን እናነባለን፡፡ ቀጥለን እንደምንመለከተው በአሰፋ ገብረማርያም የተደረሱትን ግጥሞች/መዝሙሮች አገልግሎት እንደሰጡ ቆጥረው መዝግበው አቅርበዋል፡፡

ይኹን እንጂ፣ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር የዜማ ውድድርን ለመዳኘት ከተቋቋመው ኰሚቴ ሪፖርት መረዳት እንደሚቻለው ከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ ውድድሮች እንዲካኼዱና ዝግጅቶቹ ተጠናቅቀው ሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ቢሞከርም እንኳ በተለያዩ ምክንያቶች ጥረቱ ዳር ሊደርስ እንዳልቻለ ተዘግቧል፡፡ መጀመሪያ የሥነ ጽሑፍና የሙዚቃ ባለሙያዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር በማቅረብ እንዲወዳደሩ ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ሲጋበዙ ለሰንደቅ ዓላማ መዝሙር የሚኾኑ ሥራዎችን እንዲያቀርቡም መጋበዛቸውን ዐርብ ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. <u>አዲስ ዘመን</u> ጋዜጣ ፴፫ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፺፻፷ ላይ ተገልጿል፡፡ በዚኹ ጋዜጣ የሥነ ጽሑፍና የሙዚቃ ባለሙያዎች ለሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ግጥምና ዜማ እንዲያቀርቡ ለኹለተኛ ጊዜ ተጋበዙ፡፡ በመጀመሪያው ውድድር የባለሙያዎች ውድድር ያልተሳካው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙርን ሳይከተሉ ስለቀሩ መኾኑ ተዘግቧል፡፡ [27]

ለሦስተኛ ጊዜ የሥነጽሑፍና የሙዚቃ ባለሙያዎች ለሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ግጥምና ዜማ በማቅረብ እንዲወዳደሩ የተጋበዙት በ፲፱፻፸፰ ዓ. ም. ነው፡፡ ይኸም የመጀመሪያው ውድድር ከተደረገ ከዐሥራ ሦስት ዓመታት በኋላ ማለት ነው፡፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ዝግጅት ጉዳይ

የተደረሰውን ግጥም ለሕዝብ መዝሙር በሚስማማና በሚጥም ዜማ በማቅረባቸው ከብዙ ተወዳዳሪዎች" አሸናፊ በመኾናቸው እንደኾነ ተዘገበ፡፡ ዳንኤል ዮሐንስ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹን በዜማ ቢያቀነባብሩም፣ በመንግሥት ለመመስገን የቻሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር የሙዚቃ ደራሲ በመኾናቸው ነው፡፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹን ሙዚቃ ቢደርሱም በመንግሥት ዕውቅና አለመሰጠቱ ሥራው ተቀባይነት እንዳልነበረው ይጠቁማል፡፡ ከዚኽም፣ ዳንኤል ዮሐንስ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹን በሙዚቃ አቀነባብረው ለውድድር አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም ማለት ነው፡፡ ወደፊትም እንደምንመለከተው በ፲፱፻፸፰ ዓ. ም. የሥነጽሑፍና የሙዚቃ ሰዎች የሰንደቅ ዓላማ ግጥምና ዜማ እንዲያቀርቡ ሲጋበዙ አሰፋ የደረሷቸውን የሰንደቅ ዓላማ ግጥሞች ለውድድር ደግመው ማቅረባቸው ሥራቸው ቀድሞውኑም ተቀባይነት እንዳልነበራቸው ያመለክታል፡፡ በመንግሥት ተቀባይነት ያላገኘን ግጥም በሙዚቃ ማቀነባበር ተቀባይነት የለውም አይኖረውም ማለት ነው፡፡

[27]የሰንደቅ ዓላማ ዐዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፸፰ <u>ነጋሪት ጋዜጣ</u>" የሰንደቅ ዓላማ ምንነት"፣ "የሰንደቅ ዓላማው ቀለማትና ቅርጽ"፣ "የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት ትርጉም"፣ "የሰንደቅ ዓላማው አጠቃቀም"፣ "የሰንደቅ ዓላማው አያያዝ" ሰንደቅ ዓላማው የሚወጣበትና የሚወርድበት ጊዜ ወዘተርፈ ሲገለጽ ስለ ሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ግን ምንም አልተባለም፡ ፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች አገልግሎት እንዲሰጡ ቢወሰን ኖሮ ሰንደቅ ዓላማው የሚወጣበትና የሚወርድበት ጊዜ ሲገለጽ የሰንደቅ ዓላማው መዝሙሮች አገልግሎትም ሲገለጽ ይችል ነበር፡፡ ይኸም "ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣና ሲወርድ ይዘመራሉ" ተብለው የተደረሱት መዝሙሮች በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ተቀባይነት ያላገኙ ስለመኾናቸው ፍንጭ ይሰጣል፡፡

እንዴት እንደገና ትኩረት እንደተሰጠውና የምርጫው ሂደት እንዴት እንደነበር ቀጥሎ በሚቀርበው ንዑስ ርእስ እንመለከታለን፡፡

### 4.1) የኢሕዲሪ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር መመዘኛና የአመራረጥ ሂደት

የኢትዮጵያን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምሥረታን ምክንያት በማድረግ የመንግሥት ዓርማ፣ ብሔራዊ መዝሙርና የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ለማዘጋጀት ተወሰነ፡፡ በየካቲት ወር ፲፱፻፹ ዓ. ም. የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ግጥምና ዜማ ውድድር እንዲደረግ ከኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ ርዕዮተዓለም መምሪያ ለባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ከመወዳደሪያ መመሪያ ጋር ማስታወሻ ተላከ፡፡ በማስታወሻውም ለሰንደቅ ዓላማ መዝሙር እንዲሆን ለውድድር የሚቀርበው ግጥም ይዘት ተገለጸ፡፡ በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር የሥነ ጥበባትና ቲያትር መምሪያ ከኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) ማዕከላዊ ኮሚቴ ርዕዮተዓለም መምሪያ የተላከለትን የማወዳደሪያ መስፈርት ከኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ጋር በመተባበር መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ ለሰንደቅ ዓላማ የሚሆኑ ግጥሞችን በማቅረብ እንዲወዳደሩ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎችን በ<u>አዲስ ዘመን</u> ጋዜጣ ጋበዘ (አዲስ ዘመን፣ ፵፯ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፳፻፴፱፣ ግንቦት ፳፭ ቀን ፲፱፻፹፤ ፬)፡፡ በ<u>አዲስ ዘመን</u> ጋዜጣ ላይ ለተወዳዳሪዎች የተገለጹት የማወዳደሪያ መሥፈርቶች (የግጥሙ ይዘት መሆን ያለበት) የሚከተሉት ናቸው፡፡[28]

- የሰንደቅ ዓላማችንን ትርጉም የሚያንፀባርቅና ከፍ ያለ የሥነ ውበትደረጃ ያለው፤
- ሰንደቅ ዓላማችን ያባቶቻችን ጀግንነት፣ የረጅም ታሪካችንና የአኩሪ ባህላችን መግለጫ መሆኑን የሚያሳይ፣
- የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት፣ እኩልነትና ኅብረት ማንፀባረቂያ መሆኑን የሚገልጽ፣
- ሰፊው ሕዝብ እናት ሀገሩን በሥራ ለመገንባትና ለደኅንነቱ ዋስትና ለመስጠት ቆርጦ መነሣቱን የሚያረጋግጥ፣
- በማንኛውም የዕድሜ ክልል የሚገኝ ዜጋ ሁሉ በቀላሉ ሊረዳውና በቃል ሊይዘው የሚችል፤ የቃላቱም ትርጉም አሻሚነት የሌለው፣
- ግጥሙ ከ፳ መስመሮች ያልበለጠና ለሙዚቃ ቅንብር አመች እንዲሆን ያሻል፡፡

ከዚህ በላይ ከተመለከቱት የግጥሙ ይዘት በተጨማሪ የሚከተሉት ማሳሰቢያዎች በአወዳዳሪ ኮሚቴው ለተወዳዳሪዎች ተገለጸ፡፡

- የሰንደቅ ዓላማው መዝሙር ጠዋት ለማውጫና ምሽት ላይ ለማውረጃ የሚዘመር ስለሆነ ሁለት የተለያዩ ግጥሞች እንዲቀርቡ፡፡
- በውድድሩ አሸናፊ ለሚሆኑ ሽልማት ይሰጣል፡፡

---

[28]ማስታወቂያውን መሠረት በማድረግ ፻፶፩ ተወዳዳሪዎች፣ አሰፋን ጨምሮ፣ ለሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ይሆናል ያሏቸውን ግጥሞች ለውድድር አቀረቡ፡፡ (በተወዳዳሪዎች ከቀረቡት ግጥሞች ስንቱ ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ስንቱ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ ይዘመራሉ ተብለው እንደቀረቡ ለማወቅ አልተቻለም፡፡)

- ተወዳዳሪዎች ሙሉ ስማቸውንና አድራሻቸውን ከግጥሞቹ ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተወዳዳሪዎች ሥራዎቻቸውን እስከ ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፸ ድረስ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ቢሮ ቁጥር ፸፩ ድረስ በማምጣት ማስረከብ ይኖርባቸዋል፡፡

የማወዳደሪያ መስፈርቱ በዐዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፸ በአንቀጽ ፫ የተደነገገውን የሰንደቅ ዓላማ ዐዋጅ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ መዝሙሩ የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት፣ የረጅም ታሪክ ባለቤትነት፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት፣ ኅብረትና የወደፊት ተስፋን ይገልጻል፡፡ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ለተወዳዳሪዎች ከተገለጹት የመወዳደሪያ መስፈርቶች በተጨማሪ ገምጋሚ ኰሚቴው “፩) የቃላት አመራረጥ፣ ፪) ሙዚቃዊ ምት፣ ፫) ለአንደበት የቀናነቱ ሁኔታ እና ፬) ለመታወስ ያለው ብቃት” የሚሉ ተጨማሪ መመዘኛዎችን ተጠቅመዋል፡፡

አሰፋ ገብረማሪያም ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣና ሲወርድ እንዲዘመሩ በ1967 ዓ. ም. ያቀረቧቸውና በ1971 ዓ. ም. ያሳተሟቸውን ግጥሞች በተጨማሪም ከእነዚሁ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች አውጣጥተው ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣም ሲወርድም የሚዘመር ሦስተኛ መዝሙር በ፲፱፻፸ ዓ. ም. ለተደረገው ውድድር አቀረቡ፡፡ ከኹለቱ ግጥሞቻቸው የተውጣጣ ጠዋትም ምሽትም ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣና ሲወርድ ለሚዘመር ይኾናል ብለው አንድ ግጥም ጨምረው ያቀረቡት ቀደም ሲል በተገለጸው መጽሐፋቸው ያሳተሟቸው ኹለቱ ግጥሞቻቸው ተቀባይነት ካላገኙ ብለው በማሰብ ነው፡፡[29]

---

[29] በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር በሥነ ጥበባትና ቲያትር መምሪያ ሥር በተቋቋመው አወዳዳሪ ኰሚቴ ለውድድር ከቀረቡት ፻፶፩ ግጥሞች የሰባት ተወዳዳሪዎች ስምንት ግጥሞች ተመረጡ፡፡ ከተመረጡት ስምንት ግጥሞች መካከል ሁለቱ በአሰፋ ገብረ ማርያም የቀረቡ ናቸው፡፡ ግጥሞቹም በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. አሸናፊ ያሏቸውና በመጽሐፋቸው አካተው ያሳተሟቸው ናቸው፡፡ በገምጋሚ ኰሚቴው ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ምሽት ደግሞ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ እንዲዘመሩ በአሰፋ ገብረ ማርያም የቀረቡት ግጥሞች በአንደኛነት ተመረጡ፡፡ ስድስቱ ተወዳዳሪዎች የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች የኹሉም “ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የሚዘመሩ” በሚል የቀረቡ ሲኾን በገምጋሚ ኰሚቴው የተሰጣቸው ደረጃም የአርዮስ ከመንቱ ፪ኛ፣ የግርማ ዘነበ ፫ኛ፣ የታገል ሰይፉ መሸሻ ፬ኛ፣ የበቀለ ተሾመ ፭ኛ፣ የወግአየሁ ተገኝ ፮ኛ እና የሚሊዮን ደሳለኝ ፯ኛ የሚል ነበር፡፡ በአሰፋ የቀረበው ሦስተኛው ግጥም ደረጃው ሳይገለጽ ከተመረጡት መዝሙሮች ጋር አብሮ ለኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ማዕከላዊ ኰሚቴ ጽ/ቤት ርዕዮተ ዓለም መምሪያ ተላከ፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ለማዕከላዊ ኮሚቴው የተላኩት ግጥሞች ብዛትም ዘጠኝ ነበር፡፡

ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በቁጥር በ1/መ30/9/1 በቀን፣ 13-1-81 በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ለርዕዮተ ዓለም መምሪያ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ግጥም ውድድር ውጤትን ለመግለጽ በጻፈው ደብዳቤ የተገለጸ ነው፡፡ በደብዳቤው እንደተገለጸው ለኢህዲሪ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ጠዋት ለማውጫና ምሽት ለማውረጃ የሚኾን የመዝሙር ግጥም በውድድር እንዲመረጥ ከርዕዮተ ዓለም መምሪያ ለባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር መመሪያ በመተላለፉ፣ ለተወዳዳሪዎች ጥሪ ማድረጉን፣ ፩፻፶፩ ግጥሞች መቅረባቸውንና የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ግጥሞቹን እንዲገመግም በደብዳቤ ትብብር መጠየቁን ያትታል፡፡ ማኅበሩም ግጥሞቹን ገምግሞ በመጀመሪያው ዙር ፳፯ ግጥሞችን መርጦ፣ በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት የኢደማ [የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር] መሠረታዊ ማኅበር ኮሚቴ አቋቁሞ፣ የመጨረሻ ማጣሪያ አድርጎ የሰባት ደራሲያንን ስምና ግጥሞች እንደቅደም ተከተላቸው በማስቀመጥ ሪፖርት ያደረገውን ውሳኔ እንዲሰጥበት አባሪ በማድረግ መላኩን ይገልጻል፡፡

የርዕዮተ ዓለም መምሪያ በአወዳዳሪ ኰሚቴው ተመርጠው ከቀረቡለት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች መካከል ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የአሰፋ ገብረ ማርያምን፣ ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ ደግሞ የሚሊዮን ደሳለኝን ግጥም ማሻሻያ እንዲደረግባቸው አስተያየት በመስጠት መረጠ፡፡ ሚሊዮን ደሣለኝ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የሚዘመር ብለው ያቀረቡት ግጥም በርዕዮተ ዓለም መምሪያ ተሻሽሎ ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ እንዲዘመር በማለት ያቀረበውን ሐሳብ ተቀበሉ፡፡ መቀበላቸውንም በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ሥነ ጥበባትና ቴአትር መምሪያ ሥር ለተቋቋመው አወዳዳሪ ኰሚቴ በደብዳቤ በመግለጻቸው ሥራቸው ተቀባይነት አገኘ፡፡ አሰፋ ገብረ ማርያም ግን፣ ተሻሽሎ ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ እንዲዘመር የተመረጠውን ግጥም አሻሽለው እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይኾኑ ቀሩ፡፡ የማሻሻያውን ሐሳብ ባለመቀበል ተቃውሞ በማቅረብ የእሳቸው ግጥም ከውድድሩ እንዲወጣ እንዲደረግ ውድድሩን ለሚመራው በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ሥር ለነበረው ለሥነ ጥበባትና ቲያትር መምሪያ ማስታወሻ አቀረቡ፡፡[30] በእሳቸው ግጥም ምትኩም የታገል ሰይፉ መሸሻ ግጥም ተሻሽሎ ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ እንዲዘመር ተመረጠ፡፡

ከዚህ በላይ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የታገል ሰይፉ ግጥም፣ ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ ደግሞ የሚሊዮን ደሣለኝ ግጥም ለሰንደቅ ዓላማ መዝሙርነት እንዴት እንደተመረጡ ተመልክተናል፡፡ ቀጥለን ደግሞ የኹለቱንም የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ይዘት እንተነትናለን፡፡ ትንተናችንንም ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀል እንዲዘመር በተመረጠው በታገል ሰይፉ ግጥም እንጀምራለን፡፡

## 4.2) በኢሕዲሪ መንግሥት የተመረጡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ይዘት ትንተና

ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ እንዲዘመር የተመረጠውን የታገል ሰይፉ መሻሻን ግጥም ይዘት ከመተንተናችን በፊት ለውድድር ያቀረቡትንና እንዲሻሻል የተባለውን ግጥም እንጠቅሳለን፡፡

[30] አሰፋ ገብረ ማርያም ባቀረቡት ማስታዎሻ እንደገለጹት በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በተደረገው ውድድር በእሳቸው የተደረሱት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ማሸነፋቸውን፣ መታተማቸውንና በአንባቢያን ዘንድ መታወቃቸውን ገልጸዋል፡፡ ማሻሻያውን ለመቀበል ያልፈለጉበት ምክንያትም ግጥሞቹ በቀረቡበት ጊዜ የነበረውን የኢትዮጵያ ኹኔታ የሚገልጹ፣ ነገር ግን፣ ከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ወዲኽ የተፈጠረውን የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኰኖሚያዊ ኹኔታዎች እንደማይገልጹ ካቀረቡት ደብዳቤ መረዳት ይቻላል፡፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ግጥሞችን ባቀረቡበት በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የነበረው የኢትዮጵያ ኹኔታ ከ፲፱፻፹ዎቹ የኢትዮጵያ ወቅታዊ ኹኔታ የተለየ ነበር፡፡ ከለውጦቹ መካከል፣፲፱፻፷፱ ዓ. ም. የሶማሊያ ወረራን ማሸነፍ፣ ኢትዮጵያ በኅበረተሰባዊነት የምትመራ መኾኑ መታወጁ፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ መመሥረቱ፣ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ተቃዋሚ ኀይሎች እንቅስቃሴ በርትቶ ለሀገር አንድነት ሥጋት መኾኑ፣ በሶቪየት ኅብረት ይመራ የነበረው የምሥራቁ ኀይል መዳከሙ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ የፈጠራ ግጥም በተፈጠረበት ይዘቱና ቅርጹ ሳይነካካና ሳይለወጥ መቀመጥ አለበት ብለው ማመናቸው ተጨማሪ ምክንያታቸው ነው፡፡ ከአወዳዳሪ ኰሚቴው ቃለ ጉባዔ መረዳት እንደሚቻለው አሰፋ ገብረ ማሪያም ምክንያታቸውን ገልጸው ማሻሻያውን አልቀበልም በማለት ለሥነጥባበትና ቲያትር መምሪያ ማስታወሻ አቅርበው ጥያቄአቸው ተቀባይነት በማግኘቱ አሸናፊ የነበረው ግጥማቸው ከውድድር እንዲወጣ ተደረገ፡፡

ቀጥሎም ግጥማቸው ምን ያኽል እንደተሻሻለ እንመረምራለን፡፡ ታገል ሰይፉ ለውድድር ያቀረቡት ግጥም የሚከተለው ነው፡፡[31]

የነጻነት አርማ - <u>የፍትሕ የህብረት</u>
<u>የእኩልነት ሚዛን</u> - የአንድነት መሠረት
<u>የህብረተሰባዊነት - የትግል ፋናችን</u>
<u>ትውለብለብ ዘላለም - ሰንደቅ አላ</u>ማችን
የሀገር ልምላሜ - <u>የወንዝ የተራራ</u> /1/
የሥልጣኔ ጎህ - <u>የተስፋችን ጮራ</u> /2/
<u>የደማችን ዋጋ</u> - የታሪክ <u>ውርሳችን</u> /3/
ትውለብለብ ዘላለም - ሰንደቅ አላማችን (አጽንኦት የታከለ)

ይኽ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ እንዲዘመር የተመረጠው የታገል ሰይፉ መሻሻ ግጥም ተመርጦ ከነበረው የአሰፋ ገብረ ማርያም ሰንደቅ ዓላማ ግጥም ጋር በቃላት አጠቃቀሙ፣ በሐረግ አመጣጠኑና አከፋፈሉ፣ በተምሳሌት አፈጣጠሩ፣ እንዲሁም በአዝማቹ ይመሳሰላል፡፡[32] በተጨማሪም፣ ቁጥሮቹ የሚወክሏቸው የሰንደቅ ዓላማ ቀለማት አንድ ዓይነት ናቸው፡፡ ቁጥሮቹ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ የሰንደቅ ዓላማው ቀለማትን እንደሚወክሉ አሰፋ ገብረ ማርያም ከግጥሙ ግርጌ ገልጸዋል፡፡ በታገል ሰይፉ ከሥንኞቹ ፊት ለፊት የጻፏቸው ቁጥሮች ከላይ ወደ ታች ሲቆጠሩ አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማትን ይወክላሉ፡፡ ይኽም አሰፋ ገብረማርያም በቁጥሮቹ አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ በማለት ከገለጿቸው የሰንደቅ ዓላማ ቀለማት ጋር ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል፡፡ የታገል ሰይፉ ግጥም የአሰፋን ግጥም እንዲተካ የተደረገበት ምክንያት በተመሳሳይነቱ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የታገል ሰይፉ መሻሻ ግጥም እንደሚከተለው እንዲሻሻል ተደርጓል (ከሥራቸው የተሠመረባቸው ሐረጋት እና ሥንኝ በሌላ የተተኩ ናቸው)፡፡

---

[31]በሐረጋትና በሥንኞች የተሰመረው ግጥሙ ሲሻሻል በሌሎች ሐረጋትና ሥንኞች የተተኩ መኾናቸውን አንባቢ በቀላሉ እንዲረዳ በአጥኚው የተጨመሩ ናቸው፡፡ በዐምስተኛው፣ በስድስተኛውና በሰባተኛው ሥንኞች መጨረሻ በቅንፍ የተጻፉት ቁጥሮች የደራሲው ናቸው፡፡

[32]ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ ተሻሽሎ እንዲዘመር ተመርጦ የነበረው የአሰፋ ገብረ ማርያም (1971፤ 56) ግጥም የሚከተለው ነው፡፡ግጥሙ ታገል ሰይፉ መሻሻ ካቀረቡት ግጥም ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ያንድነት የህብረት- የትግላችን ዐርማ
የድል የጀግንነት - የነጻነት ግርማ
የህብረሰባዊነት - መሪ ኮከባችን
ትውለብለብ ዘላለም - ሰንደቅ አላማችን!

ያገራችን ውበት - የወንዝ የተራራ..... /1/
የተስፋችን ብርሃን - የማለዳ ጮራ.... /2/
የታሪክ ቅርሳችን - የደም ያጥንታችን... /3/
ትውለብለብ ዘላለም - ሰንደቅ አላማችን
(1) አረንጓዴ (2) ቢጫ (3) ቀይ

አረንጓዴ ብጫ፣ ቀይ ቀለማት ህብረት፣
የነጻነት አርማ - የአንድነት መሠረት፡፡
የሀገር ልምላሜ - የተስፋ የሥራ፣
የሥልጣኔ ጎህ - የአዲስ ሕይወት ጮራ፣
የእኛነታችን ውርስ -የታሪክ ቅርሳችን፣
ትውለብለብ ዘላለም - ሰንደቅ ዓላማችን፡፡

(አጽንኦት የታከለ)

ከዚህ በላይ እንደሚነበበው ታገል ሰይፉ መሻሻ የተለያዩ ሐረጋትን በማጣመር በአዳዲስ ሐረጋት በመተካት፣ አንድ ሥንኝ በመጨመር እና/ወይም በመቀነስ ለውድድር ያቀረቡትን ግጥም አሻሽለውታል፡፡ ለምሳሌ፣ የተሻሻለው ግጥም የመጀመሪያ ሥንኝ "የነጻነት አርማ" የሚለው የመጀመሪያ ሐረግ ከኹለተኛው ሥንኝ ኹለተኛ ሐረግ "የአንድነት መሠረት" ከሚለው ጋር ተጣምሮ አንድ ሥንኝ ኾኗል፡፡ እንደዚሁም፣ በሦስተኛው፣ በአራተኛውና በዐምስተኛው ሥንኞች ከሥራቸው የተሰመረባቸው ሐረጋት በሌላ ተተክተዋል፡፡ ለውድድር በቀረበው ግጥም የመጀመሪያው ሥንኝ ኹለተኛ ሐረግ እና የመጀመሪያ ሐረግ እንዲሁም አራተኛው ሥንኝ ተቀንሰዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቀለማትን የሚጠራ አንድ ሥንኝ ተጨምሯል፡፡ በዐምስተኛው፣ በስድስተኛውና በሰባተኛው ሥንኝ መጨረሻ የተጨመሩት ቁጥሮች ቀርተዋል፡፡ በአጠቃላይ የሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ እንዲዘመር ለውድድር ከቀረበው ባለ ዐሥራ ስድስት ሐረጋት ግጥም ዐሥሩ ተቀይረዋል፡፡ ለውድድር የቀረበው ግጥም ኹለት ሦስተኛው ተሸሽሏል ወይም ተለውጧል፡፡ ለውድድር የሚቀርበው ግጥም ከ፰ መስመሮች (የሥንኞች) እንዳይበልጥ በማወዳደሪያ መስፈርትነት የተገለጸ ቢኾንም፣ ግጥሙ እንዲሻሻል ሲደረግ የመስመሮቹ ብዛት ስድስት ብቻ እንዲኾኑ ተደርጓል፡፡

የግጥሙ ይዘት የሰንደቅ ዓላማችንን ትርጉም የሚያንፀባርቅ እንዲኾን በማወዳደሪያ መስፈርቱ የተገለጸው በሦስተኛው፣ በአራተኛውና በዐምስተኛው ሥንኞች በቅደም ተከተል (ከላይ ወደ ታች) ተንጸባርቋል፡፡ ግጥሙ የቀረበባቸው የቃላት ትርጉም አሻሚነት የሌላቸው በማንኛውም የዕድሜ ክልል የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ኹሉ በቀላሉ ሊረዳቸውና ሊያስታውሳቸው ይችላል፡፡ የተሻሻለው የታገል ሰይፉ መሻሻ ግጥም በመስፈርትነት ለተወዳዳሪዎች በማስታወቂያው ላይ የተገለጹትን ይዘቶች አሚልቷል፡፡

የተሻሻለው የሰንደቅ ዓላማ ግጥም የመጀመሪያው ሥንኝ የሰንደቅ ዓላማውን ቀለማት ከላይ ወደታች በቅደም ተከተል ይጠራል፡፡ የመጨረሻው ሥንኝም ሰንደቅ ዓላማው ዘላለም በነጻነት እንዲውለበለብ ይመኛል፡፡ ግጥሙ ከቀረበባቸው ቃላት ልምላሜ፣ የአረንጓዴው፤ ተስፋ የቢጫው የሰንደቅ ዓላማ ቀለማት ትርጉም እንደሆኑ በዐዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፹ አንቀጽ ፫ ከተሰጠው ድንጋጌ እንረዳለን፡፡ ነጻነት የሚለው ቃል በኢትዮጵያ ላይ በተለያዩ ጊዜያት የውጭ ወራሪዎች የ፲፱፻፷፱ ዓ. ም. የሶማሊያ መንግሥት የፈጸመውን ጥቃት ጨምሮ ለመመከት የተከፈለውን መሥዋዕትነት፣ በሀገር ውስጥ አርሶ አደሩ የምርቱ ባለቤት እንዲኾን፣ የፋብሪካ

ሠራተኛው ከጉልበት ብዝበዛ ነጻ እንዲወጣ የሠራተኛ ዐዋጅ ለማወጅ የተደረገውን ትግል፣ የደም፣ የአካል፣ የሕይወት ዋጋ መከፈሉን ይዘክራል፡፡ ከዚኽም፣ ነጻነት የመሥዋዕትነት ውጤት መኾኑን እንረዳለን፡፡ መሥዋዕትነቱም የቀዩ የሰንደቅ ዓላማ ቀለም ምሳሌ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ “የነጻነት አርማ” በሚለው ሐረግ ነጻነት የሚለው ቃል በሌላ ሰው ቁጥጥር ሥር አለመኾን፣ ራስን በራስ ማስተዳደርን ይገልጻል፡፡ በ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. በተካኼደው ለውጥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢኰኖሚና የፖለቲካ ነጻነት አግኝቷል ብሎ ያምናል፡፡ የገጠር መሬት ዐዋጅ መታወጅ “መሬት ላራሹ” የሚለውን ጥያቄ የመለሰ፣ በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ የነበረውን የመሬት ሥሪት የለወጠ፣ ገበሬው የምርቱ ባለቤት የኾነበት፣ በከተማ የፋብሪካ ሠራተኛው ሙብት የሚያስከበር ሕግ መውጣቱ ምቹ የሥራ ኹኔታ መፈጠሩን ይገልጻል፡፡ ስለኾነም፣ የአርሶ አደሩና የወዝአደሩ ሕይወት የተሻለ እንዲኾን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነቱ መለያው ምልክቱ መታወቂያው ኾኗል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያጋጥሙት የነበሩት ችግሮች በተካኼደው የሥርዓት ለውጥ በመፈታታቸው የሕዝብ አንድነት ጎልብቷል ተብሎ መታመኑን “የአንድነት መሠረት” በሚለው ሐረግ ተገልጿል፡፡ በምሥራቅ ኢትዮጵያ ድንበር ተሻግሮ የወረራ ተግባር የፈጸመውና የግዛት ይገባኛል ጥያቄ የነበረው የሶማሌ መንግሥት ወራሪ ኀይል የተደመሰሰበትን ጊዜ ያስታውሳል፡፡ በሌላ በኩል፣ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የመገንጠል ዓላማ ይዘው ይንቀሳቀሱ ለነበሩት ኀይሎች የተቃውሞ መልእክትም ተላልፎበታል፡፡

በመዝሙሩ የሀገሪቱ የኢኰኖሚ መሠረት የነበረው ግብርና እየጎለበተ፣ እየተሻለና እያደገ መኾኑን “የሀገር ልምላሜ” በሚለው ሐረግ ተገልጿል፡፡ “አረንጓዴው ዘመቻ” በሚል መሪ ሐሳብ መንግሥት የኢኰኖሚ ለውጥ ለማምጣት ያደረገው እንቅስቃሴ ለግብርናው ትኩረት መስጠቱ አረንጓዴው የኢኰኖሚ ዕድገት ለሕዝቡ የተስፋ ስንቅን ይሰጣል፡፡ ኢኰኖሚው የሚጎለብተው ሥራን መርኅ ያደረገ መንግሥትና ኅብረተሰብ ሲኖር ነው፡፡ “የተስፋ የሥራ” የሚለው ሐረግ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ሥራን መርኅ ማድረጉን፣ የሕዝቡ መሠረታዊ ፍላጎቶች የሚሟሉት የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ክፍሎች በመለወጥ አዳዲስ ቁሶች (ነገሮች) የሚፈጥርበት የሚያመርትበት ዓላማ ተኰር ተግባር የሚከተል መኾኑን ያስረዳል፡፡ ይኸም መንግሥት ይከተለው በነበረው የኅብረተሰባዊነት ርዕዮተ ዓለም “ከእያንዳንዱ እንደችሎታው፣ ለእያንዳንዱ እንደሥራው” የሚለውን መርኅ ተግባራዊ የሚያደርግ ሥርዓት እያለመ መኾኑን ይጠቁማል፡፡ ወዝ አደሩ ከብዝበዛ ነጻ የሚኾነው የሥራ ክቡርነትን በማስተማርና የኅብረተሰባዊነት ሥርዓትን በመገንባት መኾኑን የተጠቀሰው የመዝሙሩ ሐረግ ያስረዳል፡፡ ከታሪካዊ ዐውዱ መረዳት እንደሚቻለውም የማምረቻ መሣሪያዎችን በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ የኅብረተሰባዊነት ሥርዓት ግንባታ ኺደት ተደርጎ ይቆጠር ነበር፡፡

በ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. የተካኼደው የሥርዓት ለውጥ፣ ያስገኘውንና ወደፊትም ያስገኛል ተብሎ የሚጠበቀውን ሥልጣኔና የተሻሻለ የአኗኗር ኹኔታ “የሥልጣኔ ጎህ፣ የአዲስ ሕይወት ጮራ” የሚለው ሥንኝ ይገልጻል፡፡ ጎህ በደንብ ከመንጋቱ በፊት የሚታይ ብርሃን ነው፡፡ ጨለማን እያሸነፈ የሚመጣው ብርሃን የመንጋትን፣ አካባቢ በብርሃን የመሞላትን እውነትነት፣ አይቀሬነት፣

የሚፈለገውን ሥራ ለማከናወን የሚቻልበት ኹኔታ መፈጠሩን ያበሥራል፡፡ ብሥራቱ ደግሞ የምሥራች፣ መልካም ዜና ነው፡፡ ኅህ ከሥልጣኔ ጋር ተጣምሮ በማኅበራዊ ሕይወት ሲተረጎም ከኋላ ቀርነት የመላቀቅ እርምጃን፣ የዕድገትን ጅማሬ፣ የዘመናዊነትንና የመሻሻልን ምዕራፍ መገለጥን በቅርብ ጊዜ የዕድገት ውጤት መኖሩን ይጠቁማል፡፡ ለውጡ ያስገኘው ሥልጣኔ ከጅምርነት ያላላፈ፣ ወደፊት ግን እውን እንደሚኾን በደንብ ከመንጋቱ በፊት በሚታይ ብርሃን ተመስሏል፡፡ ለውጡ ዐዲስ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማኅበራዊ ግንኙነት ማስግኘቱንና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተሻለ የሕይወት ለውጥ ያመጣል ተብሎ ተስፋ መደረጉን ያስረዳል፡፡ ለውጡ ከተስፋ ወደ ተጨባጭ ተግባር መሸጋገሩን "የአዲስ ሕይወት ጮራ" በሚለው ሐረግ ተገልጿል፡፡ ዐዲስ የሚለው የነበረውን የሻረ፣ በአሸናፊነት የራሱን ቦታ የፈጠረ፣ አሮጌውን የተካ ማለት ነው፡፡ አሮጌው ከለውጥ በፊት የነበረው፣ ዐዲሱ ደግሞ ከለውጥ በኋላ የተመሠረተው ሥርዓት ነው፡፡ "ጮራ" የሚለው ቃል በተምሳሌትነቱ የጠዋት ብርሃንን ይወክላል፡፡ የጠዋት ብርሃን ደግሞ በአንድ ሙሉ ቀን የሚገኘው ብርሃን የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው፡፡ ጨለማን በመሻገር የሚገኘው ብርሃን እፎይታን ይፈጥራል፣ ተስፋን ያለመልማል፣ ደስታን ይሰጣል፡፡ የጠዋት ጮራ ተፈጥሮአዊ ቀለሙ ቢጫ ነው፡፡ ቢጫ ቀለም ደግሞ "የተስፋ፣ የፍትሕ፣ የእኩልነትና የዕውቀት ምልክት" መኾኑ በሰንደቅ ዓላማ ዐዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፹ አንቀጽ ፫(ለ) ተደንግጓል፡፡

የመጨረሻዎቹ ኹለት ሥንኞች የሰንደቅ ዓላማዋን ታሪካዊነት፣ ውርስነት፣ ቅርስነትና የነጻነት ተስፋነት ይገልጻሉ፡፡ "እኛ" በሚል አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም የተጠሩት የሰንደቅ ዓላማው መዝሙር ዘማሪዎች ኢትዮጵያውያን በጠቅላላ ናቸው፡፡ ከተውላጠ ስሙ የወጣው "እኛነት" የሚገልጸው የእኛ የኢትዮጵያውያን ማንነት፣ በነጻነት የመኖር ውርስነት የተገኘበት መታወቂያነት ነው፡፡ ውርስ የሚለው ቃልም አውራሽንና ወራሽን እንዲሁም የሚወረስ ነገር መኖርን ይገልጻል፡፡ አውራሾቹ አባቶቻችንና እናቶቻችን ሲኾኑ ወራሾቹ ደግሞ እኛ መዝሙሩን በነጻነት የምንዘምረው ልጆቻቸው ነን፡፡ ያወረሱንም ነጻነትንና የነጻነት ትእምርት የኾነውን ሰንደቅ ዓላማ ነው፡፡ የእኛ አባቶችና እናቶች ያወረሱንም የነጻነት ማንነታችን ነው፡፡ የታሪካችን መሠረት፣ የዜግነታችን ክብር፣ የነጻነታችን ብርሃን፣ የሉዓላዊታችንና የባህላችን ዋስትና ምልክት ለኾነችው ሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ቆመን ለምንዘምረው ኢትዮጵያውያን ኹሉ በውርስነት ከቀደመው ትውልድ ያገኘነው ቅርሳችን ነው፡፡ "የእኛነታችን ውርስ የታሪክ ቅርሳችን" የሚለው ሥንኝ የሚገልጸው ይኸንኑ ነው፡፡ በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈጸመን ያለፈ የኢትዮጵያውያን (ሕዝብ፣ መንግሥታትና መሪዎች) ድርጊት የሚገልጸው ታሪካችን ከሰንደቅ ዓላማችን በነጻነት ከመውለብለብ ጋር ቀጥታ የተሳሰረ ነው፡፡ ሰንደቅ ዓላማችን በቅርስነቷ ለትውልድ የተላለፈችውና የምትተላለፈው የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪክና ባህል በማንጸባረቅ ነው፡ ፡ የተጠቀሱትን ታሪካዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ቁም ነገሮች ለሚገልጸው፣ ለሚወክለው ሰንደቅ ዓላማችን ፍቅር ሰጥተንና አክብረን ዘወትር ስትውለበለብ ድምጻችንን ከፍ አድርገን መዘመራችን ለእኛነታችን ክብር መስጠት ነው፡፡ የሰንደቅ ዓላማችን ዘላለም መውለብለብ የማንነታችን፣ የታሪካችንና የቅርሳችን መቀጠል ነው፡፡ የመዝሙሩ ግጥም የሚነግረው ይኸንኑ ነው፡፡

ከዚኽ በላይ የተመለከትነው በታገል ሰይፉ መሻሻ የተደረሰው ጠዋት የሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የሚዘመረው መዝሙር ሰንደቅ ዓላማችንን ደጋግሞ ይጠራል፡፡ ለሰንደቅ ዓላማው ቀለማት ትርጉም ይሰጣል፡፡ ሰንደቅ ዓላማችን የማንነታችን ውርስ፣ የታሪካችን አሻራ ቅርሳችን መኾኗን ያስረዳል፡፡ ነጻነታችን ተከብሮ፣ ሉዓላዊነታችን ታውቆ በእኛነታችን እንድንኖር ሰንደቅ ዓላማችን በነጻነት እንድትውለበለብ ይመኛል፡፡

ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ እንዲዘመር በተመረጠው የሚሊዮን ደሣለኝ ግጥም ምን ምን ይዘት እንደተንፀባረቀ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ ቀድመን ለውድድር የቀረበው፣ ቀጥለን ደግሞ የተሻሻለውን ግጥም በመጥቀስ እንመረምራለን፡፡

የሚሊዮን ደሣለኝ ግጥም ለውድድር የቀረበው ጠዋት እንዲዘመር ነበር፡፡ በርዕዮተ ዓለም መምሪያ የተመረጠው ማሻሻያ ተደርጎበት ምሽት ሰንደቅ ዓለማ ሲወርድ እንዲዘመር ነው፡፡ ሰንደቅ ዓላማው ሲወርድ ተሻሽሎ እንዲዘመር የተመረጠው የሚሊዮን ደሣለኝ ባለ ስምንት መስመር ግጥም የሚከተለው ነው፤

የጀግኖች <u>ደም አጥንት የአደራ ቅርሳችን</u>
የዘመናት <u>ሞገስ ክብር መመኪያችን</u>
<u>የህብረት</u> የእኩልነት <u>የአንድነት ውርሳችን</u>
<u>የዐርበኝነት ሰንደቅ የሥራ ዓላማችን</u>
<u>ለክብር ለዝናሽ በአንድነት ቆመናል</u>
<u>በሥራም ለማደግ ቆርጠን ተነሥተናል</u>
<u>ታሪክሽን</u> ልንጠብቅ ቃል ኪዳን ገብተናል
በደም በአጥንታችን ዋስትናሽ ኾነናል፡፡
(አጽንኦት የታከለ)

ከዚኽ በላይ እንደተመለከተው የተሠመረባቸው ሐረጋትና ሥንኞች የተሻሻሉ ወይም የቀሩ ናቸው፡፡ ግጥሙ ከቀረበባቸው ሠላሳ አራት ቃላት መካከል ዐሥራ ዐምሥቱ እንዲለወጡ፣ ስምንቱ ደግሞ እንዲቀየሩ ተደርገዋል፡፡ የተለወጡትና እንዲቀሩ የተደረጉት ቃላት ድምር ሐያ ሦስት ነው፡፡ ከዚኽም፣ ለውድድር የቀረበው የሚሊዮን ደሣለኝ ግጥም ከኹለት እጅ በላይ ቃላቱ መቀየራቸውን ወይም መቅረታቸውን እንረዳለን፡፡ የግጥሙ የሥንኝ ብዛትም ከስምንት ወደ ስድስት ዝቅ እንዲል ተደርጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የጀግኖች <u>ተጋድሎ የአባቶች አደራ</u>፣
የዘመናት <u>ፈለግ የታሪክ አሻራ</u>፡፡
<u>የሙብ</u>ት የኩልነት <u>የፍትሕ አርማችን</u>፣
<u>የናት አገር ፍቅር ያንድነት ፋናችን</u>፡፡
<u>ክብርሽን</u> ልንጠብቅ ቃል ኪዳን ገብተናል፣
በደም በአጥንታችን ዋስትናሽ ሆነናል፡፡
(አጽንኦት የታከለ)

ከዚኽ በላይ እንደተመለከተው ከሥራቸው የተሠመረባቸው ዐሥራ ዐምስት ቃላት የተሻሻሉ ናቸው። ግጥሙ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በቀጥታ በስም አይጠራም። ይኹን እንጂ በእያንዳንዱ ሥንኝ በተዘዋዋሪ መንገድ በአነስታይ ጾታ ኢትዮጵያንም፣ የኢትጵያ ሰንደቅ ዓላማም መጠራታቸውን መረዳት ይቻላል። ግጥሙ ተመሳሳይይ ወይም ተቀራራቢ ፍች ያላቸውን ቃላት በመጠቀም የቀረበ ለመኾኑ (ጀግና፣ ተጋዳይ)፣ (ፈለግ፣ አሻራ) (ሙብት፣ ፍትሕ) የሚሉት በማስረጃነት ይጠቀሳሉ። ግጥሙ ያለፈውን የጀግኖች የተጋድሎ ታሪክ በመዘከር ትውልዱ የአባቶቹን አደራ እንዲቀበል፣ ሰንደቅ ዓላማውን እንዲያስከብር ያስተምራል፤ ይቀሰቅሳል። የኢትዮጵያን ነጻነትና ሰንደቅ ዓላማ ለመጠበቅ ቃል የገቡት፣ አደራ የተቀበሉት ተተኪዎቹ ልጆች ናቸው።

"የጀግኖች ተጋድሎ የአባቶች አደራ" የሚለው ሥንኝ ጀግኖች የሚለው ብዙ ቁጥር አመልካች ቃል የሚገልጸው ለሀገራቸው ለወገናቸው መሥዋዕትነት የከፈሉ፣ መልካም ተግባሮች ያከናወኑ፣ ወኔ ድፍረት በሚጠይቁ ኹኔታዎች ላይ ጀብዱ ሠርተው የታሪክ ግዴታቸውን የተወጡ ኢትዮጵያውያንን ነው። ጀግንነታቸውም የተጋድሏቸው ውጤት ነው። የኢትዮጵያውያን ተጋድሎ የሚለው ቅጽልም ዐርበኞች ሕይወታቸውን አሳልፈው በመሥጠት የሀገራቸውን ሉዓላዊነት፣ ነጻነትና የሰንደቅ ዓላማቸውን ክብር ለመጠበቅ ቆርጠውና ወስነው ከፍተኛ ትግል ማድረጋቸውን ይገልጻል። "የአባቶች አደራ"[33] በሚለው ሐረግ አባቶች ለልጆቻቸው አደራ መስጠታቸው ልጆቻቸውም አደራ መቀበላቸው ተነግሯ.ል። አባቶች ከፍተኛ ትግል አድርገው፣ መሥዋዕትነት ከፍለው የኢትዮጵያን ነጻነት እንዳስከበሩ ኹሉ፣ ልጆቻቸውም ተመሳሳይ ተግባር በመፈጸም ኢትዮጵያን እንዲጠብቁ የጠበቀ ተማጽእኖ፣ ልመና እና ማሳሰቢያ አቅርበዋል፤ አደራ ብለዋል። አባቶች የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ ነጻነት፣ ሰንደቅ ዓላማ እንዲጠብቁና እንዲያስከብሩ ለልጆቻቸው አደራ የሰጡት ራሳቸው ፈጽመውና ተግብረው በማሳየት ወይም በመንገር፣ አርአያ፣ ምሳሌ በመኾን ነው። ልጆች የሀገርን ነጻነት የመጠበቅ ኀላፊነት አደራ የተቀበሉት፣ አባቶቻቸው ለብዙ ዓመታት የፈጸሙትን የጀግንነት ተጋድሎ በዐይናቸው ዐይተው ወይም በጆሮአቸው ሰምተው ነው።

በኹለተኛው ሥንኝ እንደተገለጸው፣ የአባቶች የጀግንነት ተጋድሏቸው የረጅም ጊዜ ታሪካቸው የታተመበት፣ አደራውን ለተቀበሉት ልጆቻቸው በአርአያነት፣ በምሳሌነት የሚጠቀስ፣ ሊከተሉት የሚገባ ተግባር ነው። የአባቶች ጀግንነት በታሪክ አሻራነቱ፣ በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈጸሙትን፣ የአለፈ ድርጊታቸውን ይዘረዝራል። በአሻራነቱም አባቶች በጀግንነት የተጓዙበትን፣ ያለፉበትን የትግል ውጣ ውረድ ያሳያል፤ ያስረዳል። ይኸም በተለያዩ ጊዜያት የኢትዮጵያን ነጻነትና የሕዝቡን ክብር ለመጠበቅ የተከፈለውን መሥዋዕትነትና የተገኘውን ድል ትውልዱ እንዲመረምር ያነሣሣል። ትውልዱ በታሪኩ የመኩራቱ ምክንያትና መሠረት ያባቶቹ የተጋድሎ ውጤት መኾኑን እንዲያጤን ይጋብዛል። ከዚኽም በላይ መዝሙሩ የቀረበለት ትውልድ የአባቶቹን አርአያ

[33] ሐረጉ አባቶችን ብቻ በመጥራቱ የሴቶችን ሚና የረሳ ይመስላል። ይኹን እንጂ የኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ ፴፭ (፩) እና አንቀጽ ፴፮ (፩-፫) ስለሴቶች እኩልነት ተደንግጓል። ከቀበሌ እስከ ሀገር አቀፍ የራሳቸውን ማኅበር እንዲያቋቁሙ መደረጉም መንግሥት ለሴቶች እኩልነት ያደረገውን ጥረት ይገልጻል።

የመከተል፣ አደራቸውን የመፈጸም፣ ማሳሰቢያቸውን የማስታወስ፣ የጀግንነት ታሪካቸውን ለመድገም የመትጋት ኀላፊነት እንዳለበት የመዝሙሩ የመጀመሪያዎቹ ኹለት ሥንኞች ይሰብካሉ፡፡ የኹለቱ ሥንኞች ትኩረት በጀግንነት ታሪክ ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያውያን የጀግንነት ታሪክም የነጻነትና የሉዓላዊነት ታሪክ ነው፡፡

የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሩ የ፲፱፻፰፯ ዓ. ም. ለውጥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያስገኘው መብት እኩልነትና ፍትሕ የሚከበረው፣ የሀገር ፍቅርና የአንድነት ስሜት የሚጸናው ሰንደቅ ዓላማዋ በነጻነት ትእምርትነት በክብር ስትውለበለብ መኾኑን በሚከተሉት ሥንኞች ይገልጻሉ፡፡

<u>የመብ</u>ት የኩልነት <u>የፍትሕ አርማችን</u>፣
<u>የናት አገር ፍቅር ያንድነት ፋናችን</u>፡፡ (አጽንኦት የታከለ)

ከዚኽ በላይ እንደተገለጸው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰብአዊነቱ ያለው ወይም በሕግ ያገኘው መብቱ በሌላ ሰው ወይም አካል የማይደፈርበት ወይም የማይነጠቅበት፣ የሚከበርበት፤ በሀብት፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በሃይማኖት ልዩነት የማይደረግበት፣ በሕግ መሠረት የሚዳኝበትና ትክክለኛ ፍርድ፣ ብያኔ የሚያገኝበት ሁኔታ የሚኖረው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ስትከበር፣ በነጻነት ስትውለበለብ ነው፡፡ ሰንደቅ ዓላማዋ መብት የሚከበርባት፣ ፍትሕ የሚኘኝባት፣ የማንነት መለያ፣ መታወቂያ ናት ማለት ነው፡፡

በመዝሙሩ ሰንደቅ ዓላማዋ የመብት፣ የእኩልነትና የፍትሕ መለያ፣ ምልክት ናት፡፡ ይኽም፣ በተዘዋዋሪ መንገድ ከ፲፱፻፰፯ ዓ. ም. የሥርዓት ለውጡ በፊት መብት በመገፈፍ፣ ፍትሕ በማጉደልና እኩልነት በመንፈግ ይከሰስ የነበረው ሥርዓት መለወጡን ይነግራል፡፡ ከለውጥ በፊት የውጭ ጠላትን በመከላከል ሰንደቅ ዓላማዋ እንድትውለበለብ ቢደረግም መብት ተከብሯል፤ እኩልነት ተረጋግጧል፣ ፍትሕ ሰፍኗል ተብሎ አይታመንም ነበር፡፡ በሌላ በኩል፣ መዝሙሩ ለውጡ "አስገኝቷል" ተብሎ በመንግሥት የሚታመነውን መብት መከበር፣ ፍትሕ መስፈን፣ እኩልነት መንገሥና መረጋገጥ ያስረዳል፡፡ ይኽም በየኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ረፑብሊክ ሕገ መንግሥት መቅድም ገጽ ፲፩ "የዘውድ አገዛዝን በማስወገድና በተከታታይ ልዩ ልዩ አብዮታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ለአዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት መሠረት ጣለ፡፡ የገጠር መሬት፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች፣ ታላላቅ የማምረቻ የማከፋፈያና አገልግሎት ሰጭ ተቋሞች የሕዝብ ሀብት ሆነዋል፡፡ ለብሔረሰብ፣ ለጾታና ለሃይማኖት እኩልነት ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፡፡" በማለት ተገልጿል፡፡ የሠራተኛው መብት ለማስከበርም የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር /፷፬፲፱፻፷፯ መታወጁ ይታወቃል፡፡

የሀገር ፍቅር፣ የአንድነት ቀናኢነትና ለሰንደቅ ዓላማዋ ክብር መስጠት አስፈላጊ መኾኑ በመዝሙሩ የተገለጸው፣ ታሪክን መሠረት በማድረግ፣ የወቅቱን የመንግሥት ትኩረት በማገናዘብ፣ የወደፊቱን ተመሳሳይ የሀገር ችግር በማጤን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ላይ በተደጋጋሚ በውጭ ጠላት የተሰነዘረውን ጥቃት መመከት የተቻለው በጠንካራ የሀገር ፍቅር ስሜትና በአንድነት ነው፡፡ በወቅቱ የሀገር አንድነት ሥጋት ተደርገው ከሚቆጠሩት (ከሚታዩት) ኀይሎች (ሕዝባዊ ግንባር

ሓርነት ኤርትራ (ሻዕብያ)፣ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት)፣ ተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ (ጀብሃ)፣ የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር (ኦነግ)፣ የኦጋዴን ነጻነት ግንባር፣ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር፣ እና የሲዳማ አርነት ንቅናቄ) ጋር ይካኼድ በነበረው ጦርነት የኢትዮጵያ ሠራዊት መሥዋዕትነት ይከፍል የነበረው፣ ፍቅሩንና አንድነቱን ያጸና የነበረው በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ፋናነት ነበር፡፡ የተጠቀሱት ተፋላሚ ኀይሎች አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያን በቅኝ ገዥነት የፈረጁ፣ የራሳቸው ሉዓላዊነት የነበራቸው አድርገው የሚያምኑ፣ በውጭ መንግሥታት የሚረዱ[34] ነበሩ፡፡ የእነዚኽን ኀይሎች ጥቃት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚከላከለው ፍቅሩን አጽንቶ፣ አንድነቱን ጠብቆ፣ በሰንደቅ ዓላማው ተመርቶ እንዲኾን መዝሙሩ ይቀሰቅሳል፡፡ ምንጊዜም የኢትዮጵያውያን የሀገር ፍቅር ስሜትና የአንድነት መሠረት የሚጸናውም የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ፋናቸው በማድረግ እንደኾነ መዝሙሩ ያስተምራል፡፡

ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸውና ለሰንደቅ ዓላማቸው ልእልና፣ ገናናነት፣ ታዋቂነትና ቀጣይነት እስከ ምን ድረስ ተስፋ እንደሰጡ የሚከተሉት ሥንኞች ያስረዳሉ፡፡

> <u>ክብርሽን</u> ልንጠብቅ ቃል ኪዳን ገብተናል፣
> በደም በአጥንታችን ዋስትናሽ ሆነናል፡፡ (አጽንኦት የታከለ)

በሥንኞቹ እንደተገለጸው ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸውና ለሰንደቅ ዓላማቸው ባላቸው ጽኑ ፍቅር ደማቸውን በማፍሰስ፣ አጥንታቸውን በመከስከስ ሊጠብቋቸው ቃል ኪዳን ይገባሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸውና ለሰንደቅ ዓላማቸው ደማቸውን ለማፍሰስ፣ አጥንታቸውን ለመከስከስ ዋስትና መስጠታቸው፣ የሰጡትን ተስፋ አስተማማኝነትና እርግጠኛነት ይገልጻል፡፡ ለሰንደቅ ዓላማቸው፣ ለሀገራቸው ተስፋ የሰጡት፣ ቃል ኪዳን የገቡት ኢትዮጵያውያን ሰውኛ ዘይቤን በመጠቀም ነው፡፡ ሀገራቸው ኢትዮጵያን፣ ሰንደቅ ዓላማቸውን "አንቺ" በሚል ኹለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር በስም ምትክ በሚገባ ተውላጠ ስም ጠርተዋታል፡፡ ኢትዮጵያ ልጆቿ ሉዓላዊነቷን ለማስከብር፣ ነጻነቷን ለመጠበቅ፣ ክብሯን ለማስቀጠል የገሯትን የምትሰማ ተደርጋ ተገልጻለች፡፡ ይኽም በመዝሙሩ የተገባው ቃል ኪዳን ለዘማሪው ወይም ለተከታዩ ትውልድ ስሜት ቅርበት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

ለማጠቃለል በምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ እንዲዘመር የተመረጠው መዝሙር ባለፈ ጊዜ፣ በወቅቱ ሁኔታና ወደፊት ይፈጸማል ተብሎ በሚታሰብ ጉዳይ ላይ ያተኩራል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ኹለት ሥንኞች ታሪክን መሠረት ባደረገ የጀግንነት፣ የተጋድሎ ጉዳይ ላይ ያተኩራሉ፡፡ በሦስተኛውና አራተኛው ሥንኞች ሰንደቅ ዓላማው የኢትዮጵያ ሕዝብ መብት፣ እኩልነት፣ ፍትሕና አንድነት ትእምርት መኾኑን ይገልጻሉ፡፡ የመጨረሻዎቹ ኹለት ሥንኞች ደግሞ ተከታዩ ትውልድ ወደፊት ትኩረት ሊያደርግበት የሚገባውን ነጻነትንና ሉዓላዊነትን የመጠበቅና የማስከበርን ጉዳይ አጽንኦት ይሰጣሉ፡፡

---

[34] ፍቅረ ሥላሴ ወግደረስ (2006) <u>እኛና አብዮቱ</u> በሚለው መጽሐፋቸው ለኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኀይሎች ድጋፍ ያደርጉ የነበሩ ሀገሮችን ስም ዘርዝረዋል፡፡

## 5) ማጠቃለያ

የኢጣልያ ፋሽስት ወራሪ በጦር በዐርበኞች ተጋድሎና በእንግሊዝ ጦር ድጋፍ ከኢትዮጵያ ለቆ ወጣ፡፡ በስደት የነበሩት ንጉሠ ነገሥትና ዐርበኞች አዲስ አበባ ገቡ፡፡ በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. አንዱ ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ፣ ሌላኛው ደግሞ ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የሚዘመሩ ኹለት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች በየፍትሔ ንጉሤ ተደረሱ፡፡ በሙዚቃ እሸቴ መኰንን አቀናበሯቸው፡፡ በኹለቱም የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ጉልቶ የተገለጸው የዐርበኞች ተጋድሎ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈሉት መሥዋዕትነትና ያስገኙት ድል ነው፡፡ መዝሙሮቹ የተደረሱት የኢትዮጵያ ሕዝብ የዜግነቱ ኩራት፣ የነጻነቱና የሉዓላዊነቱ ምልክት፣ የታሪኩ መሠረትና የባህሉ መገለጫ የኾነችውን ሰንደቅ ዓላማ ክብርና ፍቅር ለመግለጽ ነው፡፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የሕዝቡ ልዕልና፣ ገናናነትና ታዋቂነት መገለጫና መታወቂያ ትእምርት የኾነውን ሰንደቅ ዓላማ ክብር ለመዋረድ የሚያስቡና የሚሞክሩ የውጭ ጠላቶችን የሚከላከሉት፣ የሚመክቱት፣ ንጉሠ ነገሥቱና ዐርበኞች መኾናቸውን ይገልጻሉ፡፡

የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ እያንዳንዱ ዜጋ የሀገር ፍቅሩን፣ ለነጻነቱና ለሉዓላዊነቱ ያለውን ቀናኢነት፣ ለሰንደቅ ዓላማው የሚሰጠውን አክብሮት እንዲገልጽ፣ ተተኪው ትውልድ የሀገር ፍቅር ስሜት እንዲያዳብር፣ የንጉሠ ነገሥቱን የሀገር መሪነት፣ የዐርበኞችን ተጋድሎ እንዲረዳ የሚያደርጉ የብሔራዊ ማንነት ግንባታ አካል ኾነው አገልግለዋል፡፡

የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ የተደረሱት ዐርበኞች በሕይወተ ሥጋ እያሉ ከጠላት ጋር ያደረጉት ተጋድሎ ትዝታ ከሕዝቡም፣ ከዐርበኞችም አእምሮ ሳይደበዝዝ፣ የዐርበኝነት ተጋድሎ የፈጸሙ ኢትዮጵያውያን በጫካ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ የነበራቸውን አለባበስና ጎፈሬ አበጣጠር ሳይለውጡ፣ የዐርበኝነት ወኔያቸው፣ ሀገራቸውን ከጠላት የመከላከል ቁርጠኛ አቋማቸውና ስሜታቸው እንደጸና ነበር፡፡ ሚያዝያ ፳፯ ቀን በሚከበረው የድል ቀን ዐርበኞች ፀጉራቸውን አጎፍረው ትጥቃቸውን አሳምረው እየሸለሉና እየፎከሩ ማየታቸው፣ በጊዜው በየትምህርት ቤቶቹ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮችን የሚዘምሩ ወጣቶች የዐርበኞችን ማንነት ይበልጥ እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፡፡ የዐርበኞች የትናንት ወኔያቸውና ስሜታቸው ሀገራቸውን ከጠላት ለመከላከል የነበራቸው ቁርጠኛ አቋም፣ ሳይላላ፣ ሳይለወጥ፣ በሕይወተ ሥጋ እያሉ የሚዘምሩት ወጣቶች በአንደበታቸው የሚዘምሩት፣ በጆሮው የሚያዳምጡት መዝሙር የሚያመጣላቸውን ምስል በዐይናቸው ዐይተው አርአያነታቸውን ለመከተል፣ እንዲነሣሡ ያደርጋቸዋል፡፡ መዝሙሮቹ ከተጠቀሰው አገልግሎታቸው በተጨማሪ ከኢጣልያ ጋር ለዐምስት ዓመታት የተደረገውን የተጋድሎ ታሪክ ይዘክራሉ፡፡

የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ መጀመሪያ ሲደረሱ የመጨረሻዎቹ ኹለት ሥንኞች አንድ ዓይነት ነበሩ፡ በተመሳሳይ ይዘታቸው ለተወሰኑ ዓመታት አገልግሎት ሰጡ፡፡ ከ፲፱፻፴፭ ዓ. ም. በኋላ ግን ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ የሚዘመረው መዝሙር የመጨረሻ ኹለት ሥንኞች ተለውጠው ሰንደቅ ዓላማውን ክብር ለማዋረድ የሚያስቡና የሚሞክሩ የውጭ ጠላቶችን መከላከልና ነጻነትን የማስከበር፣ የመጠበቅ ኀላፊነት የንጉሠ ነገሥቱ መኾኑን በሚገልጹ ሥንኞች ተተኩ፡፡ ምሽት

ሰንደቅ ዓላማው ሲወርድ በሚዘመረው መዝሙር ግን ሰንደቅ ዓላማውን የማስከበርና የመጠበቅ ኀላፊነት የዐርበኞች ኢትዮጵያውን መኾኑን መግለጹ እንዲቀጥል ተደረገ፡፡

በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የመንግሥት ለውጥ በመካኼዱና ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ይመሩት የነበረው ዘውዳዊ ሥርዓት ተለውጦ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በመተካቱ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ ከአገልግሎት ታገዱ፡፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ ለመታገዳቸው ምክንያቶቹ፡- አንደኛ፣ ጠዋት በሚዘመረው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር የለውጡ መሪዎች ከሚያራምዱት የፖለቲካ አስተሳሰብ ጋር የማይጣጣም በንጉሥ የሚመራ ሥርዓት ማራመጃ ሐሳብ መገለጹ ነው፡፡ ንጉሥ የሚልን የሥልጣን መጠሪያ የሀገር መሪ በሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ማንቆለጳጰስ የወቅቱ መንግሥት ከሚከተለው የፖለቲካ አስተሳሰብ ጋር የሚጣጣም አልነበረም፡፡ የለውጡ መሪዎች ይከተሉት ከነበረው ወይም “እንከተለዋለን” ከሚሉት የፖለቲካ አስተሳሰብ (በኋላ የኅብረተሰባዊነት ርዕዮተ ዓለም እንከተላለን ማለታቸውን ልብ ይሏል) ጋር ንጉሥ የሚለው ቃል የሚገልጸው ሐሳብ አይጣጣምም፡፡ ስለኾነም ንጉሥ የሚለውን ቃል ማውገዝና ማስወገድ ሥልጣን ላይ የነበረው መንግሥት አጥብቆ ይሻ ስለነበር መዝሙሩ ለመታደጉ አንድ ምክንያት ነው፡፡

ኹለተኛ፣ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ በይዘታቸው በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የተካኼደውን የፖለቲካ ለውጥ ማራመጃ ሐሳብ እንደሌላቸው መቁጠሩ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ እንዲታገዱና በሌላ እንዲተኩ ኹለተኛ ምክንያት ኾነ፡፡ በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ለውጡን የሚደግፉ የፖለቲካ ማራመጃ ሐሳቦች እንዲንጸባረቁ የለውጡ መሪዎች መፈለጋቸው አገልግሎት ላይ የነበሩትን የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች በሌላ ለመተካት ምክንያት ነው፡፡ ይኽንንም አገልግሎት ይሰጡ የነበሩትን እንዲተኩ በታጩት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች የለውጡ መሪዎች እንከተለዋለን የሚሉት የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ሐሳቦች እንዲካተቱ ከተደረገው መረዳት ይቻላል፡፡ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ በሚኖር ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ምክንያት የተከሰተን የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ አላካተተም በሚል የሀገር ጥሪት የኾነን የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ማገድና ለመለወጥ ማቀድ ተገቢነት የለውም፡፡ የተወሰደው ርምጃ ብሔራዊ ጥሪቱ (ሀገራዊ ቅርሱ)ተገቢው አገልግሎት እንዳይኖረው አድርጓል፡፡

ሦስተኛ፣ የቀዳማዊ ዐፄ ኀይለ ሥላሴን መንግሥት በኹሉም መስክ አጠይሞ ወይም ጥፋተኛ አድርጎ መግለጽ ከእሳቸው ሥልጣን የወሰደው መንግሥት እንደፖለቲካ ማሳኪያ ስልት መጠቀሙ ስለነበር ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ለሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ መደረስ ምክንያት የኾነውን፣ የዐርበኞች ተጋድሎና ድል በየዓመቱ የሚታወስበትን የድል ቀን ከሚያዝያ ፳፯ ቀን ወደ መጋቢት ፳፰ ቀን ቀይሯል፡፡ ይኽ ቀን ዐርበኞች ለዐምስት ዓመታት የከፈሉት መሥዋዕትነት የተገታበት፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከዐምስት ዓመት የሽንፈት፣ የስደትና የትግል ጊዜ በኋላ በእንግሊዝ ጦር ድጋፍ አዲስ አበባ የገቡበትና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በቤተ መንግሥታቸው እንዲውለበለብ ያደረጉበት ዕለት ነው፡፡ ሚያዝያ ፳፯ የድል ቀን ኾኖ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንዲከበር የተደረገበትን ምክንያት፡- “የኢትዮጵያ ልጆች ከባዕድ የመከራ ቀምበርና ከዘለዓለም ባርነት ነጻ የወጡበት ቀንና እኛም ዐምስት ዓመት ሙሉ ተለይተነው ከነበርነው ከምንወደውና ከምንናፍቀው ሕዝባችን ጋራ ለመቀላቀል የበቃንበት ቀን ስለሆነ ይህ

ቀን የተከበረና የተቀደሰ በያመቱም ታላቁ የኢትዮጵያ በዓል የሚውልበት ነው።” (ከበደ፣ 2007፤ 424) በማለት ንጉሠ ነገሥቱ በተናገሩት መሠረት ነው።

ደርግ የድል ቀኑን የቀየረው ንጉሠ ነገሥቱ በድል አድራጊነት የገቡበት ቀን ለማጠየምና የኢጣልያ ጦር በዐርበኞች ተጋድሎ በእንግሊዝ ጦር ድጋፍ ተሸንፎ አዲስ አበባን የለቀቀው መጋቢት ፳፫ ቀን ነው በሚል ነው። ይኹንና የደርግ መንግሥት ከሥልጣን ከተወገደ በኋላ የኢትዮጵያውያን የድል ቀን ድሮ በሚከበርበት ሚያዝያ ፳፯ ቀን  እንዲከበር መደረጉ በንጉሠ ነገሥቱ የታወጀ የድል ቀን በዐል ትክክል እንደነበር ያስረዳል።[35]

የኢጣልያን ጦር ድል በተደረገ ማግሥት የተደረሱት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች በኢትዮጵያና በኢጣልያ ጦር መካከል የተደረገውን ጦርነትና የተገኘውን ድል በመዘከራቸው የታሪካችን አካል ቅርሶቻችን ናቸው። ዐርበኞች ለዐምስት ዓመታት ከኢጣልያ ጦር ጋር ያደረጉትን ተጋድሎ፣ የከፈሉትን መሥዋዕትነት እና ያገኙትን ድል የሚዘክረው መዝሙር ንጉሥ የሚለው ቃል ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ በሚዘመረው መዝሙር ከመካተቱ በስተቀር ሥልጣን ላይ የነበረውን መንግሥት የሚያስከፋ፣ ከሚያራምደው ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ጋር የሚጋጭ አመለካከት አልተንጸባረቀበትም። ይኽንንም፣ አንደኛ፣ ጠዋት በሚዘመረው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ሦስተኛ ሥንኝ የሚነበበውን ንጉሥ የሚል መጠሪያ፣ እንደ አስፋው (1991፤ 26) መሪ በሚል ቃል መተካት ይቻል ነበር። ኹለተኛ፣ ጠዋት በሚዘመረው የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር የመጨረሻው ሥንኝ ላይ የሚነበበው “ንጉሥ” የሚል ቃል የተጨመረበት በመሻሻሉ ምክንያት ነው። መዝሙሩ መጀመሪያ ሲደረስ የሚጠራው ዐርበኛ የሚልን ቃል ነበር። ስለኾነም መዝሙሩ አገልግሎት መስጠቱ እንዲቀጥል ለማድረግ መጀመሪያ ሲደረስ የነበሩትን ሥንኞች በመተካት ንጉሥ የሚለውን ቃል ማውጣት ይቻል ነበር።

በምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ ይዘመር የነበረው መዝሙር ንጉሥ የሚል ቃል የለበትም። ሰንደቅ ዓላማችንን፣ ነጻነታችንን ማስከበራቸውና ወደፊትም በተመሳሳይ ተጋድሏቸው ነጻነትን ለማስከበር ዐርበኞች ቃል ኪዳን መግባታቸው የተገለጸበት ነው። የለውጡ መሪዎች ከሚያራምዱት ሐሳብ ጋር የማይጣጣምን ሐሳብ የሚገልጽ ቃል ወይም ሐረግ የለበትም። መዝሙሩን በሌላ ለመተካት አስገዳጅ ምክንያት ነው የሚባል ሐሳብ በማስረጃነት መጥቀስም አይቻልም።

ስለኾነም፣ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ ሲደረሱ ከነበራቸውን ይዘት የኢሕዲሪ መንግሥት ከሚያራምደው የፖለቲካ ሥርዓት ጋር የማይጣጣመውን በማሻሻል አገልግሎታቸው እንዲቀጥልና ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ይቻል ነበር። አገልግሎት መስጠታቸውን

[35]ተጨማሪ ምሳሌ የሚኾነን በ፲፱፻፲፱ የተደረሰውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር በ፲፱፻፳፫ ዓ. ም. በሌላ ብሔራዊ መዝሙር እንዲተካ አድርጓል። በቀዳማዊ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ዘመነ መግሥት የተደረሰው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ዘውድ በመጫን ሀገርን የሚመራ፣ ዙፋን ላይ የሚቀመጥ ንጉሥን የሚገልጽ ቃል በማካተቱ እንዲቀር ተደረገ። ይኹን እንጂ የብሔራዊ መዝሙሩን የሀገር ቅርስነት ታሳቢ በማድረግ አሻሽሎ አገልግሎቱ እንዲቀጠል ማድረግ ይቻል ነበር።

ቢቀጥሉ ኖሮ የኢትዮጵያን የድል ቀን ከማድመቅ አልፈው የዐርበኞች መዘከሪያ መኾን በቻሉ ነበር፡፡ ይኹን እንጂ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹን በቅርስነት ከማስቀጠል ይልቅ አገልግሎት እንዳይሰጡ፣ በሌላ እንዲተኩ ለማድረግ ጥረት አደረገ፡፡ ሥልጣን ላይ የነበረውን መንግሥት የፖለቲካ ማራመጃ ሐሳቦች በሚያንጸባርቁ ሌሎች የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ለመተካት መወሰኑ ተገቢ አልነበረም፡፡

በዚኽ መሠረት ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ለሰንደቅ ዓላማ መዝሙር የሚኾኑ ግጥሞችን እንዲያቀርቡ ባለሙያዎችን በጋዜጣና በቴሌቪዥን ጋበዘ፡፡ በማስታወቂያው መሠረት ከቀረቡት ሥራዎች በአሰፋ ገብረ ማርያም የቀረቡት ግጥሞች እንደተመረጡ ቢገለጽም፣ አገልግሎት ላይ አልዋሉም፡፡ ከዓመታት ቆይታ በኋላ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሥልጣነ መንግሥት "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት" በተባለ ማግሥት በ፲፱፻፹ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ለሰንደቅ ዓላማ የሚኾኑ ግጥሞችን በማቅረብ እንዲወዳደሩ በድጋሚ በማስታወቂያ ጋበዘ፡፡ በዚኹ መሠረት ተወዳዳሪዎች ካቀረቧቸው ግጥሞች ኹለቱ ተመረጡ፡፡

እንዲቀሩ በተባሉትና እንዲተኩ በተመረጡት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች መካከል ተመሳሳይነትም ልዩነትም ይስተዋላል፡፡ ተመሳሳይነታቸው ትኩረታቸውን በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ በማድረግ የኢትዮጵያን ነጻነትና ሉዓላዊነት ለማስከበር መሥዋዕትነት የከፈሉ አባቶች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለልጆቻቸው በቅርስነት ያወረሷቸው መኾኑን ማስረዳታቸው፤ ዐርበኞች የኢትዮጵያን ነጻነትና ሉዓላዊነት ለማስከበር የጠላታቸውን ደም ማፍሰሳቸውንና ጠላትን ገዳይነታቸው ድልም ማግኘታቸውን መዘከራቸው፤ ጠላታቸውን ድል ማድረጋቸውን፣ ማሻነፋቸውን፣ የኢትዮጵያውያን ክብር ማግነናቸውን፣ ዝናቸው እንዲናኝ ማድረጋቸውን ማንጸባረቃቸው፤ መሥዋዕትነት ከፍለው ያስከበሩትን ነጻነት የማስከበር፣ የማስቀጠል፣ ሰንደቅ ዓላማው ከፍ ብሎ በክብር እንዲውለበለብ የማድረግ፣ ከሩቅም ከቅርብም የሚመጣን ጠላት የመከላከል፣ የመመከት፣ የመጠበቅ፣ ለሰንደቅ ዓላማው ዋስትና የመኾን ኀላፊነት የዐርበኞቹን ፈለግ የሚከተለው ትውልድ መኾኑን መግለጻቸው የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የነጻነት ትእምርት የኾነውን ሰንደቅ ዓላማ የኢትዮጵያ ጀግኖች ልጆች እንደሚጠብቁት ዋስትና እንደሚኾኑት ቃል ኪዳን መግባታቸውም ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል፡፡ እንደዚሁም፣ እንዲቀሩ የተባሉት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮችም እንዲተኩ የተመረጡትም የሥንኝ ብዛት ስድስት መኾኑ በቅርፅ መመሳሰላቸውን ይነግራል፡፡

በምሽት ሰንደቅ ዓላማው ሲወርድ እንዲዘመር የተመረጠው መዝሙር ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ ነጻነትና አንድነት ሲሉ የጀግንነት ተግባር የፈጸሙ ኢትዮጵያውያንን ከመዘከር የሰፋ ትርጉም ሊሰጠው ይችላል፡፡ የጀግንነት ተግባር የሚለውም ለዐምስት ዓመታት ከኢጣልያ ጦር የተደረገውን ተጋድሎ፣ የሶማሌ ወራሪ ኀይልን ለመመከትና ድንበርን ለማስከበር የተደረገውን ትግል፣ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል አንድነት ለማስከበር የተከፈለውንና የሚከፈለውን ማስዋዕትነት በጥቅሉ ይጠራል ማለት ይቻላል፡፡

በዐፄ ኀይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት አገልግሎት ይሰጡ የነበሩትን የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች እንዲተኩ በ፲፱፻፳፪ ዓ. ም. የተመረጡት የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ከቀደሙት ልዩ የሚያድርጓቸው በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የተካኼደውን የፖለቲካ ለውጥ ማራመጃ ሐሳቦች የሚያንጸባርቁ መኾናቸው ነው። ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ እንዲዘመር በተመረጠው መዝሙር/ግጥም ውስጥ ነጻነት፣ አንድነት፣ ተስፋ፣ ሥራ፣ ሥልጣኔ፣ ኅሀ፣ዐዲስ ሕይወት እና ጮራ በሚሉት ቃላት የፖለቲካ ማራመጃ ሐሳቦች እንዲገለጹ ተደርጓል። በተመሳሳይ ምሽት ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ እንዲዘመር በተመረጠው ግጥምም ሥልጣን ላይ ለነበረው መንግሥት በፖለቲካ ማራመጃነት የሚያገለግሉ ሐሳቦችን የሚገልጹ ቃላት ተካተዋል። ቃላቱም መብት፣ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አንድነት እና ፋና የሚሉ ናቸው። ይኹን እንጂ በሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮቹ አማካይነት ፖለቲካውን ለማራመድ የሚረዱ ሐሳቦች ለሕዝብ ሳይቀርቡ መንግሥት ከሥልጣን ተወገደ።

ከጥናቱ መረዳት እንደተቻለው በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የነጻነት ትእምርት የኾነውን ሰንደቅ ዓላማ ወጣቱ ትውልድ እንዲረዳና እንዲያከብር ከፍተኛ ጥረት ይደረግ ነበር። ከንጉሡ ሥልጣን የነጠቀው መንግሥት ተመሳሳይ ዕቅድና ዓላማ እንደነበረው ካደረጋቸው እንቅስቃሴዎች መረዳት ይቻላል። በ1983 ዓ. ም. ሥልጣን የያዘው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ግን ለእንዲኽ ዓይነቱ ሥራ የተጋ ነበር ለማለት አይቻልም። ሌላው ቀርቶ የኢትዮጵያ አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል የተቀበለው ሰንደቅ ዓላማ አለው ለማለት የማይቻልበት ኹኔታ እንደፈጠረ በተለያዩ ክፍሎች በሚደረጉ ሰልፎች የሚሳተፉ ኢትዮጵያውያን ይዘዋቸው የሚወጡት ሰንደቅ ዓላማዎችና የፖለቲካ ድርጅት ዐርማዎች ማሳያዎች ናቸው። ስለኾነም መጀመሪያ ኅብረተሰቡ የተቀበለው ሰንደቅ ዓላማ እንዲርማድረግ አስፈላጊ ነው። ቀጥሎም በትምህርት ቤቶች የሰንደቅ ዓላማውን ክብር ከፍ የሚያደርግ፣ የሉዓላዊነትና የነጻነት ትእምርት መኾኑን በመዝሙር ማስተማር አስፈላጊ ነው።

## መረጃ ጽሑፎች


መርስዔ ኅዘን ወልደ ቂርቆስ (አዘጋጅ አምኃ መርዔ ኅዘን):: ፲፱፻፺፱:: *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922*:: አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

መርስዔ ኅዘን ወልደ ቂርቆስ (ብላቴን ጌታ) :: 1943:: *የትእምርተ መንግሥት ታሪክ በመዋዕሲሁ ለቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*::

ሙሉጌታ ስዩም:: 1964:: "የቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ የሕይወት ታሪክ"፣ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ዲማፅ)::

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል:: ፲፱፻፷፩:: *ዝክረ ነገር*:: አዲስ አበባ፤ ሴንተራል ማተሚያ ቤት::

ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው :: 1987::*የተጉዋጎጠ ልብ* :: አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት:: ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት:: ፲፱፻፷፫:: *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፩ኛ መጽሐፍ*:: ኢንግላንድ ባዝ ፲፱፻፷፱ (የታተመበት አገር አልተጻፈም)፤ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት::

ባሕሩ ዘውዴ:: ፪ሺህ:: *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983*:: (ተሻሽሎ የታተመ) አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

ብርሃኑ ገበየሁ:: 1999:: *የአማርኛ ሥነ ግጥም*:: አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች::

ትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር:: ፲፱፻፷፬::*የትምህርት ቤት መዝሙር*:: አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት::

አሰፋ ገብረ ማርያም ተሰማ:: 1971:: *የማስከረም ጮራ፤ ልዩ ልዩ ግጥሞች*:: አዲስ አበባ፤ ቼምበር ማተሚያ ቤት::

አስፋው ተፈራ:: 1991:: *የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰንደቅ ዓላማ Ethiopian National Flag በደም ጠብታ የጸና ታሪክ* :: አዲስ አበባ፤ ቼምበር ማተሚያ ቤት::

..............:: ፲፱፻፹:: *አዲስ ዘመን ጋዜጣ* :: ፵፯ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፷፻፴፱ ገጽ ፬:: ኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ:: ፲፱፻፹:: "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሰንደቅ ዓላማ ዐዋጅ"፣ *ነጋሪት ጋዜጣ* :: ዐዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፹::

ኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት:: ፲፱፻፹:: ኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት፣ *ነጋሪት ጋዜጣ* :: አዲስ አበባ፤ አርባ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፩ አዋጅ ቁጥር ፩/ ፲፱፻፹::

ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል:: 2001::*አማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ፤ አዲስአበባዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት:: ፲፱፻፷፷:: "የብሔራዊ ዓርማና መዝሙር አሸናፊዎች ከዋናው ሊቀ መንበር ቀርበው ተመሰገኑ፣" *አዲስ ዘመን* ፴፭ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፷፻፸፤ ገጽ ፲፩::

ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት:: ፲፱፻፷፯:: "ስለኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር በድጋሚ የወጣ ማሳሳቢያ፣" *አዲስ ዘመን* :: ፴፭ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፺፻፷፤ ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯፣ ገጽ ፩ እና ፫::

ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት:: ፲፱፻፷፯:: "ሊቃውንት አዲስ የሕዝብ መዝሙር እንዲያዘጋጁ ተጠየቀ፣"*አዲስ ዘመን*:: ፴፬ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፫፻፵፬፤ መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፷፯፣ ገጽ ፩ እና ፫::

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት:: ፲፱፻፹፯:: "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯፣" *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*:: አዲስ አበባ፤ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፩ ነሐሴ ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፯::

ከበደ ተሰማ :: ፲፱፻፷፪:: የታሪክ ማስታወሻ:: አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ሊሚትድ::

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት:: 1978:: *ማርክሳዊ ሌኒናዊ መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት::

ዮሐንስ አድማሱ (አዘጋጅ) :: ፪ሺህ፩:: *ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ አጭር የሕይወቱና የጽሑፉ ታሪክ 1887-1939*:: (ዮሐንስ አድማሱ 1929-1967) (አሰናኘ ዮናስ አድማሱ) አዲስአበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

ደስታ ተክለ ወልድ:: ፲፱፻፷፪:: *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያቤት::

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ። ሺ፱፻፳፯፡፡ *የወንድ ልጅ ኩራት ስለ ሀገር መሞት*፡፡ አዲስ አበባ፤ ቀ፤ ኃ፤ ን፤ ነ፤ ዘኢ.፤ ለቤ፤ ሳ፤ ሆ፤ በተሰጠ ማ ቤ፡፡

ዘውዴ ረታ፡፡ 2005፡፡ *የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ፩ መጽሐፍ ፲፱፻፳፫ - ፲፱፻፵፰፣ እ. ኤ. አ. 1930- 1955*፡፡ አዲስ አበባ፣ ሻማ ቡክስ (ሮኖቦት አታሚዎች ኃ. የተ.የግ.ማ.)፡፡

ገብሩ አሥራት፡፡ 2007፡፡ *ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ*፡ (ሁለተኛ እትም) አዲስ አበባ፤ (መተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)፡፡

ገዛኸኝ ውቤ፡፡ ፲፱፻፷፩፡፡ "የነጻነት ክብር፣ የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር እየታደሰ ስለመሔዱ፣" *አዲስ ዘመን*፡፡ አንደኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፪፣ ገጽ ፱፡፡

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፡፡ ፲፱፻፷፯፡፡የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፷፬/፲፱፻፷፯፡፡ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ሠላሣ አምስተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፲፩፡፡

ፍቅረ ሥላሴ ወግ ደረስ፡፡ 2006፡፡ *እኛና አብዮቱ*፡፡ አዲስ አበባ፤ ፀሐይ አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅት፡፡

Simeneh Betreyohannes. 2008. "Music and Politics in Twentieth Century Ethiopia: Empire, Modernization and Revolution." A Thesis Submitted to the School of Graduate Studies of Addis Ababa University in Partial Fulfilment of the Requirements for the Degree of Masters of Arts in Ethiopian Studies, Contemporary Cultural Studies Program.